# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## አስረኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ አስረኛ ክፍል

አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

አስረኛ ክፍል




የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ይህን መፅሐፍ በጥንቃቅ ያዝ/ያዥ

ቀጥሎ መጥሀፉን በጥንቃቅ ስመያዝ የሚረዱ አሥር ነጥቦች ቀርበዋል።

1. መፅሐፉን እንደ ፕላስቲክ ፣ ጋዜጣ ወይንም ወርቀቶች በመጠቀም ሽፍን /ሽፍኝ ።
2. ምንጊዜም መፅሐፉን በንፁህ እና ደረቅ ቦታ አስቀምጥ/አስቀምጭ ።
3. መፅሐፉን በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት እጆችህ/እጆችሽ ንፁህ መሆን አለባቸው ።
4. በመፅሐፉን  ሽፋን ላይ ወይንም በውስጥ ገጾች ውስጥ አትፃፍ/አትፃፊ ።
5. ለመፅሐፉ  የገፅ ማስታወሻ መያዝ ሲያስፈልግ ቁራጭ ወረቀት ተጠቀም/ተጠቀሚ ።
6. ከመፅሐፉ ውስጥ ገጾችን ወይንም ስዕሎችን በፍፁም ቀደህ/ቀደሽ አታውጣ/ አታውጭ ።
7. የተቀደዱ ገጾች ሲኖሩ በማጣበቂያ ወይም በፕላስተር ጠግን/ጠግኝ ።
8. መፅሐፉን በቦርሳ ውስጥ ስታስገባ /ስታስገቢ ጥንቃቅ አድርግ/ አድርጊ ።
9. መፅሐፉን ለሌላ ሰው በምታቀብልበት/በምታቀብይበት ወቅት ጥንቃቄ አድርግ / አድርጊ ።
10. በአንድ ጊዜ ጥቂት ገጾችን ብቻ በጥንቃቄ ግለጥ/ ግለጭ ።

# አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## አስረኛ ክፍል

**አዘጋጆች፡**

ሙሉጌታ ደታየው (ፒ.ኤች.ዲ)

ጋሻው አረቴ (ፒ.ኤች.ዲ)

**አርታኢዎች፡**

ታደሰ ሲባሞ (ፒ.ኤች.ዲ)

ጌታቸው አዱኛ (ፒ.ኤች.ዲ)

**ሰዓሊ፡**

ታደሰ ደሄደስ (ኤም.ኤስ.ሲ)

**ዲዛይነር፡**

አጥናፉ ዓለሙ (ኤም. ኤስ. ሲ)

**ገምጋሚዎች፡**

መኮንን አስማማው (ኤም.ኤ)

ግሩም ጥበቡ (ኤም.ኤ)

ፍሬሕይወት አሰፋ (ኤም.ኤ)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ

# ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው ስራ የተጀመረው በ2022 እ.ኤ.አ ሲሆን፣ የዲዛይን፣ ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስ በትምህርት ሚኒስቴር በአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP-E) አማካኝነት ነው:: የገንዘቡ ምንጭ ደግሞ ብድርና እርዳታ ነው:: አበዳሪዎችም፦ የዓለም ባንክ፣ የእንግሊዝ ዓለማቀፍ ልማት ድርጅት (DFID) ከውጭ ልማት ቢሮ (FCDO) ጋር በመተባበር፣ ከፊላንድ የውጭ ጉዳይ ቢሮ፣ ከኖሮጂያን ኢንባሲ፣ ከተባበሩት መንግስታት የህጻናት ፈንድ (UNICEF)፣ ከአለማቀፍ የትምህርት አጋርነት ድርጅት (GPE) እና ከዳኒሽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዓለማቀፉ ትረስት ፈንድ በኩል እገዛው ተገኝቷል:: ለዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም

የዚህን መጽሐፍ ክፍል ያለባለቤቱ ፈቃድ በተለያዩ መሳሪያዎች እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የሚያመለክት ሲሆን፣ በተጨማሪም የኮፒራይትና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 55 10ኛ ዓመት አዲስ አበባ ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ይከለክላል::

ይህ መጽሐፍ ለህትመት እንዲበቃ ተሳትፎ ላደረጉ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና የተለያዩ ባላድርሻ አካላት ትምህርት ሚስቴር ምስጋናውን ያቀርባል:: በተለይ ደግሞ ትልቁን የማስተባበር ድርሻ በመውሰድ የጽሑፉን ዝግጅት ላስተባበረው ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአጋሮቹ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ የላቀ ምስጋና ይደረሳቸው ይላል::

የኮፒራይትና የሥዕል ባለቤትነት መብቶችን በተቻለ መጠን ለማክበር የሚቻለው ሁሉ ጥረት ተደርጓል:: ነገር ግን ሳናወቅ በስዕተት ሳንጠቀሳቸው የተዘለሉ ጽሑፎችና ስዕሎች ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን፣ ስዕተቱን አራት ኪሎ በሚገኘው ዋና መስሪያቤት፣ ትምህርት ሚኒስቴር በአካል በመቅረብ ማመልከት የሚቻል ሲሆን፣ በአካል መምጣት የማይችሉ ደግሞ በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 1367 አዲስ አበባ ብለው መላክ ይችላሉ::

አሳታሚ ድርጅት

______________ማተሚያ ቤት

የመ.ሳ.ቁ-----------------------

-------------------ኢትዮጵያ

በትምህርት ሚኒስቴር ውል ቁጥር____________

ISBS:978-999944-2-046-9

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


መግቢያ ........................................................... i

ምዕራፍ አንድ: የሥራ ባህልና ምርት ........................................................... 1

ምዕራፍ ሁለት: የህይወት ክህሎቶች........................................................... 16

ምዕራፍ ሶስት: ሱስና አደንዛዥ ዕጽ ........................................................... 29

ምዕራፍ አራት: ልቦለድ ........................................................... 41

ምዕራፍ አምስት: እንግዳ ተቀባይነት ........................................................... 51

ምዕራፍ ስድስት: ባህላዊ ክንውኖች ........................................................... 61

ምዕራፍ ሰባት: አካቶ ትምህርት ........................................................... 72

ምዕራፍ ስምንት: ሥነግጥም ........................................................... 82

ምዕራፍ ዘጠኝ: አንድነትና ብዝሃነት ........................................................... 91

ምዕራፍ አስር: ስደት ........................................................... 101

ማጣቀሻ ........................................................... 109

አባሪ ........................................................... 110

# መግቢያ

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ነው፡፡ ከትምህርቱ የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶችም፤

1. የማዳመጥ_____________ ክሂልን ማዳበር
2. የንግግር ______________ ክሂልን ማዳበር፣
3. የንባብ ________________ ክሂልን ማዳበር፣
4. የጽሕፈት ______________ ክሂልን ማጎልበት፣
5. የቃላት _______________ ዕውቀትን ማዳበር
6. የሰዋስው ______________ ዕውቀትን ማበልጸግ የሚሉ ናቸው፡፡

መጽሐፉ የተሰናዳው ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሐትምህርት መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ተማሪዎች በደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ዓለማቀፋዊ፣ ወዘተ. ይዘቶችን/ እሴቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ፣ መጽሐፉ ለይዘቶችም ከክሂሎች ያልተናነሰ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ ተማሪዎች በምንባቦች አማካይነት የንግግርና የማዳመጥ፣ የንባብና የጽሕፈት ክሂሎቻቸውን፤ የቃላትና የሰዋስው ዕውቀታቸውን እንዲሁም የሥነጽሑፍ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ነው፡፡

መጽሐፉ ከሕይወት ተሞክሮ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራትና መልመጃዎች በየምዕራፎቹ ተካተዋል፡፡ ተግባራቱም ተማሪዎቹ ቋንቋውን በተለያየ መንገድ እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አንድ ፡ የሥራ ባህልና ምርት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- አዳምጣችሁ መረጃዎችን ትናገራላችሁ::
- በአዳመጣችሁት መሠረት የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች ትመልሳላችሁ::
- የስራ ባህልና ምርት ከሚለው ይዘት የአዳመጣችሁትን ፍሬ ሀሳብ ታብራራላችሁ::
- በተመረጡ ይዘቶች ላይ ውይይት ታካሂዳላችሁ::
- አውድን መሠረት ያደረገ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- በሚና-ተኮር ልምምድ ንግግር ታከናውናላችሁ::
- ምንባብ አንብባችሁ የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች ትመልሳላችሁ::
- ሀሳቦችን አፍልቃችሁ ትጽፋላችሁ::
- የህይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ::
- ቃላት ምንባብን ለመረዳት ያላቸውን አስተዋጽኦ ትገልጻላችሁ::
- የቃላትን ቀጥተኛና አውዳዊ ፍችዎች ትሰጣላችሁ::
- በቃል ውስጥ የሚገኙ ምእላዶችን ትለያላችሁ::



## ክፍል ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ሰነፍ ይከስራል፣ ሰራተኛ ይከብራል

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የስኬት ምስጢሮች የምትሏቸውን ዘርዝሩ::
2. በሕይወት ውስጥ ውጤታማ ለመሆን ዕደለኛ ከመሆንና ጠንከሮ ከመስራት ወሳኙ የትኛው ነው?

የተግባር መመሪያ

“ሰነፍ ይከስራል፣ ሰራተኛ ይከብራል” በሚል ርእስ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከአዳመጣችሁ በኃላ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ::

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

### ፩. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. የመሬቱ ተከራይ  የሥራ ውጤታማነት ምስጢር ሰርቶ ማሰራቱ ነበር፡፡
2. የመሬቱ ባለቤት አገልጋዮች  ታታሪ ሠራተኞች ነበሩ፡፡
3. የመሬቱ ባለቤት ለሠራተኞቹ በየቀኑ የሠሩበትን ሂሳብ አይከፍልም ነበር፡፡
4. የመሬቱ ባለቤት ሙሉ መሬቱን አከራይቶታል፡፡
5. የመሬቱ ተከራይ  ውጤታማ የሆነው ከሠራተኞቹ ጎን እኩል ጠንክሮ ስለሚሰራና ስለሚያሰራ ነው፡፡
6. የመሬቱ ባለቤት ያሰበውን ለማሳካት ሠራተኞችን በስራ ያግዝ ነበር፡፡
7. ተከራዩ መሬት ለመግዛት የሚበቃ ገንዘብ ያገኘው በተከራየው መሬት ላይ ሠርቶ በማትረፉ ነው፡፡
8. አከራዩ ለኪሳራ የተዳረገው በሠራተኞቹ ስንፍና ብቻ ነው፡፡

### ፪. ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. የመሬቱ ባለቤት እቅድ ምን ነበር?
2. የመሬቱ ባለቤት እቅዱን  ከግብ ለማድረስ ሊጠቀምባቸው የፈለጋቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
3. የመሬቱ ባለቤት ሠራተኞችን ትእዛዝ የሚሰጣቸው ምን እያለ ነበር? እርሱስ ምን ያደርግ ነበር?
4. የመሬቱ ባለቤት ለምን ያህል ጊዜ ያሰበውን ስራ አከናወነ?
5. የመሬቱ ባለቤት  ያሰበው ነገር ያልተሳካለት ለምንድን ነበር?
6. የመሬቱ ባለቤት  ያሰበው ነገር እንዳልተሳከለት ሲያውቅ ምን አደረገ?
7. የመሬቱ ተከራይ ውጤታማ ሊሆን የቻለው በምን ምክንያት ነው?
8. የምንባቡ አጠቃላይ መልእክት ምንድን ነው?
9. ፀሐፊው የተጠቀማቸው ነገር ግን በዕለት ከዕለት ተግባቦት ብዙም ግልጋሎት ላይ የማይስተዋሉ ቃላትን በመዘርዘር በፍችዎቻው ላይ ተወያዩባቸው፡፡
10. በአከባቢያችሁ ጠንክረው በመሥራታቸው ውጤታማ የሆኑ ሰዎችን በምሳሌነት በመጥቀስ የሥራ ባህልና ስኬት ያላቸውን ግንኙነት አብራሩ፡፡

### ፫. በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ በቡድን በቡድን በመሆን ክርክር እና ውይይት አድርጉ፡፡

1. የመሬቱ ባለቤት ለተካራዩ መሸጡ ትክክልና ተገቢ ውሳኔ ነው፤ የሚለውን ሀሰብ ደግፋችሁና ነቅፋችሁ ተከራከሩ፡፡
2. አከራዩ ሰው ከኪሳራ ለመውጣት ምን ማድረግ ነበረበት? በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ተወያዩ፡፡



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

**በውይይት ጊዜ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- የውይይት ርእስ ጉዳይ መምረጥ፣
- የውይይት ዓላማ መለየት፣
- ተወያዮችን መምረጥ፣
- የቡድን መሪ መምረጥ፣
- መረጃ መሰብሰብና ማደራጀት፣
- ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
- በቂ ዝግጅት አድርጎ መገኘት፣
- ከመናገር በፊት ማሰብ፣
- ተራን ጠብቆ መናገር፣
- ሀሳብን በአግባቡ ግልጽ በሆነ ቋንቋና ለሁሉም ተሳታፊዎች ሊሰማ በሚችል ድምፅ አብራርቶ ማቅረብ፣
- ሌሎች ተወያዮች በሚቀርበው ሀሳብ ወይም በሚሰነዘረው ነጥብ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ መጋበዝ፣
- ሀሳብን በበቂ ትንተናና ማብራሪያ በምክንያት አስደግፎ ማቅረብ፣
- የግለሰቦችን ሀሳብ እንጂ ግለሰቦችን አለመንቀፍ፣
- የውይይት ተሳታፊዎችን ማክበር (እርስበርስ  መከባበር)፣
- በጥሞና ማዳመጥ፣
- የውይይቱ አድማጮች ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላቸው እድል መስጠት፣
- በመጨረሻም የውይይቱን ተካፋዮች አመስግኖ ውይይቱን ማጠናቀቅ ይገባል፡፡

**፩. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ተግባራት በመመሪያዎቹ መሠረት ተግብሩ፡፡**

1. የሽመና ሥራ በኢትዮጵያዊያን የስራ ባህል ውስጥ በአለው አስተዋጽኦ ላይ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡
2. በየአካባቢያችሁ በቡድን የሚሠሩ ሥራዎችን በማንሳት እንዴት እንደሚከወኑ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
3. ጉልበት የሚፈልጉ ስራዎችን በግል ከመሥራት ይልቅ በጋራ መሥራት ውጤታማ ያደርጋል፤ የሚለው ሀሳብ እውነትነት አለው ትላላችሁ? ተወያዩበት፡፡

፩. ለራት ለራት በመሆን ቡድን መሥርቱና አንዳችሁ የአንድ ቀበሌ የግብርና ባለሙያ፣ ቀሪዎቻችሁ ደግሞ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ገበሬዎችን ሚና በመውሰድ የሚከተለውን የሚና ለዋጭ ተግባር እየተቀያየራችሁ አከናውኑ፡፡

የግብርና ባለሙያው፡ እንደየአካባቢው በእርሻ ስራ ወይም በእንስሳት እርባታ እንዴት ስኬታማ መሆን እንደሚቻል ገለጻ ያደርጋል፤ ምክር ይሰጣል፡፡

ገበሬዎቹ፡ ካላቸው ልምድ በመነሳት እርሻ ስራ ወይም እንስሳት እርባታ ሲያከናውኑ የገጠሟቸውን ችግሮችና ያሏቸውን ጥሩ ተሞክሮዎች ለግብርና ባለሙያው ያካፍላሉ፡



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## አውራምባ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. በማኅበረሰባችሁ ያለ የስራ ባህል ምን ይመስላል? ተናገሩ፡፡
2. ምንባቡ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል? ተነጋገሩበት፡፡
3. የአውራምባ ማህበረሰብ ምን ዓይነት የስራ ባህል ያለው ይመስላችኋል?

ድህነት በተንሰራፋባት፣ ኋላቀር አስተሳሰብ ሥር በሰደደባት፣ የሃይማኖትና የባሕል ተጽእኖ ጠንክሮ በሚታይባት ሀገር ውስጥ አዲስና በመሰረቱ የተለየ አስተሳሰብ በተለይም በማህበረሰቡ ዘንድ እንደነውር የሚቆጠር ፍልስፍና ይዞ ብቅ ማለት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በሌላ አባባል ያረጀና ያፈጀውን እሣቤ ሽሮ ለለውጥ የሚበጅ ተራማጅ አስተሣሰብ ማመንጨት፣መቀበልና መተግበር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ለውጥ በአንድ አካባቢ መንጭቶ ሲቀርብ ለማመንና ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ሁኔታዎች ቢያስገድዱት እንኳ እጅግ ፈታኝና አዝጋሚ መሆኑ አይቀርም፡፡

ይሁን እንጂ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚገኘው የደቡብ ጐንደር አስተዳደር ዞን ፎገራ ወረዳ ውስጥ የሚገኝና አሁን ካለው ሕብረተሰብ አመለካከት አንጻር ሲታይ በእጅጉ ያፈነገጠ ወይም ወጣ ያለ ይመስላል፡፡ ነገር ግን እጅግ ተራማጅና ጠቃሚ አስተሳሰብና ጠንካራ የስራ ባህል በመያዝ ራሱን አቅንቶና ለመስዋዕትነትም አዘጋጅቶ ኋላቀር አመላካከቶችንና ጎታች የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችን ታግሎ በማሸነፍ ከጠፍር የጠነከረውን ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ጫና በጽናት የመከተና ድህነትን ተረት ለማድረግ ዘላቂ ሕይወቱን በሥራና በሥራ ብቻ ለመለወጥ ቀኑ አልበቃው ብሎት መሽቶ እስኪነጋ ድረስ ሲባትል የሚኖር ነው፡፡

ይህ ማህበረሰብ አውራምባ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጠንካራ የስራ ባህሉና በመልካም ሥነምግባሩ ታዋቂነትንና ዝናን እያተረፈ የመጣ፣ ታታሪነትን መለያቸው ያደረጉ አባላት የተሰበሰቡበት፣ የመልካም አስተዳደርና የጠንካራ የስራ ባህል ባለቤት እንዲሁም የሰላምና የፍቅር ተምሳሌት መሆን በመቻሉ የቱሪስቶችንና የደጋፊዎቹን ቀልብ በቀላሉ መሳብ የቻለ ማህበረሰብ ለመሆንም በቅቷል።

የአውራምባ ማህበረሰብ እንዴትና መቼ እንደተመሠረተ ለማህበረሰቡ ልደትና ዘላቂ ሕልውና መሠረት የሆነው ፍልስፍና (እምነት) እንደምንና ከየት ሊመነጭ እንደቻለ ለማወቅ የማህበረሰቡ መሥራችና መሪ የሆኑትን አቶ ዙምራ ኑሩን በአካል አግኝቶ ስለሁኔታው ማነጋገር የግድ ይላል። በመሆኑም አቶ ዙምራ የማህበረሰቡን አነሣስ አስመልክተው ሲጠየቁ በአጭሩ የሚከተለውን መልስ በመስጠት ሁኔታውን ያብራራሉ። ወላጆቼ ገበሬዎች ነበሩ፤ የሚተዳደሩትም በእርሻ ሥራና ከብት በማርባት ነበር፣ ኑሯቸውም ድካም የሞላበት፣ ችግር የወረሰውና ከእጅ ወደ አፍ ያልዘለለ ነበር። ገና የሁለትና የሦስት አመት ልጅ ሳለሁ ከታዘብኳቸውና በወቅቱ ስሜቴን በእጅጉ ካቆሰሉት ሁኔታዎች መካከል አንዱ የጾታ የበላይነትና የበታችነት ሁኔታ ነግሶ ማየቴ ነበር። ሁለቱም ወላጆቼ ቀኑን ሙሉ አብረው በሥራ ተጠምደው ሲባክኑ ውለው አመሻሽ ላይ ወደቤት ይመለሳሉ።

ይሁን እንጂ የአባቴ ሥራ እዛው ማሳ ላይ የቀረ ይመስል መጥቶ ቤቱ አረፍ ሲል የእናቴ ግን ቢያንስ እስከ ምሽቱ አምስትና ስድስት ስአት ድረስ ይቀጥላል። በመሆኑም እናቴ ነግቶ እስኪመሽ፣መሽቶ እስኪነጋ ጭምር የምትለፋው ልፋት የሁሉም ሴቶች እጣፈንታ መሆኑን በልጅነት አእምሮዬ እየተገነዘብሁ መጣሁ ይላሉ አቶ ዙምራ ኑሩ የልጅነት ትውስታቸውን መለስ ብለው በመቃኘት። ቀጥለውም ችግሯን ያቃልልሁ መስሎኝ እናቴን በሥራ ላግዛት ሞከርኩ፣ ሆኖም ገና ሕጻን በመሆኔ የሚቻለኝ አልሆነም። ተወልጄ ያደግሁበትን አካባቢ ሕብረተሰብ አኗኗር ልብ ብዬ ስመለከተው ደግሞ ማህበራዊና ባህላዊ ሕይወቱ በሌላም ችግር የተተበተበ ሆኖ አገኘሁት። ሥርቆት፣ ጸብ፣ ውሸት፣ እርስ በርስ መበዳደልና ያለአግባብ መጠቃቀም በግልጽ ሰፍኖ ይታያል። አንዱ የሌላውን መብት በግልጽ ይጋፋል፣ ለግል ጥቅም ማጋበስና ለስልጣን ሲባል ግጭት ይፈጥራል። በመሆኑም ፍቅር፣ መከባበር፣ መቻቻልና የመሳሰሉት የሕብረተሰቡ መልካም እሴቶች ብዙም ቦታ ሲሰጣቸው አይስተዋልም።

በዚያ ላይ የከፋ ድህነት አለ። ከጥገኝነትና ኋላቀርነት ነጻ አልወጣንም። ለህጻናት መብትም ተገቢ ጥበቃና እንክብካቤ አይደረግም። በጉብዝና ዘመናቸው ለሀገራቸውና ለወገናቸው ኩራት የነበሩ አረጋዊያንና አቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎች ውለታ ተዘንግቶ አስታዋሽ ማጣት እጣ ፈንታቸው ሆኖ አገኘሁት። እነዚህና መሰል አሉታዊ ውጤት የሚያስከትሉ አድራጎቶችና እሣቤዎች ለምን ከህብረተሰቡ መካከል አይወገዱም? እስከመቼስ ነው ከማህበረሰባችን ጋር እንዲህ ተጣብቀው የሚቆዩት? ብዬ ከመጠየቅ ጀምሮ ችግሮቹን በዘላቂነት ሊያስወግድ የሚችል መፍትሄ ለማግኘትም በልጅነት አዕምሮዬ ማሰላሰል ጀመርሁ በማለት ባለታሪኩ አቶ ዙምራ ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከነዚህ አሉታዊ አስተሣሰቦች ነጻ የወጣ፣ በፍቅርና በእኩልነት የሚያምን እርስበርሱ የሚተሣሰብና የሚረዳዳ፣ በሥራና ሰርቶ በማደግ ብቻ የሚተማመንና ለዘላቂ ሕይወቱ መለወጥ ጠንክሮ ለመሥራት የሚተጋ ሕብረተሰብን ማየት ተመኘሁ በማለት የመጀመሪያ ህልማቸውን በአጭሩ ይተርካሉ።

ይህን ምኞታቸውን እውን ለማድረግና አዲሱን አስተሳሰባቸውን የሚጋራ ሰው ለማግኘትም ቆላ መውረድ፣ ደጋ መውጣት፣ እንዲያም ሲል ከማህበረሰቡ ጋር መጋጨትና መገለል ነበረባቸው:: በወቅቱ እንደአፈንጋጭ አሊያም እንደ ዕብድ ይቆጠሩ ነበር:: ይህ ሁሉ ሲሆን እድሜያቸው ገና አሥራ ሶስት ዓመትን እንኳ አልዘለለም ነበር:: ድካምና ልፋቱ ሳይበግራቸው በዚህ የጨቅላነት ዕድሜያቸው ወሎን፣ጐንደርንና ጐጃምን አካለሉ:: ለአሥራ ሰባት ዓመታት መውጣት መውረዱ ቀጥሎ የኋላ ኋላ ልፋትና ድካማቸው መና ባለመቅረቱ ፎገራ ወረዳ ውስጥ ጥቂት ተከታዮችን ከጐናቸው ማሰለፍ ቻሉ:: እናም ዙምራ የተመኙትና የናፈቁት ብሎም በልጅነት እድሜያቸው ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉለት አስተሣሰብ በ1964 ዓ.ም እውን ሆኖ መተሳሰሪያውን ፍቅር ህይወቱን ሥራ ያደረገ ማህበረሰብ በይፋ ተመሠረተ:: ይህንንም ማህበረሰብ አውራምባ ብለው ሰየሙት::

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. አቶ ዙምራ አውራአምባን እንዲመሠርቱ ያደረጉዋቸው ችግሮች ምንና ምን ናቸው?
2. የአውራአምባ ማህበረሰብ መቼና የት ተመሰረተ?
3. የአውራአምባ የሥራ ባህል ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ተናገሩ::

የአውራምባ ማህበረሰብ አባላት የስራ ባህል፣ የሚመሩበት የአኗኗር ዘይቤና የሚከተሉት ፍልስፍና ከሌላው ሕብረተሰብ በብዙ መልኩ እንዲለዩ ያደርጋቸዋል:: ማህበረሰቡ በአስተሣሰብና በእምነት ፍጹም ለየት ያለ በመሆኑ እምነቱን ፍቅር፣ ሃይማኖቱን ደግሞ ሥራ ያደረገ መሆኑ ብቻ ሣይሆን ይህ ሥራ የሴት ይህኛው ደግሞ የወንድ የሚባል የሥራ ክፍፍልንም ሆነ ልዩነትን አይቀበልም:: ሴቶች በሬዎችን ጠምደው ያርሣሉ፤ ሸማ ይሠራሉ:: በአጠቃላይም በተለምዶ የወንድ ሥራ ተብሎ በሚታወቀው ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ውስጥ ሁሉ በእኩል ይሣተፋሉ፣ ወንዶች እንጀራ ይጋግራሉ፣ ወጥ ይሠራሉ፣ ጥጥ ይፈትላሉ ወዘተ. ብቻ ስራን ሳይንቁና ወደ ሌላ ሳይገፉ በኩራት ይሰሩታል እንጅ ሀፍረት ብሎ ነገር አይስተዋልባቸውም አውራምባዎች::



ሥዕል 1፡ ወንድ እንጀራ ሲጋግር



ሥዕል 2፡ ሴት ስታርስ

ስለሆነም አውራምባዎች ሥራ ያሉትንና ለህይወታቸው ጠቃሚ ነው ብለው ያመኑበትን ሁሉ ተባብረውና ተከባብረው እንዲሁም ተግባብተው ይሠሩታል። የጾታ ልዩነት ሣያግዳቸውና የአካባቢው ህብረተሰብ የተሳሳተ አስተሳሰብ እንቅፋትነት ሳይገታቸው ያቀላጥፉታል። ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ከድህነትና ኋላቀርነት መላቀቅ የሚቻለው በሥራ እንጂ ቁጭ ብሎ ከሰማይ መና እንዲወርድለት በመጸለይ እንዳልሆነ በጽናት ያምናሉ። እናም ኑሮአቸውን ለማሻሻልና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሌት ከቀን ተግተው ይሠራሉ፣ ለለውጥና ለሥራ ማነቆ የሆኑ ኋላቀር አስተሣሰቦችንና ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጽናት ይታገሏቸዋል እንጂ በጭራሽ ለማስታመም አይሞክሩም። ለማደናቀፍ ለሚሞክሩ ስራ ፈቶችና ኋላ ቀሮችም ጊዜና ቦታ መድበው ሀሳባቸውን እንዲያደናቅፉባቸው ዕድል አይሰጧቸውም።

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት በጽሑፍ መልሱ።**

1. የአውራምባ ማህበረሰብ ኑሮን ለማሻሻል ከጸሎት ይልቅ ጠንክሮ መሥራት ያዋጣል ብለው ያምናሉ።
2. በአውራምባ ማህበረሰብ ጾታን መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል የለም።
3. በአውራምባ ማህበረሰብ የጾታ እኩልነት የለም።
4. የአውራምባ ማህበረሰብ ሀይማኖት የአካባቢው ማህበረሰብ የሚከተለው ሀይማኖት ነው።
5. የአውራምባ ማህበረሰብ ለአሁኑ ትውልድ መልካም አርአያ በመሆን ያገለግላል።
6. የአውራምባ ማህበረሰብ መሥራች ህልሙን እውን ለማድረግ አንድ ክፍለ ዘመን ወስዶበታል።

**፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን አማራጭ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የአውራምባ ማህበረሰብ ልዩ መገለጫ የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. እርስ በርስ መሰራረቅ
   - ለ. ውሸት አለመናገር
   - ሐ. እርስ በርስ መበዳደል
   - መ. ያላግባብ መጠቃቀም
2. የአውራምባ ማህበረሰብ መሥራች ማን ነው?
   - ሀ. አቶ ዙምራ
   - ለ. የአቶ ዙምራ እናት
   - ሐ. የአቶ ዙምራ አባት
   - መ. አይታወቅም
3. ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ የአውራምባ ማህበረሰብን የማይገልጸው የቱ ነው?
   - ሀ. ጠንክረው ይሠራሉ፤
   - ለ. እርስ በርስ ይተሳሰባሉ፤
   - ሐ. በፍቅርና በእኩልነት ያምናሉ፤
   - መ. ከአሉታዊ አስተሳሰቦች የጸዱ ናቸው፤
   - ሠ. መልሱ አልተሰጠም

4. የማህበረሰቡን መሥራች አስመልከቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አዲስ አስተሳሰባቸውን የሚጋራቸውን ሰው ለማግኘት ብዙ አልደከሙም፤

   ለ. ለማህበረሰቡ አዲስ የሆነ አስተሳሰብ አልነበራቸውም፤

   ሐ. ለወንዶች አሉታዊ አመለካከት አላቸው፤

   መ. አሁን የያዙትን ሀሳብ ያፈለቁት በልጅነታቸው ካስተዋሏቸው ነገሮች ነው፤

5. የአውራምባ ማህበረሰብን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ተራማጅና ጠቃሚ አስተሳሰብ አላቸው፤

   ለ. ጠንካራ የሥራ ባህል አላቸው፤

   ሐ. ማህበረሰቡ መቼ እንደተመሠረተ በግልጽ አይታወቅም፤

   መ. የመልካም ሥነምግባር ባለቤቶች ናቸው፤

ፎ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

1. የአውራምባ ማህበረሰብ መሥራች ዓለማ ምን ነበር? ዓላማውስ ተሳክቷል ወይ?
2. የማህበረሰቡ መሥራች ከቦታ ቦታ የተንከራተተው በምን ምክንያት ነው?
3. የአውራምባ ማህበረሰብ ባህል ጠቃሚ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
4. የአውራምባ ማህበረሰብ ከሌሎች የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር የሚያጋጨው ነገር ምንድን ነው?
5. አውራምባ የቱሪስቶችን ቀልብ ሊስብ የቻለው በምን ምክንያት ነው?



## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

### የደብዳቤ አጻጻፍ

ደብዳቤ ኢመደበኛ (የግል)ና መደበኛ (የሥራ) ደብዳቤ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል።

ሀ. ኢመደበኛ ደብዳቤ ለጓደኛ የሚጻፍ ደብዳቤን፣ ለግብዣ፣ እንኳን አደረሳችሁ ለማለት፣ ሀዘንን ለመግለጽ፣ ምስጋናን ለመግለጽ የሚጻፉ ደብዳቤዎችን ያካትታል። ይህ የደብዳቤ ዓይነት አምስት ክፍሎች አሉት።

1. ራስጌ፡- የጸሐፊውን አድራሻና ደብዳቤው የተጻፈበትን ቀን የሚያካትት ሲሆን የሚቀመጠውም

   በቀኝ ጠርዝ ከላይ ነው።

   ምሳሌ ፡- ነሐሴ 07፣ 2013 ዓ.ም

2. ሠላምታ፡- የመክፈቻ ሠላምታ ሲሆን ከራስጌው ጥቂት መስመሮችን ዝቅ ብሎ በግራ በኩል

   ይቀመጣል።

   ምሳሌ፡- ውድ እህቴ፣ ውድ ፍቅሬ፣ ውድ ጓደኛዬ ...

3. ሐተታ (ዋና ክፍል)፡- የደብዳቤው በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ ቀላልና ግልጽ በሆነ ነገር ግን ትህትና በተላበሰ ቋንቋ ሊጻፍ ይገባል፡፡

4. መደምደሚያ፡- የደብዳቤው መዝጊያ ቃል ወይም ሀረግ ነው፡፡ ምሳሌ ከሠላምታ ጋር፣ ውድ ጓደኛሽ፣ አፍቃሪሽ...

5. ፊርማ፡- ከመዝጊያ ቃሉ ወይም በታች የሚሠፍረው የጸሐፊው ስም ነው፡፡

## የኢመደበኛ ደብዳቤዎች ቅርጽ

| | |
|---|---|
| ራስጌ | መገናኛ<br>ኃይሌ ገብረ ሥላሴ መንገድ<br>ነሐሴ 07፣ 2013 ዓ.ም |
| ሠላምታ | ውድ እናቴና አባቴ፣ |
| ሐተታ | ..............................................<br>..............................................<br>.............................................. |
| መደምደሚያ | ከአክብሮት ጋር! |
| ፊርማ | ሚሚ |

ለ. መደበኛ ደብዳቤ ደግሞ የሥራ ማመልከቻ፣ ምስክርነት መጠየቂያ፣ ቅሬታ ማቅረቢያ፣ ለጋዜጦች የሚጻፉ ደብዳቤዎችና የሸያጭና ግዢ መጠየቂ ደብዳቤዎችን ያካትታል፡፡ ይህ የደብዳቤ ዓይነት ስድስት ክፍሎች አሉት፡፡

1. ራስጌ፡- የጸሐፊውን አድራሻና ደብዳቤው የተጻፈበትን ቀን የሚያካትት ሲሆን የሚቀመጠውም በቀኝ ጠርዝ ከላይ ነው፡፡ ምሳሌ፡- ነሐሴ 07፣ 2013 ዓ.ም

2. የውስጥ አድራሻ፡- ደብዳቤው የሚላክለት ሰው ወይም ተቋም ስምና አድራሻ

3. ሠላምታ፡- የመክፈቻ ሠላምታ ሲሆን ከራስጌው ጥቂት መስመሮችን ዝቅ ብሎ በግራ በኩል ይቀመጣል፡፡ የሠላምታ ቃሉን ወይም ሐረጉን ተከትሎ ነጠላ ሠረዝ ወይም ሁለት ነጥብ ይቀመጣል፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ ነጠላ ሠረዙም ሆነ ሁለት ነጥቡ ሊነሣ ይችላል፡፡ ስሙ

የሚታወቅ ከሆነ ውድ አቶ/ ወ/ሮ/ ወ/ሪት እገሌ ወይም እገሊት... ስሙ የማይታወቅ ከሆነ ውድ ኃላፊ፣ ወዘተ በማለት ይጻፋል፡፡

4. ሐተታ (ዋና ክፍል)፡- የደብዳቤው በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ ቀላልና ግልጽ በሆነ ነገር ግን ትህትና በተላበሰ ቋንቋ ሊጻፍ ይገባል፡፡

5. መደምደሚያ፡- የደብዳቤው መዝጊያ ቃል ወይም ሀረግ ነው፡፡ ምሳሌ፡- ያንተው/ያንቺው/ የእርስዎ ታማኝ፣...

6. ፊርማ፡- ከመዝጊያ ቃሉ ወይም በታች የሚሠፍረው የጸሐፊው ስም ነው፡፡

## የመደበኛ (የሥራ) ደብዳቤዎች ቅርጽ

| | |
|---|---|
| ራስጌ | መገናኛ<br>ኃይሌ ገብረ ሥላሴ መንገድ<br>ነሐሴ 07፣ 2013 ዓ.ም |
| የውስጥ አድራሻ | ወ/ሮ ሠላም ይበልጣል<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኃላፊ<br>ኑሩ ቅርንጫፍ |
| ሠላምታ | ውድ ወ/ሮ ሠላም ይበልጣል<br>........................................................................ |
| ሐተታ | ........................................................................<br>........................................................................<br>........................................................................ |
| መደምደሚያ | ከሠላምታ ጋር! |
| ፊርማ | መንግሥት አለነ |

## ናሙና የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ

መገናኛ

ኃይሌ ገብረ ሥላሴ መንገድ

ነሐሴ 07፣ 2013 ዓ.ም

ወ/ሮ ሠላም ይበልጣል

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ

ኑሩ ቅርንጫፍ

አዲስ ዓለም


ውድ ወ/ሮ ሠላም ይበልጣል፣

በድርጃታችሁ ማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ነሐሴ 05፣ 2013 ዓ.ም ባወጣችሁት ክፍት የስራ ማስታወቂያ መሠረት ለባንካችሁ የምክትል ሥራ አስኪያጅነት አመልክቻለሁ፡፡ ከማስታወቂያው ላይ በሂሳብ አያያዝ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና ከፍተኛ የሥራ ልምድ ያለው ባለሙያ እየፈለጋችሁ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከተያያዙት የማመልከቻ ሰነዱ እንደምታዩት በሂሳብ አያያዝ የትምህርት መስክ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ ውጤት የተመረቅሁ ሲሆን፣ በተለያዩ የግል ባንኮች የስድስት ዓመታት የስራ ልምድ አለኝ፡፡ በተጨማሪም የኮምፒዩተርና የፒችትሪ ሶፍትዌር ክህሎት አለኝ፡፡ ከሰዎች ጋር ተባብሮና ተግባብቶ የመሥራት እንዲሁም ነገሮችን በቀላሉ የመልመድ ብቃት አለኝ፡፡

የአማርኛ፣ የአፋን ኦሮሞ፣ የአፍ ሶማሌና የእንግሊዝኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፌ እናገራለሁ፡፡ ይህን ሥራ ብትሠጡኝ ትርፋማና ውጤታማ እንደማደርጋችሁ አምናለሁ፡፡ መልሳችሁን እጠብቃለሁ፡፡

የናንተው ታማኝ፣

(መንግሥት አለነ)



፩. ከላይ በቀረበው የግል ደብዳቤ አጻጻፍ ቅርጽ መሠረት በሩቅ ለሚኖር ዘመዳችሁ፣ የቤተሰባችሁ አባል፣ ጓደኛችሁ ወይም ሌላ ግለሰብ  የሚሆን የግል ደብዳቤ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፪. ከላይ በቀረበው የሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ ቅርጽ መሠረት በአንድ ድርጅት ውስጥ ሥራ ለማመልከት የሚሆን የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

### የሰዎችን ህይወት ታሪክ መጻፍ

የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ታሳቢ ሲደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦች፡-

- የትውልድ ቀንና ቦታ፣
- የቤተሰብ መረጃ፣
- የትምህርት መረጃ፣
- ግለሠቡ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት፣
- ግለሰቡ ያሳለፋቸው ዋና ዋና ሁነቶች፣
- በኖረበት ማህበረሰብ ውስጥ ያሳደረው ወይም ማህበረሰቡ ያሳደረበትና የእነዚህ ጉዳዮች ታሪካዊ ፋይዳ ፣ወዘተ ናቸው።

፫. በአካባቢያችሁ ስለሚገኝ/ስለምትገኝ አንድ ጀግና/ኒት ከሰነድና ከሰዎች መረጃዎችን አሰባስባችሁ የህይወት ታሪኩን ወይም ታሪኳን ጻፉ።

፬. የአባታችሁን፣ የእናታችሁን ወይም የአንዱን የቤተሰብ አባል የህይወት ታሪክ ከውልደት ጀምሮ አሁን እስከአለበት ደረጃ የሚያሳይ የህይወት ታሪክ ጻፉ።

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ቀጥሎ "ሰነፍ ደከስራል፤ ሠራተኛ ደከብራል" በሚል ርእስ እንድታደምጡት ከተደረገው ምንባብና "አውራምባ" በሚል ርእስ ከቀረበው ድሁፍ የተወሰዱ ቃላት ተዘርዝረዋል። በምንባቦቹ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍችዎች ግለጹ።

1. ርስት
2. አያሻኝም
3. አገልጋዮች
4. መማገጥ
5. እንደማትነሳቸው
6. የሚበጅ
7. የተሰወረ
8. ማሳ
9. የጨቅላነት
10. ሳይበግራቸው

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

፩. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሠረት በውስጣቸው ያሉትን ምእላዶች ከፋፍሉ፡፡

ምሳሌ፡- ደብተሬን › ደብተር-ኤ-ን

ላክሁት ላክ-ሁ-ት

1. ሀገራችን
2. ውጤታማነት
3. ጀግንነታችንን
4. አሸንፋችሁት
5. በለጸገች

፪. ቀጥሎ የቀረቡትን እስር ምእላዶች በአስጠጊ (ነፃ) ምእላዶች ላይ በመጨመር በምሳሌው መሠረት ቃሎችን ፍጠሩ፡፡

ምሳሌ፡- -ኡ-ት፣ -ኡ ፣ -ኡ-ኝ (አወቁት፣ አወቁ፣ አወቁኝ)

-ነት ፣ -ኦች ፣ ኦች-ን (ሰውነት፣ ሰዎች፣ ሰዎችን...)

-ነት

-ኣም

-ኡ

-ኦች

-ኣችን

-ን

-ኝ

-ሀ

1. አወቅ-
2. ሰው
3. ልጅ
4. ሰርግ
5. ደስታ
6. የዋህ
7. ጎበዝ-

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ሥራ ባህል የተመለከቱ ምንባቦችን አዳማጣጭሁና አንብባችሁ ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን መለየት ችላችኋል። በተሰጧችሁ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሚና ለዋጭ ንግግር አድርጋችኋል። በተጨማሪም በተሰጧችሁ ርእሰ ጉዳዮች በተደረጉ ውይይቶችም ተሳትፋችኋል። ጽሕፈት በሚለው ክፍል ደግሞ የተለያዩ የደብዳቤ አይነቶችን ጽፋችኋል። ደብዳቤ ኢመደበኛ (የግል)ና መደበኛ (የሥራ) ደብዳቤ ተብሎ ይከፈላል። ኢመደበኛ ደብዳቤ ለጓደኛ የሚጻፍ ደብዳቤን፣ ለግብዣ፣ እንኳን አደረሳችሁ ለማለት፣ ሀዘንን ለመግለጽ፣ ምስጋናን ለመግለጽ የሚጻፉ ደብዳቤዎችን ያካትታል። በሌላ በኩል መደበኛ ደብዳቤ የሥራ ማመልከቻ፣ ምስክርነት መጠየቂያ፣ ቅሬታ ማቅረቢያ፣ ለጋዜጦች የሚጻፉ ደብዳቤዎችና የሽያጭና ግዢ መጠየቂ ደብዳቤዎችን ያካትታል። በተጨማሪም በዚህ ክፍል የሰዎችን የህይወት ታሪክ መጻፍ ችላችኋል። የህይወት ታሪክ ሲጻፍ የባለታሪኩ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ የቤተሰብ መረጃ፣ የትምህርት መረጃ፣ ግለሠቡ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት፣ ግለሰቡ ያሳለፋቸው ዋና ዋና ሁነቶች፣ በኖረበት ማህበረሰብ ውስጥ ያሳደረው ወይም ማህበረሰቡ ያሳደረበትና የእነዚህ ጉዳዮች ታሪካዊ ፋይዳ ፤ወዘተ ታሳቢ ሊደረግባቸው ይገባል። በክፍል አምስት ቃላት በሚለው ስር ለቃላት አውዳዊ ፍች ሰጥታችኋል። በመጨረሻም ሰዋስው በሚለው ክፍል በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቅጥያዎችን መለየት ችላችኋል።

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. የአውራባ ማህበረሰብ የሚታወቅበት የሥራ ባህል ምንድን ነው?
2. የህይወት ታሪክ ለመጻፍ ስንነሳ ልናተኩርባቸው የሚገቡ ነጥቦችን ዘርዝሩ።
3. የኢመደበኛና የመደበኛ ደብዳቤ አይነቶችን ልዩነትና አንድነት ተናገሩ።
4. ሰውነታችንን ኃይል <u>ለመንፈግ</u> ከፈለግን ራሳችንን በረሀብ እየቀጣን መሆን የለበትም፤ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበትን ቃል አውዳዊ ፍች ስጡ።
5. “እንደሚወስዷቸው” በሚለው ቃል ውስጥ ያሉ ምዕዶችን ለዩ።

የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በሥራ ባህልና ምርት ላይ የሚያተኩር ጽሑፍን አዳምጬ ፍሬ ሀሳቡን እለያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በሚሰጡኝ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አውድን መሰረት ያደረገ ንግግር አደርጋለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በተመረጡ ይዘቶች ላይ ውይይት አካሂዳለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በሥራ ባህል ላይ የሚያተኩር ምንባብን አንብቤ እረዳለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የተለያዩ የደብዳቤ አይነቶችን እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የሰዎችን ታሪክ መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ለቃላት አውዳዊና ቀጥተኛ ፍች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 8 | በቃል ውስጥ የሚገኙ ምእላዶችን እተነትናለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡ የህይወት ክህሎቶች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የማዳመጥ ቴክኒኮችን በመተግበር በድምጽ የተቀረጸ የህይወት ታሪክ አዳምጣችሁ ጥቅልና ዝርዝር መረጃዎችን ትሰጣላችሁ::
- በምታደምጡት ምንባብ ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ትሰጣላችሁ::
- ማህበራዊ ተራክቦን ተጠቅማችሁ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- የምንባቡን ይዘት ታብራራላችሁ::
- አመዛዛኝ አንቀጾችን ትጽፋላችሁ::
- የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍቺ ታብራራላችሁ::
- የአማርኛ የቃል ክፍሎችን ትለያላችሁ::



## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የህይወት ታሪክ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ

የህይወት ታሪኩን ከማዳመጣችሁ በፊት ሀዲስ አለማየሁ ማን ናቸው? ስለእሳቸው ታሪክና ሥራዎቻቸው የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ በቃል ንገሯቸው::

የተግባር መመሪያ

1. መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን በድምጽ የተቀረጸ የሀዲስ አለማየሁን የህይወት ታሪክ በጥሞና አዳምጡ::
2. በመቀጠል ከታች በድህረ ማዳመጥ ጥያቄ ስር ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 የተዘረዘሩ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በትክክል ለመገንዘብ ከምታዳምጡት ጽሑፍ ማስታወሻ ያዙ::




ሥዕል 3፡ ሀዲስ ዓለማየሁና መጽሐፋቸው

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. የአዳመጣችሁትን ታሪክ መሰረት አድርጋችሁ ጥያቄዎችን በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ሀዲስ አለማየሁ መቼና የት ተወለዱ?
2. የዚህ ታሪክ ባለቤት ከጸሐፊነት ሌላ ሀገራቸውን በምን በምን መስክ አገልግለዋል?
3. ሀዲስ አለማየሁ በአርበኝነት ኢትዮጵያን ያገለገሉት መቼና ከማን ጋር በተደረገ ውጊያ ነው?
4. ባለታሪኩ በዲፕሎማትነት ያገለገሉት የት የት ሀገራት ነው?
5. ሀዲስን በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁ ካደረጓቸው ልቦለዶች መካካል ሁለቱን ጥቀሱ?
6. ባለ ታሪኩ በህዝብ ዘንድ ይበልጥ እንዲታወቁ ያደረጋቸው ሥራቸው የትኛው ሙያቸው ነው?
7. ሀዲስ አለማየሁ በሥነ ጽሑፍ ዘርፍ የተሸለሟቸው ሽልማቶች ምን ምን ናቸው? መቼ ተሸለሙ? ሽልማቶቹንስ ያበረከቱላቸው እነማን ናቸው?

፪. በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በድረ ገጽ የሚቀርቡ የስኬታማ ሰዎች የህይወት ታሪኮችን አዳምጡ፡፡

ሀ. ስኬታማ ስለሆኑባቸው ዘርፎችና ተግባራት ማስታወሻያዙ፡፡

ለ. የያዛችሁትን መረጃ እንደገና አዋቅራችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### የሀኪምና ታካሚ ተግባቦት

፩.ቀጥሎ በሀኪምና በታካሚ መካከል የሚደረግ ምልልስ ቀርቧል:: ለአምስት ለአምስት በመከፋፈል እያንዳንዳችሁ አንዱን ገጸ ባህሪ በመወከል ንግግር አድርጉ::

አቶ ልዑል ታመዋል:: ሰብለ ወደ ጤና ጣቢያ ልታደርሳቸው ነው:: ሶፍያ ደግሞ መርፌ ለመወጋት ወደ ሆስፒታል መሄድ ያስፈልጋታል:: ስለዚህም አብራቸው ልትሄድ ትወስናለች::

| | |
|---|---|
| አቶ ልዑል፡ | ራሴን አሞኛል:: ባለፈው ሳምንት ጉንፋን ይዞኝ ነበር:: ራስ ምታቱ ግን እስካሁን አለቀቀኝም:: ጤንነት አይሰማኝም:: እባክሽ ወደ ጤና ጣቢያ ውሰጂኝ:: |
| ሰብለ፡ | ትምህርት ቤት ልሄድ ነበር :: |
| ሶፍያ፡ | እኔም መርፌ ለመወጋት ወደ ጤና ጣቢያ ልሄድ ነው:: አቶ ልዑልንም እኔ ልወስደው እችላለሁ:: |
| ሰብለ፡ | አይ! ግድ የለም፤ እወስደዋለሁ:: |
| ሶፍያ፡ | አብሬያችሁ ልመጣ እችላለሁ? |
| ሰብለ፡ | እንዴታ! |
| ከጤና ጣቢያ ሲደርሱ አቶ ልዑልን ይዘውት ወደ መመዝገቢያ ክፍሉ ሄዱ:: | |
| ሰብለ፡ | ጤና ይስጥልኝ! አባቴ ታሞብኛልና ሀኪሟ እንዲያዩት እፈልጋለሁ:: |
| መዝገብ ክፍሉ፡ | እሺ! ስማቸውን ማን ልበል? |
| ሰብለ፡ | ልዑል ካሳ |
| ነርስ፡ | እድሜያቸውስ? |
| ሰብለ፡ | አርባ ስድስት:: እባክዎ፣ በጤናው አይደለም:: መጠበቁ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል |
| መዝገብ ክፍሉ፡ | ሀኪሟ እስክትጠራዎ ከማረፊያው ክፍል ውስጥ ትንሽ ይጠብቁ:: ብዙ ጊዜ አይፈጁም፤ ምን አልባት ቢበዛ ከአሥር ደቂቃ በላይ አይሆንም:: |

| | |
|---|---|
| ከአንድ ሰዓት በኋላ መዝገብ ክፍሉ መጥቶ ለአቶ ልዑል ሀኪሟ አሁን ታይዎታለች ይላቸዋል፡፡ | |
| ሀኪም፡ | ጤና ይስጥልኝ! ምን ይሰማዎታል? ትኩሳት አለብዎ? የት ላይ ነው የሚሰማዎት? |
| አቶ ልዑል፡ | ራሴን በኃይል ያመኛል፡፡ ደግሞም ሣል አለብኝ፡፡ በምሥል ጊዜ ጉሮሮዬን ያመኛል፡፡ |
| ሀኪም፡ | ትኩሳትዎን እለካልዎታለሁ፡፡ … እባክዎ አሁን ምርመራ እንዳደርግልዎ እዚህ ላይ ጋደም ይበሉ፡፡ ልብስ ማውለቅ አያስፈልግም፡፡ … እሺ ሕመምዎ ከባድ አይደለም፡፡ መድኃኒት እሰጥዎታለሁ፡፡ አንድ ኪኒን ጠዋት ሲነሡ አንድ ደግሞ ማታ ሲተኙ ይዋጡ፡፡ |
| አቶ ልዑል፡ | እንደገና መመለስ ያስፈልገኛል? |
| ሀኪም፡ | የለም፡፡ ካልዳኑ በቀር መመለስ አያስፈልግም፡፡ |

(ዴቪድ አፕሊያርድ፡፡ 1995፡፡ ከገጽ 188-89 መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የተወሰደ)

፬. በቡድን በቡድን ሆናችሁ በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን ከሚተላለፉና ከምትከታተሏቸው ድራማዎች አንዱን መርጣችሁ በድራማዎቹ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፭. በአካባቢያችሁ ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች (ሠርግ፣ ሞት፣ ድንገተኛ አደጋ፣ ወዘተ) መረጃ ከአንዱ ወደ ሌላው እንዴት እንደሚያስተላልፉ ውይይት አድርጉ፡፡ የተወያያችሁባቸውን ፍሬ ነገሮች ለክፍሉ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት የቃል ዘገባ አቅርቡ፡፡



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## ቴክኖሎጂ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ቴክኖሎጂ ምንድን ነው?
2. በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ምን ምን የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሉ? ስማቸውን ጥቀሱ፡፡

## ቴክኖሎጂ

ይህ አሁን ያለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን በርካታ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየተዋወቁበት ያለ ነው። ከዘመናችን ዋና ዋና ቴክኖሎጂዎች መካከል የባዮቴክኖሎጂ ምህንድስና፣ ስልተ-ቀመርን መሰረት ያደረገው የመረጃ ቴክኖሎጂ እና ሰው ሰራሽ አእምሮ ተጠቃሽ ናቸው።

በ19ኛው ምዕተ ዓመት የዓለም ህዝቦች በስፋት ግብርና ላይ ነበር የተሰማሩት። አሁን ታዳጊ አገሮች ውስጥ ያ ዓይነት ሁኔታ ሲንጸባረቅ ይታያል። በኢኮኖሚ ባደጉት አገሮች ግን በግብርና ላይ የሚሰማራው የሰው ጉልበት በጣም ቀንሷል። ለምሳሌ በ2010 በአሜሪካ በግብርና የተሰማራው የሰው ኃይል ሁለት በመቶ፣ በኢንዱስትሪ ሃያ በመቶ፣ በአገልግሎት ሰባ ስምንት በመቶ ነበር፡፤ ይህ የሚያመለክተው ቴክኖሎጂ የተካው የጉልበት ስራን እንደሆነ ነው።

በሥነሕይወት ምርምር ብዙ ያልታለሙ ተግባራት ተፈጽመዋል። ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ በአንድ አይጥ ጀርባ ላይ በባዮቴክኖሎጂ ምህንድስና ተመስርቶ የሰው ጆሮ እንዲበቅል ተደርጓል። በዚህ መንገድ የሚገኝ ጆሮ ስራው ለተሰናከለ ለሕያው ጆሮ መተኪያ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። በዚህም ሂደት መስማት የተነሳናቸው በቀዶ ጥገና ሰው ሰራሽ ጆሮ ተበርክቶላቸው፣ መስማት ይችሉ ይሆናል የሚል ተስፋ ማንገብ ተችሏል።

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. እስካሁን ካነበባችሁት ውስጥ ስለዘመናችን ቴክኖሎጂ ምን ተረዳችሁ? በቀጣይስ ምን ማወቅ ትፈልጋላችሁ?
2. ቀጥሎ በሚቀርበው የምንባቡ ቀሪ ክፍል ምን ምን ሀሳቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትጠብቃላችሁ?


ቴክኖሎጂ የሰው ልጅ ሌላ ለየት ያለ ተግባርም እንዲፈጽም እያስቻለ ነው። ሕያው አካል ላይ ህይወት አልባ አካል እየተቀጠለ (ሕያው እና ሕያው ያልሆነ እያገናኘ) አዲስ ዓይነት ሕያው አካል መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶች ታይቷል። ይህም ቴክኖሎጂ አዲስ ስም ተሰጥቶታል፤ "ሳይቦርግ" ይባላል።

በዘመናችን አዲስ አይነት ሕያው መሰል ግኝት አለ። ከሕያው አካል ጋር ሕይወት አልባ የሆነ አካል መሰል መሳሪያ (ለምሳሌ እጅ መሰል፣ እግር መሰል) በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች እገዛ፣ ሕይወት-አልባው ቅጥያ (እግር፣ እጅ) ከአንጎል ትዕዛዝ እንዲቀበል እና የተፈለገውን ተግባር እንዲፈጽም ለማድረግ ተችሏል።

ስለዚህ ሳይንሳዊ ግኝት የሚኖረን ግንዛቤ የበለጠ ይዳብርልን ዘንድ ስለሳይቦርግ" ቴክኖሎጂ ውጤት ዳግም እናንሳ። እጆቻቸውን በአደጋ ምክንያት ያጡ፣ ሕይወት-አልባ እጆች ለተቀጠሉላቸው ግለሰቦች እንደነባር እጆች (ክንዶች) ሆነው የሚያገለግሉ አዳዲስ እጆች ለማበርከት ተችሏል። "ጀሲ ሱልቫን" የሚባል አሜሪካዊ እጁን ከትከሻ መለስ በአደጋ ምክንያት ያጣ እና "ክላውድያ ሚሽል" የምትባል አሜሪካዊት እንዲሁ ከክንድ በመለስ እጇን በአደጋ ምክንያት ያጣች፣ እጅ ለእጅ ሲጨባበጡ በመገናኛ ብዙሃን ታይተዋል። ለመጨባበጥ የተጠቀሙባቸው እጆቻቸው ሰው ሰራሽ ሲሆኑ፣ እጆቹ የእንቅስቃሴ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ደግሞ በአንጎል ነው። ይህም ሰው ሰራሽ እጅ እና ነባራዊ አንጎል ግንኙነት ለመመስረት ቻሉ ማለት ነው። ግኝቱ ትልቅ የቴክኖሎጅ እመርታን ያመለክታል።



ሥዕል 4፡ ተፈጥሯዊ አዕምሮ ከሰው ሰራሽ እጅ ጋር መረጃ ሲቀባበል



ሥዕል 5፡ ሮቦት

ሌላኛው የዘመናችን ቴክኖሎጂ ሰው-ሰራሽ አእምሮ ነው፡፡ ለብዙ ዘመን ግለሰቦች ስልተ-ቀመር የሰውን የጭንቅላት (አእምሮ) ተግባር አይተካም፤ የጉልበት ስራን ነው ሊያስተናግድ የሚችለው ብለው ያምኑ ነበር፡፡ ለምሳሌ ሮቦት የሰውን ፊት መለየት (ማን እንደሆነች/ እንደሆነ) አይችልም፤ ያ ችሎታ ለሕፃናት የታደለ (እናት መለያ) ስጦታ እንደሆነ ይወሰድ ነበር፡፡ እንዲሁም የቼዝ ጨዋታን ሊረዳ አይችልም ይባል ነበር፡፡ ሆኖም “አይ ቢ ኤም” የሰራው ሮቦት “ዲፕ ብሉ” የሚባለውን ሮቦት በወርሃ ሐምሌ፣1996 የዓለምን የቼዝ ሻምፒዮን “ጋሪ ካስፖሮቭን” በጥቂት ደቂቃዎች ነበር ያሸነፈው፡፡ እንዲሁም ዋትሰን የሚባል ሌላ በ”አይ ቢ ኤም” የተፈበረከ ሮቦት በቴሌቪዥን አማካኝነት በ2011 በተስተናገደ የጂኦፓርድ ውድድር ነባር የውድድር አሸናፊዎች የነበሩ ሁለት ግለሰቦችን በአንድ ጊዜ ረትቷቸዋል፡፡

(ከሽብሩ ተድላ 2011፡ ከገፅ163-165 መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የተወሰደ)፡፡

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች በጥሞና ከአነባባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን “እውነት”፣ ትክክል ያልሆኑትን “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ስልተ-ቀመር የመረጃ ቴክኖሎጂ የሰዎችን ህይወትን ያቀላል፡፡
2. በሳይቦርግ ቴክኖሎጂ ሰው-ሰራሽ የሰውነት ክፍልን ከአእምሮ ጋር ማገናኘት ተችሏል፡፡
3. ስልተ-ቀመር የሰውን ጭንቅላት (አእምሮ) ወደ መተካት እየተጠጋ ነው፡፡
4. ቴክኖሎጂ የሰውን ልጅ ጉልበት ሊተካ አይችልም፡፡
5. ቴክኖሎጂ የግብርና ውጤታማነትን ይቀንሳል፡፡

**፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡**

1. በባዮቴክኖሎጂ ምህንድስና ምን ምን ሥራዎች ሊሠሩ ይችላሉ?
2. ሳይቦርግ ቴክኖሎጂ ምንድን ነው?
3. የሳይቦርግ ቴክኖሎጂ በሀገራችን ቢስፋፋ በምን መንገድ ሊጠቅመን ይችላል?
4. ስልተ-ቀመር ለምን ይጠቅማል?

**፫. የጽሑፉን ፍሬ ሀሳብ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

## ክፍለ ትምህርት ሰራት፡ ጽሕፈት

### የማወዳደርና የማነፃፀር የአፃፃፍ ስልቶች

ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በመካከላቸው ያሉ ተመሳሳይ ገጽታዎችን መሠረት አድርጎ አግባብነትና ተዛማጅነት ያላቸውን ሀሳቦች በማደራጀት የመግለጽ ዘዴ የማወዳደር ሥልት ይባላል፡፡ በሌላ በኩል ተመሳሳይ ባህሪያት ያላቸውን ሁለት ነገሮች በመካከላቸው ያሉ ልዩነቶችን መሠረት በማድረግ ልዩ ልዩ ተጓዳኝ ሀሳቦችን የማደራጀት፣ የማስፋፋትና የመግለጽ ዘዴ የማነጻጸር ስልት ይባላል፡፡

#### ናሙና አንቀጽ 1.

ቀጥሎ ከደረጀ ገብሬ (1996፣ 66) የተወሰደ በዱሮ ሴቶችና በዘመናዊዎቹ መካከል ያለው የምግብ አዘገጃጀት ልዩነት አስመልክቶ በንጽጽር ቀርቧል፡፡

ዘመናዊ ሴቶች ከአያቶቻቸው በቀለለ ሁኔታ ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡ የጥንቶቹ ወደ እንጨት ለቀማ ሄደው፣ ለቅመውና ሲያስፈልግም ፈልጠው ማገዶ ያቀርባሉ፡፡ የዛሬዎቹ የልጅ ልጆቻቸው ግን የጋዝ ምድጃ ለመለኮስ ክብሪት ይጭራሉ፤ ወይም የኤሌክትሪክ ምድጃ ማብሪያ ማጥፊያ ይጠመዝዛሉ፡፡ የድሮዎቹ እጅግ ተጨንቀውና ተጠብበው፣ በተፈጥሮ ካገኙት እውቀትና ልምድ ዝግጅቱን ያጠናቅቃሉ፤ ያሁኖቹ ግን ልዩ ልዩ የባልትና መጻሕፍት ያነባሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ምግቡ ተመጥኖና ተቀምሞ፣ በየሱቁ ስለሚገኝ በማሸጊያው ላይ የሚገኘውን ማብራሪያና መግለጫ በማንበብ ስለአዘገጃጀቱ መረጃ ያገኛሉ፡፡ የድሮዎቹ አብዛኛውን ለምግብ ዝግጅት ጥሬ ነገር የሚያገኙት ከጓሯቸው ነው፡፡ እንደ ዘመናዊዎቹ ከገበያና ከሱቅ የሚሸምቷቸው ብዙ ነገሮች አልነበሯቸውም፡፡ አንድ ጊዜ የበሰለ ምግብ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ የሚያደርጉ መሳሪያዎችም አልነበሯቸውም፡፡ የአሁኖቹ ሴቶች ለምግብ ማብሰያው እንዲመቹ ሆነው የተዘጋጁ ማዕድ ቤቶች አሏቸው፡፡ ጥሬና የበሰሉ ምግቦች ጣእማቸው ሳይለውጡና ሳይበላሹ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ የሚያደርጉ ማቀዝቀዛዎች የተሟሉላቸው ናቸው፡፡ ምንም እንኳ የድሮዎቹ በጣእሙ እጅ የሚያስቆረጥም ምግብ ያቀርባሉ ቢባልም ለማብሰልና ለማዘጋጀት ከዘመናዊው የበለጠ ጊዜ፣ ልፋትና ድካም ያስፈልጋቸው እንደነበር መገመት አያዳግትም፡፡

#### ናሙና አንቀጽ 2.

ገበሬ አለበት ቦታ ላይ በእግሩ ተደላድሎ የሚቆም ነው ፡፡ ምንም እንኳን የቆመባት መሬት የእርሱ ባትሆንም እላይዋ ላይ መቆሙ ይሰማዋል ፡፡ የመሬት ምንነት ለስሜቱ ይታወቀዋል ፤፤ የፋብሪካ ሠራተኛ ግን እንደ ወፍ ነው ፡፡ እኔ የበቀልኩበት ነው የሚለው የራሱ መሬት የለውም ፡፡ የራሱ ቦታ የለውም ፡፡ ዛሬ እዚህ ቢገኝ ነገ የኸንን የነበረበትን የሥራ ቦታ ለቆ ይሄዳል ፡፡ ሴት እንኳ ከአንድ ቦታ ይዛ አታቆየውም ፡፡ አንድ ነገር ተዛብቶ ሲገኝ ያነን የነበረበትን ቦታ ሲለቅ እርሷም ትቷት ይሄዳል፡፡ የተሻለ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይናውዛል፡፡ ገበሬ ግን ከወዲያ ወዲህ ሳይባክን የኑሮ ሁኔታው የተሻለ እንዲሆንለት እዚያው ባለበት ረግቶ ይጥራል ፡፡

፩. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጋችሁ ቀጥሎ ከቀረቡት ተግባራት መካከል አንዱን በመምረጥ ሥሩ፡

ሀ. በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው አነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ።

ለ. በስልክና በበይነ መረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው ጽሑፍ አዘጋጁ።

ሐ. በኢሜል መልዕክትን መላክና በፖስታ መልዕክትን መላክ አስመልክቶ መረጃዎችን ከድረ ገጾች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

መ. ቴሌ ብርና ሞባይል ባንክ በተሰኙት አገልግሎቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍል ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፩. ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ግልጋሎት ላይ የዋሉ ቃላት ቀርበዋል። ፍቻቸውን ከተለያዩ ድረ ገጾች በመፈለግ ወይም የኮምፒዩተር ባለሙያ በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

1. ስልተ ቀመር (አልጎሪዝም)
2. ሳይቦርግ ቴክኖሎጂ
3. አርቲፊሻል የማሰብ ችሎታ (አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ)

፪. ቀጥሎ በመረጃ ቴክኖሎጂ ግልጋሎት ላይ የዋሉ ቃላት ቀርበዋል። የእነዚህ ቃላትን ፍች ከተለያዩ ድረገጾች በመፈለግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

1. በይነመረብ (ኢንተርኔት)
2. ሃርድዌር
3. ሶፍትዌር

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

### የአማርኛ የቃል ክፍሎች

የአማርኛ ቃላት በስድስት የቃል ክፍሎች ይከፈላሉ:: እነሱም ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድና መስተአምር ናቸው::

ስም፡- አንድ ቃል ስም ወይም የስም ክፍል ነው የሚባለው በቅርጹ /-ኦች/ የሚለውን የብዛት ምዕላድ የሚወስድ ከሆነ፣ በአገባቡም የአረፍተ ነገር ባለቤትና ተሳቢ መሆን የሚችል ከሆነ ነው::

ምሳሌ፡-

| ነጠላ | ብዙ |
|---|---|
| ቤት | ቤቶች |
| ልጅ | ልጆች |

<u>ልጁ</u> መጣ::　　የተሰመረበት ቃል (ስም) የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው::

ልጆች <u>ቤት</u> ሰሩ　　የተሰመረበት ቃል (ስም) የአረፍተ ነገሩ ተሳቢ ነው::

ግስ፡- ማንኛውም በአረፍተ ነገር መድረሻ ላይ ሊገባ የሚችል እንደ /-ሁ/፣ /-ህ/፣ /-ሽ/ ወዘተ ያሉ መደብ አመልካች ምዕላዶችን (የባለቤት አጸፋን) ሊያስከትል የሚችል ቃል ሁሉ በግስ የቃል ክፍል ውስጥ ሊመደብ ይችላል::

ምሳሌ፡-

እኔ ልብሴን <u>ለበስ-ኩ</u>::

አንቺ ደብተር <u>ገዛ-ሽ</u>:: የተሰመረባቸው ቃላት ግሶች ናቸው::

ቅጽል፡- ስምን ቀድሞ በመግባት ስምን የሚገልጽ (የስም ገላጭ) ሲሆን በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ ጎበዝ በሚለው ቃል ምትክ ሊገባ የሚችል ማንኛውም ቃል በቅጽል ውስጥ ሊመደብ ይችላል::

- <u>ጎበዝ</u> ተማሪ
- በጣም <u>ጎበዝ</u> የተሰመረበት ቃል ቅጽል ነው:: በጣም የሚለው ቃል ቀድሞ መግባቱም የቅጽልነቱ ሌላው ማረጋገጫ ነው::

ተውሳከ ግስ፡- ግስን ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ ወዘተ አንጻር የሚገልጹ ሲሆኑ የአማርኛ እውነተኛ ተውሳከ ግሶች በጣም ጥቂት ናቸው::

ለምሳሌ፡-

- o ቶሎ መጣ:: የተሰመረበት ቃል ተውሳከ ግስ ነው::
- o ክፉኛ ወደቀ:: የተሰመረበት ቃል ተውሳከ ግስ ነው::

ነገር ግን ተውሳከ ግሳዊ ተግባር በመስተዋድዳዊ ሀረጎችና በግሶች ሊከናወን ይችላል::

ምሳሌ፡-

- o በድንገት መጣ:: የተሰመረበት ቃል መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው::
- o ፈጥኖ መጣ:: የተሰመረበት ቃል ግስ ነው::

**መስተዋድድ፡-** ማንኛውም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ቃል መስተዋድድ ይባላል::

- o የራሱ የሆነ ተናጥላዊ ፍች የሌለው፣ ነገር ግን ተግባር ያለው፣
- o ምንም ዓይነት ቅጥያ ምዕላድ የማያስከትል፣
- o ለአዳዲስ ቃላት ምሥረታ መሠረት ሊሆን የማይችል፣

ምሳሌ፡- ከ፣ ለ፣ ወደ፣ ማዶ፣ ጋ፣ ወዘተ.

**መስተአምር፡-** መስተአምር የሚባሉት ቃላት የአንድ ነገር ድርጊትና ባህሪ ከሌላ ነገር ድርጊትና ባህሪ ተለይቶ የታወቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚያመላክቱ ቃላት ናቸው::

ምሳሌ፡- ያ፣ ይህች፣ የእኔ፣ ጥቂት፣ ወዘተ.

(ባዬ ይማም:: 2009:: ከገጽ 77-104 ለማስተማሪያ እንዲሆን ተደርጎ የተሻሻለ)

**፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት የቃል ክፍሎቻቸውን ለዩ::**

1. ሰማይ ስም
2. ሸለሉ ________________
3. ኑሮ ________________
4. ህዋ ________________
5. ወፍራም ________________
6. ቆራጥ ________________
7. የኋሊት ________________
8. ጠበቅኩት ________________
9. ጥቂት ________________
10. ጋር ________________

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከአነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ዘመኑ የሳይንስ ነው፤ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. ተውሳከ ግስ ሠ. መስተዋድድ

2. አውሮፕላኑ ቶሞ እኔን የሚጠብቀኝ መሰለኝ! በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. ተውሳከ ግስ ሠ. መስተዋድድ

3. ሙሉ ጨረቃ ከሚመስለው ክብ ፊቷ ላይ ከንበል ያለው ረጅም ጥቁር ጸጉሯን ወደ ላይ መታ አድርጋ፣ "ይህ ዘመቻ በኔ ላይ ነው የመጣው" አለች። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. ተውሳከ ግስ ሠ. መስተዋድድ

4. ገና ነሃ፣ አልጠላሃትም። አሁንም ታፈቅራታለህ፤ አሁንም ትወዳታለህ፤ ይልቅ ሰላምና እፎይታ ካማረህ ስህተቷን በስህተትነቱ ይቅር ብለህ ታረቃት። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. ተውሳከ ግስ ሠ. መስተዋድድ

5. የከሰዓት በኋላ ትምህርቷን ጨርሳ ወደ ቤቷ ስትመለስ ከሱቁ አጠገብ ሁለት ሆነው ቆመዋል። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. ተውሳከ ግስ ሠ. መስተዋድድ

6. እኩለ ቀን እንደመሆኑ ከስድስት ኪሎ እስከ አራት ኪሎ ያለው መንገድ ግርግር በዝቶበታል። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. ተውሳከ ግስ ሠ. መስተዋድድ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የማዳመጥ ቴክኒኮችን በመጠቀም በቴክኖሎጂ የሚደረግ ንግግርን አዳምጣችሁ ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ ችላችኋል:: እንዲሁም ማህበራዊ ተራክቦን መሠረት ያደረገ ንግግር ማድረግ ችላችኋል:: የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቴክኖሎጂዎችን አስመልክቶ የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ ተረድታችኋል:: በመቀጠልም በተለያዩ የቴክኖሎጂ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አነጻጻሪና አወዳዳሪ ጽሑፎችን አዘጋጅታችኋል:: በተጨማሪም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጥቅም ላይ የሚውሉ የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍች አውቃችኋል:: በመጨረሻም የአማርኛ የቃላት ክፍሎችን በዝርዝር ተገንዝባችኋል:: የአማርኛ ቃላት በስድስት የቃል ክፍሎች ይከፈላሉ:: እነሱም ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድና መስተአምር ናቸው::

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሀዲስ አለማየሁ የሚታወቁባቸው የሥነጽሑፍ ስራዎች ምን ምን ናቸው?

2. ቴክኖሎጂ የሚለው ምንባብ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

3. የአወዳዳሪና የአነጻጻሪ ጽሑፍ ምንነትን ግለጹ::

4. የአማርኛ የቃል ክፍሎች ስንት ናቸው? ስማቸውስ?

5. መብራት የሚለው ቃል የቃል ክፍሉ ስም ነው:: እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ::

6. የስልክ ቻርጀር ገዛሁ በሚለው ሀረግ ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፍች ምንድን ነው?

   ሀ. ከስልኩ የሚወጣውን ድምጽ መቀበያ ገመድ

   ለ. ስልኩ የመብራት ኃይል እንዲያገኝ የሚያደርግ ገመድ

   ሐ. የስልኩ የኃይል ማጠራቀሚያ ባትሪ

   መ. የስልኩ የአደጋ መከላከያ ሽፋን

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ጭራሹ በጭራሹ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በህይወት ታሪክ ላይ የሚያተኩር ጽሑፍን አዳምጬ ዝርዝር መረጃዎችን አወጣለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በሚሰጡኝ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ማህበራዊ ተራክቦን መሰረት ያደረገ ንግግር አደርጋለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በቴክኖሎጂ ዙሪያ የቀረበ ምንባብን አንብቤ የጽሑፉን ዋና ሃሳብ እለያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በሚሰጡኝ ርዕሰ ጉዳዮች አመዛዛኝ አንቀጾችን እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍች አብራራለሁ፡፡የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ቃላትን ፍች አብራራለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የአማርኛ የቃል ክፍሎችን እለያለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፡ ሉሲና አደንዛዥ ዕፅ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሠረት ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ::
- የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም  በቅድመ ማዳመጥ ወቅት ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ትሰጣላችሁ::
- ማህበራዊ መስተጋብርን መሠረት ያደረገ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- በሚና-ተኮር ልምምድ ትሳተፋላችሁ::
- ተጨማሪ ጽሑፎችን ታነባላችሁ::
- በሚሰጣችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ  ድርሰት ትጽፋላችሁ::
- ለሚቀርቡላችሁ ቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ::
- የሀረግና የዓረፍተ ነገር መዋቅሮችን ለይታችሁ ታሳያላችሁ::



## ክፍል ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የአደገኛ እፆች መዘዝ



#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከርዕሱ ተነስታችሁ ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ጽሑፍ ይዘት ገምቱ?
2. አደገኛ እጾችን የሚጠቀሙ ሰዎች ምን ምን እጾችን የሚጠቀሙ ይመስላችኋል? ከቀደመ እውቀታችሁ ተነስታችሁ አደገኛ እጾች የሚያስከትሏቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ::

#### የተግባር መመሪያ

መምህራችሁ "የአደገኛ እፆች መዘዝ" በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል::  በምታደምጡበት ጊዜ ማስታወሻ ያዙ:: በትእዛዛቱ መሠረት በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን መልሱ::

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት መልስ ስጡ።**

1. ሱስ ለሚያስይዙ መድኃኒቶችና እጾች በይበልጥ ተጋላጭ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል የቱ ነው?
2. ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችና እጾች ምን ምን ጉዳቶችን ያስከትላሉ? በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
3. ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችና እጾች በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ላይ የሚያስከትሏቸውን መዘዞች በምሳሌዎች በማስደገፍ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።
4. ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችና እጾች ከወንጀል መሥራት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አብራሩ።
5. የአዳመጣችሁትን ጽሑፍ ዋና ሀሳብ በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

### የንግግር አቀራረብ መመሪያ

- የንግግሩን ርዕሰ ጉዳይ መግለጽ፤
- የንግግሩን ዓላማ መለየት፤
- አድማጭን ማወቅ፤
- አስፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ፤
- የንግግሩ መግቢያ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች መዘርዘር፤

*የንግግሩ ሀተታ* - በዚህ ክፍል ርዕሰ ጉዳዩን ለማብራራት የሚያግዙ የተለያዩ ዋና ዋና ሀሳቦችንና ዝርዝር ነጥቦች/መረጃዎች/ይነሳሉ። የእነዚህን ዋና ዋና ሀሳቦች ዝርዝር በቅደም ተከተል ማንሳት፤

*የንግግሩ መደምደሚያ*- በሁለት መንገዶች ሊቀርብ ይችላል።

ሀ. ዋና ዋና ሀሳቦችን ከልሶ በማቅረብ ወይም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ከላይ በሀተታው የቀረቡትን ሀሳቦች ለማጠቃለል የሚያስችሉ የተለያዩ ዓይነት የአጨራረስ ስልቶችን በመጠቀም፤

ለ. የመፍትሄ ሀሳቦች /እርምጃዎችን/ /እንደአስፈላጊነቱ/ በማቅረብ፤

**፩. ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቂ ዝግጅት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።**

1. አልኮል በአንድ ቤተሰብ ወይም ማህበረሰብ ላይ ሊያስከትላቸው የሚችሉ ጉዳቶች ላይ ሰዎችን ጠይቃችሁ ወይም አንብባችሁ በመምጣት ንግግር አድርጉ።
2. እናንተ የወረዳችሁ ወይም የቀበሌያችሁ አስተዳዳሪ የመሆን እድል ቢያጋጥማችሁ ወጣቱን ትውልድ ከሱስ አስያዥ መጠጦችና  አደገኛ እፅዎች እንዴት ትጠብቁታላችሁ? የመፍትሄ ሀሳብ የምትሏቸውን በሙሉ ዘርዝሩ።

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

### ቅድመ ክርክር ዝግጅት

- ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ ወይም መወሰን፤
- ከርሰ ጉዳዩ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ማሰባሰብ (ለምሳሌ፡- ከራስ፣ ከባለሙያዎች፣ ከቤተመጻህፍት፣ የተለያዩ ቦታዎችን በመጎብኘት ወዘተ.)፤
- የተሰበሰበውን መረጃ በአግባቡ ማደራጀት (ለምሳሌ፡- በጊዜ፣ በቦታ፣በድርጊት ቅደም ተከተል ማደራጀት ወዘተ.)፤
- ክርክሩን ከማቅረብ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ፤
- ክርክሩን ከማቅረብ በፊት ሰብዕናንና ሥነ ሥርዓት ማሟላት ለምሳሌ፡-
- አለባበስን - ሥርዓት ያለው ማድረግ፤
- አነጋገርን - ትህትና፣ ትዕግስት፣ ፈገግታ፤
- የግል ንጽህናን መጠበቅ፤
- አክብሮት ማሳየት፤
- ማስታወሻ ማዘጋጀት፤
- በራስ የመተማመን ብቃትን ለማሳደግ በቂ ልምምድ ማድረግ፤
- ፍርሃትንና ጭንቀትን ማስወገድ፤

### የክርክር አቀራረብ

- መድረኩን በሰላምታ መክፈት፤
- የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይን ለአድማጭ ማስተዋወቅ፤
- ለክርክር የተመደበውን ጊዜ ማሳወቅ፤
- የክርክር አጀማመር ሥርዓት መጠበቅ (እያንዳንዱ ተከራካሪ "ክቡር ሊቀመንበር፣ክቡራን ዳኞች እንዲሁም የተከበራችሁ አድማጮች እንዲህ የሚለውን ሀሳብ ደግፌ እንዲህ የሚለውን ሀሳብ ደግሞ ነቅፌ ክርክሬን እጀምራለሁ ብሎ መጀመር አለበት)፤
- ክርክር በሚደረግበት ጊዜ ረጋ ባለ መንፈስ በልበ ሙሉነት የክርክር ነጥቦችን ማቅረብ፤
- ከክርክሩ ጋር የማይስማሙ እንቅስቃሴዎች አለማድረግ (እንቅስቃሴ አለማብዛት ወደ መስኮት ወደ ጣሪያ /ወደ ምድር/ አለማየት አድማጭን መመልከት ይገባል)፤
- በተቃዋሚ ወገን የሚሰጠውን ሀሳብ በትክክል በማዳመጥ የተቃውሞ ሀሳብ ማቅረብ፤
- የተከራካሪ ሀሳብን መንቀፍ እንጂ ግለሰብን ፈጽሞ አለመንቀፍ፤
- ማስታወሻ መያዝ (በማንበብ ምላሽ አለመስጠት ነገር ግን ተቃዋሚ ቡድን ሀሳቡን ሲያቀርብ፤
- ለተሰጠው ሀሳብ ምላሽ ለመስጠት ፍሬሃሳቦችን ለመለየት ብቻ መጠቀም)፤

- የሚቀርበው ሀሳብ ወይም ማስረጃ የአድማጮችን ማንነት ያገናዘበና የተመጠነ ማድረግ፤
- በክርክሩ ሂደት የተሰጠን ወይም የተፈቀደን ጊዜ አክብሮ በአግባቡ መጠቀም፤
- ክርክሩ በሚደረግበት ወቅት ሁለቱም ቡድኖች (ተከራካሪዎች) በጋራ በሚግባቡበት ቋንቋ መጠቀም፤
- ክርክር ከሚደረግበት ርዕሰ ጉዳይ ውጪ የሆነን ሀሳብ ላለማቅረብ ጥንቃቄ ማድረግ፤
- ክርክሩ ሲያበቃ አድማጮች ውጤቱን በትዕግስት እንዲጠብቁ ማሳሰብ፤
- የክርክሩን ውጤት ዳኞች እንዲያቀርቡ መጋበዝ፤
- የክርክሩን መስፈርት መግለጽ፤
- የክርክሩን ውጤት ማሳወቅ፤
- ክርክሩ ሲያበቃ አድማጮችን ማመስገን፤

፬. ከላይ በቀረበው የክርክር መመሪያ መሠረት የቡና ሱስ እንደ ጎጂ ሱስ ሊቆጠር ይችላልን? በሚለው ርዕስ ላይ ተከራከሩበት፡፡



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## ሱስና ማገገሚያ መንገዶቹ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ሱስ ምንድን ነው?
2. ከቀደመ እውቀታችሁ በመነሳት ሰዎች ወደተለያዩ ሱሶች የሚገቡት በምን በምን ምክንያቶች ይመስሏችኋል?
3. ከሰማችሁት በመነሳት የተለያዩ ሱሶች ያሉባቸው ሰዎች ሱስ ለማቆም በሚያደርጉት ጥረት ምን ምን ችግሮች ይገጥሟቸዋል?

ሱስ ማለት በሰዎች ላይ አካላዊና ሥነልቡናዊ የጥገኝነት ስሜት የሚፈጥር ማንኛውም ነገር ነው፡፡ ሰዎች ለመነቃቃት፤ ድብርትን ለማስወገድ፤ ድፍረት ለማግኘት፤ ህመምን ለማስታገስና ከፍተኛ የደስታ ስሜትን ለመጎናጸፍ ብለው የሚያጨሷቸው፤ የሚቅሟቸው በአፍንጫ የሚስቧቸውንና በደምስር የሚወስዷቸውን ነገሮች በሙሉ ያካትታል፡፡ ያለ እነኚህ ዕፆች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴአቸውን ማከናወን ሲሳናቸው ሱስ ወይም የሱሰኝነት ጠባይ እንዳለባቸው ይገለጻል፡፡

ሰዎች ምንም እንኳን ሱስ የሚያሲዙ ነገሮችን በመጀመሪያ አካባቢ በራሳቸው ተነሳሽነት የሚወስዱና የሚጠቀሙ ቢሆንም እየዋለ ሲያድር ግን በሚያስከትለው ጥገኝነት ምክንያት ሱስ የሚያስይዙ ንጥረ ነገሮችንና አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም የግድ እየሆነ ይመጣባቸዋል፡፡ ለረጅም ጊዜ በሱስ መጠመድና ተጋላጭ መሆን የአእምሮ ጉዳት፣ የማስታወስ ችሎታ ማሽቆልቆል፣ ተስፋ መቁረጥ፣ እራስን መቆጣጠር

አለመቻል፣ ሌሎች ተጓዳኝ የአካልና የሥነልቡና ቀውሶችንና ሞትን ሊያስከትል ይችላል።

በሱስና በአደንዛዥ ዕፅ ጥገኝነት አማካኝነት የሚመጡት የጤና እክሎች በሱስ የተጠመዱ ሰዎች ሱሰኝነትን ማቆም እንዳልቻሉ የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህን የጤና እክሎች ለማስወገድ የሚደረገው ህክምና አካልና አእምሮን ከሱስ ከማጽዳት አንጻር ትልቅ ጥረትና ክትትልን ይጠይቃል። ሱስና አደንዛዥ ዕፅ በሰዎች አካል፤ አእምሮና ሥነልቡና ላይ ትልቅ ተጽእኖ ስለሚኖረው የሚሰጠው ዕርዳታና ህክምና በሱስ ምክንያት የተከሰቱ አሉታዊ ተጽእኖዎችን በሙሉ ማከምን ያካተተ መሆን እንዳለበት ይጠበቃል።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ከላይ ካነበባችኋቸው ሁለት አንቀጾች ያገኛችሁት ሀሳብ በቅድመ ንባብ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከሰጣችሁት መልስ ጋር ምን ያህል ይስማማል?
2. ከቀሪው ምንባብ ክፍልስ ምን ትጠብቃላችሁ?




ሥዕል 6፡ በሱስ የተያዘ ሰው

ከዚህ በማስከተል ሱሰኝነትን ለማከም የሚያስችሉ ስልቶችን እንመለከታለን፡፡

### የመድኃኒት ህክምና

በአደንዛዥ ዕፅና ንጥረ ነገሮች ሱስ የተያዙ ሰዎች ሱሰኝነትን እንዲያቆሙና ከሱስ የጸዳ ህይወት እንዲመሩ ለማስቻል ከሚሰጡ ዕርዳታዎች መካከል አንዱ የመድኃኒት ህክምና ሲሆን ይህም የተለያዩ መድኃኒቶችን በመጠቀም በሱስ የተያዙ ሰዎች ሰውነት ውስጥ የተከማቹትን መርዛማ ኬሚካሎችን ማስወገድን ያካትታል። ከሱሰኝነት ጋር በተያያዘ አብዛኛውን ጊዜ የመድኃኒት ህክምናዎች ለብቻቸው ዘላቂ መፍትሄ የመስጠት ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው።

## ሥነ-ልቡናዊ ህክምና

ሰዎች ሱስና ሱሰኝነትን ከሚያሲዙ ድርጊቶች እንዲላቀቁ የሥነ-ልቡና ህክምና ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ከሱስ አካላዊ ጥገኝነት ይልቅ ሥነ-ልቡናዊ ጥገኝነት ስለሚበልጥ ሰዎች በመጀመሪያ ከሱስ ነጻ መውጣት እንደሚችሉ እራሳቸውን ማሳመን ካልቻሉ በሌሎች ህክምናዎችና ዕርዳታዎች ውጤታማ መሆን አይችሉም፡፡ ማንኛውም ለውጥ ከአእምሮ ይጀምራል እንደሚባለው በሱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች በምክር አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ በመታገዝ ከሱስ ለመውጣት ሥነ-ልቡናዊና አእምሮአዊ ዝግጅትና ቁርጠኝነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሰዎች የመንፈስ ጥንካሬ አእምሯቸውን ለማዘዝ የሚያስችል አቅም ሲሰጣቸው በአንጻሩ የአልችልም ባይነትን ሥነ-ልቡና ከተላበሱ አእምሮአቸው ያለመቻልን ስሜት በውስጣቸው ይዘው እንዲዘልቁ ያስገድዳቸዋል፡፡ ስለዚህ ሥነ-ልቡናዊ ህክምና በሱስ የተያዙ ሰዎችን ሥነ-ልቡና በማጠንከር የሱስ ጥገኝነትን ለማስወገድ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

## መጠንን መቀነስ

በሱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሱሰኝነትን ቀስ በቀስ ወይም በሂደት ለመተው እንዲችሉ የሚወስዱትን ሱስ የሚያሲዝ ነገር መጠን መቀነስ ይኖርባቸዋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሱስ ያለባቸው ሰዎች ሱሰኝነትን ለመተው ያስቡና ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ለማቆም ይሞክራሉ፡፡ይህ እርምጃ ምን አልባት ለአንድና ለሁለት ቀን ያገለግል እንደሆን እንጂ ዘለቄታዊ መፍትሄን ማምጣት አይችልም፡፡ ከዚህ ባሻገር ሱሰኝነት በሰውነት አካል ውስጥ በደንብ የተሰራጨ ከሆነ በአንድ ጊዜ ለመተው ማሰብ ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል፡፡ ስለዚህ ሱሰኝነትን በአንድ ጊዜ ወይም በቅጽበት ለመተው ከማሰብ ይልቅ መጠንን እየቀነሱ ለዘለቄታው እስከመተው መድረስን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ሌሎች አማራጮችን መጠቀም

ሱሰኝነት በሰዎች አካላት ውስጥ አንዴ ከተሰራጨ መጠንን በመቀነስ ብቻ በቀላሉ ማስወገድ ስለማይቻል መጠንን በመቀነስ ለመተው በሚደረገው ጥረት ከዚህ ቀደም ሰውነት የተላመደውን መጠን መጠቀም ስለሚፈልግ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ግድ ይላል፡፡ ሱሰኝነትን በአዎንታዊ መልኩ በትክክል የሚተካው ባይኖርም ሱሰኝነትን ለመተው በሚደረገው ጥረት የሚከሰቱትን እንደድብርት፤ ማቅለሽለሽ፤ ትኩረት ማጣት፤ ራስምታት፤ አለመረጋጋት፤ የእንቅልፍ ሰዓት መዛባትና እንቅልፍ ማጣትን ለማስተካከል የማነቃቃት ባህርይ ያላቸውን ትኩስ ነገሮችን መውሰድ፤ማስቲካ ማኘክና እንደየአስፈላጊነቱ በተደጋጋሚ ጸጉርን መታጠብ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## ውጫዊ ተጽእኖዎችን መቋቋም

ሱሰኝነት በተለያዩ ውጫዊ ተጽእኖዎች ሊባባስ ይችላል፡፡ እነዚህን ተጽእኖዎች ለመቋቋም ሱስ ከሚያሲዙ አካባቢዎች መራቅ አንዱ መፍትሄ ሲሆን ይህ የማይቻል ከሆነ ዳግመኛ በሱስ ተጽእኖ ስር ላለመውደቅ አመለካከትን መቀየር ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ሱሰኝነትን ለማስወገድ የሚደረጉ ዕርዳታዎች ሰዎች ከአካላዊና ሥነ-ልቡናዊ የሱስ ጥገኝነት ተላቀው ጤናማ ህይወት እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡በሱስ ለተያዙ ሰዎች በሌሎች የሚደረግላቸውን እንክብካቤና ድጋፍ ማስተናገድ ቀላል ቢሆንም ከሌሎች ዕርዳታ ተላቀው እራሳቸውን ከሱሰኝነት ለማላቀቅ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ትልቅ ተግዳሮት ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም ከሱስ የሚያገግሙ ሰዎች የሱስን አካላዊ፤ ሥነ-ልቡናዊና የውስጥ ስሜት ቁርኝነት ከልብ በመረዳት የሱሰኝነትን ስሜት በአዎንታዊ መልኩ ለመግታት መታገል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሰዎች ሱሰኝነትን ካቆሙ በኋላ የድብርት፤ የንዴትና የብስጭት ስሜት በሚሰማቸው ወቅት ከእነዚህ ስሜቶች ለመውጣት ወደተውት የሱስ ህይወት ለመመለስ ያላቸው ዕድል ከፍተኛ በመሆኑ እነዚህን አጋጣሚዎች በብልሃት ማስተናገድ ይኖርባቸዋል፡፡

(ምንጭ፡ ሀዋሳ ኦንላይን ነሐሴ 13፣ 2013 ዓ.ም ተሻሽሎ ተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆኑትን “እውነት”፣ ስህተት የሆኑትን ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ብዙዎቹ ሱሰኞች ሱስን በአንዴ ማቆም ይቸገራሉ፡፡
2. ሰዎች ወደ ሱስ የሚገቡት በራሳቸው ምክንያት ብቻ ነው፡፡
3. ሥነ ልቦናዊ ህክምና በሱስ ምክንያት የተካማቹ መርዛማ ኬሚካሎችን ያስወግዳል፡፡
4. ከሱስ ለመላቀቅ ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት ማድረግ ይጠይቃል፡፡

**፪. ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን አማራጭ ምረጡ፡፡**

1. ሰዎች ሱስን ለማቆም ሲሞክሩ የማያጋጥማቸው ችግር የትኛው ነው?

    ሀ. የጠንካራነት ስሜት

    ለ. የድብርት ስሜት

    ሐ. ትኩረት አለመስጠት

    መ. የመድከም ስሜት

2. ከሚከተሉት ውስጥ ሱስን አስመልክቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ራስን ለመግዛት ይረዳል፤

    ለ. በሰዎች አካል ላይ ጉዳት ያስከትላል፤

    ሐ. የማስታወስ ችሎታን ይጨምራል፤

    መ. ዝነኛ ያደርጋል፤

3. ከሚከተሉት ውስጥ አንድ በሱስ ውስጥ ያለ ሰው የሱስ ጥገኝነቱን ለማስወገድ ማድረግ የሌለበት የቱ ነው?

    ሀ. ወደ ህክምና ተቋማት በመሄድ የመድሀኒት ህክምና ማግኘት

    ለ. ሥነ ልቦናዊ ህክምና ማግኘት

    ሐ. የሚወስደውን የሱስ መጠን ቀስ በቀስ መቀነስ

    መ. ደጋግሞ መውሰድ

4. ሥነ ልቦናዊ ህክምናን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

    ሀ. በሱስ የተጠቁ ሰዎችን የመንፈስ ጥንካሬ ይጨምራል፤

    ለ. ከሱስ ነጻ ለመውጣት መጀመሪያ ላይ ሊሠጥ (ሊደረግ) ይገባል፤

    ሐ. በክኒን መልክ ይሠጣል፤

5. ሱስን አስመልከቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ተደጋግሞ የሚወሰድ ነው

   ለ. ለአእምሮ ጤና እክል ያጋልጣል

   ሐ. በጭስ መልክ ሊወሰድ ይችላል

   መ. ምግብ ሊሆን ይችላል

### ፫. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትእዛዛቱ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።

1. የምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ምን እንደሆነ በአንድ አንቀጽ ጻፉ?
2. ሱስን መከላከል የሚያስፈልግበትን ምክንያት አብራርታችሁ ጻፉ?
3. በዚህ ምንባብ ውስጥ የጸሐፊው ሀሳብ ምንድን ነው? በዝርዝር አብራሩ።

### ፬. ሱስ በኢትዮጵያ ትምህርትና ምጣኔ ሀብት ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖዎች ከተለያዩ ሰነዶች (ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች፣ ከድረ ገጽና ከመለሳሉት) በማንበብ በማስታወሻዎቻችሁ ላይ ከአሰፈራችሁ በኋላ መረጃዎቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ።



## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

### የድርሰት አጻጻፍ መርሆች

ድርሰት በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚጻፍ ጽሑፍ ሲሆን ይህን ተግባር ለመከወንም በቅድመ ጽሕፈትና በጽሕፈት ሂደት ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ ተግባራት አሉ።

#### ቅድመ ጽሕፈት ተግባራት

- ድርሰቱ የሚጻፍበትን ርእሰ ጉዳይ መምረጥ፡- አንዳንዴ ርዕሰ ጉዳይ ሊሰጥ ስለሚችል ሁልጊዜ ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ የጸሐፊው/ዋ ሥራ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ጸሀፊው/ዋ በሚመቸው/ኣት መንገድ ርዕሱን ማስተካከል ይችላል/ትችላለች።
- የሚጻፍበትን ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መልኩ ርዕሱን ማጥበብ (መወሰን)
- በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ተገቢ መረጃዎችን መሰብሰብ እና በፈርጅ በፈርጃቸው ማደራጀት
- አጠቃላይ የጽሑፉን አካሄድ የሚያሳየውን ዕቅድ (በድርሰቱ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ማጠንጠኛ ነጥቦች የያዘ ንድፍ) ማዘጋጀት
- ጸሐፊው የሚጽፍበትን ዓላማ ማወቅ
- ጽሑፉ ለማን እንደሚዘጋጅ ማወቅ፡- ይህ የቋንቋ አጠቃቀምን ይወስናል።

### የጽሕፈት ተግባራት

- በተዘጋጀው ንድፍ መሠረት ረቂቁን መጻፍ
- በረቂቁ ላይ ማስተካካያና እርማት ማድረግ
- የመጨረሻ ረቂቁን መጻፍ፡- ይህ ሲከናወን አላስፈላጊ ግድፈቶችን ማስተከካል ይገባል።

፭. ቀጥሎ ደግሞ ከላይ በቀረበው የድርሰት አጻጻፍ ማስታወሻ መሠረት አንድ ርዕስ በመምረጥ ድርሰት ጻፉ።

፮. ጫት መቃም በተማሪዎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ አስመልክቶ አጭር ጽሑፍ አዘጋጁ።

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፩. ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በሚገኙበት አውድ መሠረት ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ጻፉ።

1. ለረጅም ጊዜ በሱስ መጠመድና ተጋላጭ መሆን የአእምሮ ጉዳት፣ የማስታወስ ክህሎት ማሽቆልቆል፣ ተስፋመቁረጥ፣ እራስን መቆጣጠር አለመቻልና ሌሎች ተጓዳኝ የአካልና የሥነ-ልቦና ቀውሶችንና ብሎም ሞትን ሊያስከትል ይችላል።
2. ጓደኛዬ ጎንበስ ብሎ ወደ ውስጥ ሲገባ፣ ሹራቡ ወደ ላይ ተሳበና በጀርባው በኩል የወሸቃቸውን ደብተሮች አጋለጣቸው።
3. ደሀውን ከባርነቱ አርነት አወጣች።
4. ምን አልባት የሀገርና የህዝብ ክብርና ኩራት፣ ህላዌና ፈቃድ ጠባቂ፣ አስከባሪና ባላደራ ስለሆነ ይሆናል።
5. በዕቅድ መሥራት አይሆንልንም። ያዘው ጥለፈው ማለት ነው የሚቀናን። እውነቴን ነው … እስኪ የልደታችንን፣ የሠርጋችንን፣ የሞታችንን፣ የኑሯችንንና የአመጋገባችንን ሁኔታ አስበው። ግብታዊነት ይበዛበታል። በግብታዊ አሠራር እንደእኛ አይነት ህዝብ በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም።

፪. ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ ቃላዊ ፍች ስጡ።

1. ተጎናጸፈች
2. አስታገሰ
3. ተሳናት
4. እክሎች
5. ጥገኝነት
6. ማገገም

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### የአረፍተ ነገር ምንነት

አረፍተ ነገር ማለት በሥርዓት ተቀነባብሮ ሙሉ ስሜትን ሊሰጥ የሚችል የቃላት ወይም የሀረጋት ቅንጅት ነው:: በአማርኛ አረፍተ ነገሮች መዋቅር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ እንዲሁም ተሳቢውና ማሰሪያ አንቀጹ በመደብ፣ በቁጥርና በጾታ ስምምነት ሊኖራቸው ግድ ይላል:: ምሳሌ:-

- ስህተት አረፍተ ነገር፡ ተማሪዎቹ ክፍል ውስጥ ገባ::
- የተስተካከለው አረፍተ ነገር፡ ተማሪዎቹ ክፍል ውስጥ ገቡ::
- ስህተት አረፍተ ነገር፡ አስቴር ደብተር ገዙ::
- የተስተካከለው አረፍተ ነገር፡ አስቴር ደብተር ገዛች::
- ስህተት አረፍተ ነገር፡ ልጁ ሆዱን አሞሀል::
- የተስተካከለው አረፍተ ነገር፡ ልጁ ሆዱን አሞታል::

፩. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተት ይታይባቸዋል፤ ስለዚህ በተገቢው ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ጻፏቸው::

1) ተማሪዎች ጎበዝ እንፈልጋለን::
2) ተማሪዎች በጣም ጎበዝ ሊሆን ይችላል::
3) ልቦለድ የፈጠራ ጽሑፍ ናቸው::
4) ሶስቱ ልጆች ወንድም እህት ናቸው::
5) አንተ አባትህ ታከብራለህ?
6) መጽሐፍ ማንበብ ያስደስተኛል አሁን::

፪. ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ግድፈቶችን አርማችሁ እንደገና ጻፉት::

ስለሰውዬው የጫት ሱስ ያወራችልኝ ከነከነኝ:: ለማወቅ ጓጓ፤ ከዚያም በቀጥታ "የጫት ሱስ እንዴት ነው የሚያደርጋት?" አልኩት:: "ሱስ የያዛቸው ሰዎች ጫት ካልቃመ ትኩረት ታጣለች፤ ሁሉም ነገር ይደብራቸዋል በቀላል ነገር ሁሉ ይበሳጫሉ፣ ለምንም ነገር ትዕግስት ያጣሉ:: ጫቱን አግኝተው ካልቃሙ ይሄ ስሜት አይበርድላቸውም:: ስለዚህ እነሱን ለማግኘት ሲሉ ማንኛውንም መስዋዕትነት እከፍላለሁ:: አግኝተው ሲቅሙ ትረጋጋላችሁ፤ ደስተኛ ትሆኛለሽ" አለኝና አንገቱን አቀረቀረ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በማዳመጥና በንግግር ክፍሎች ስር በቀረቡ ጽሑፎች አማካኝነት የሱስንና የአደንዛዥ እጾችን ምንነት፣ መዘዞችና ማገገሚያ መንገዶችን አስመልክቶ ዝርዝር መረጃዎችን አግኝታችኋል። የጽሑፎችን ጭብጦች በመለየት ከጽሑፎቹ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ችላችኋል። እንዲሁም የሱስን አስከፊነት አስመልክቶ በአካባቢያችሁ ባያችሁትና በሰማችሁት መሠረት ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያሳይ ንግግር አድርጋችኋል። በተጨማሪም ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ያገኛችኋቸውን መረጃዎች በማቀናበር ድርሰት መጻፍን በተግባር ተለማምዳችኋል።

በቃላት ክፍል የቃላትን አገባባዊ ፍቺና ቀጥተኛ ፍቺ ሰጥታችኋል። አገባባዊ ፍች ማለት አንድ ቃል በተገኘበት ሃረግ ፣ አርፍተ ነገር ፣ ወይም አውድ ውስጥ የሚያስተላልፈው ይዘት ነው። ቀጥተኛ ፍች ግን ቃሉ ብቻውን ቆሞ ሳለ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ይዘት፣ ሀሳብ፣ ቁስ፣ ድርጊት፣ ወይም ሁነት ነው። በክፍለ ትምህርት ስድስት ደግሞ የአማርኛ አረፍተ ነገሮች ግሱ ከባለቤቱ ጋር በመደብ፣ በቁጥርና በጾታ ሊጣጣሙ እንደሚገባ እውቀት ጨብጣችኋል። ዓረፍተ ነገር ማለት በሥርዓት ተቀነባብሮ ሙሉ ስሜትን ሊሰጥ የሚችል የቃላት ወይም የሀረጋት ቅንጅት ነው። በአማርኛ አረፍተ ነገሮች መዋቅር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ እንዲሁም ተሳቢውና ማሰሪያ አንቀጹ በመደብ፣ በቁጥርና በጾታ ስምምነት ሊኖራቸው ግድ ይላል። በዚህም ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁና ያልጠበቁ አረፍተ ነገሮችን መለየትና ስህተት ያለባቸውን ማስተካከል በተግባር ተለማምዳችኋል።

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሱሰኝነትና የአደንዛዥ እጾችን አስከፊ ገጽታዎቹ ተናገሩ።
2. ሠራተኛው ለጋዜጠኛው የሆዱን <u>ተነፈሰ።</u> የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?

   ሀ) አየር አስወጣ ለ) ንፋስ እንዲያገኝ አደረገው ሐ) ተናገረ መ) ፈነዳ
3. ከሚከተሉት ውስጥ የቅድመ ንግግር ተግባር ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ርዕሰ ጉዳዩን መለየት

   ለ. አድማጭን ማወቅ

   ሐ. ዋና ዋና ሀሳቦችን ማቅረብ

   መ. መረጃ መሰብሰብ
4. የቅድመ ጽሕፈት ተግባራትን ዘርዘሩ።
5. ወጣቶች ከሱሰኝነት መራቅ አለብህ። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚስተዋለው ሰዋስዋዊ ችግር ምንድን ነው? አስተካክላችሁ ተናገሩ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦሥት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የV)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በአደንዛዥ እጽ መዘዝ ላይ የሚያተኩረውን ጽሑፍ አዳምጬ ፍሬ ሀሳቡን ለይቻለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ሱስና የማገገሚያ መንገዶቹን በተመለከተ የቀረበውን ምንባብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በሚሰጡኝ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አውድን መሰረት ያደረጉ ንግግሮችን አደርጋለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በሚና ተኮር ንግግር እሳተፋለሁ፡፡ | | | |
| 5 | በሚሰጠኝ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ድርሰት እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ለቃላት አውዳዊፍች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ሰዋስዋዊ ስርዓትን የጠበቁ ዓረፍተ ነገሮችን መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አራት: ልቦለድ

## የምየሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኂላ፦

- የሚቀርቡ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በማዳመጥ ትወያያላችሁ::
- በልቦለድ ጽሑፎች ዓላማ ላይ ውይይት ታካሂዳላችሁ::
- የቀረቡ ቅንጫቢ ጽሑፎችን ጭብጥ ተንትናችሁ ትጽፋላችሁ::
- በመምህራችሁ የሚሰጧችሁን መጽሐፎች በማንበብ  ጥያቄዎችን ትመለሳላችሁ::
- ልቦለዶችን ታነባላችሁ::
- ሰፊና ጥልቅ የንባብ ብልሃቶችን በመተግበር መረጃዎችን ትፈልጋላችሁ::
- በልቦለድ ውስጥ የቃላትን አጠቃቀም በመጻፍ ታሳያላችሁ::
- የልቦለድን ጭብጥና ዋና ዋና ገጸባህሪያትን ትለያላችሁ::
- ያነበባችሁትን የልቦለድ ታሪክ ትተርካላችሁ::
- የራሳችሁን አጭር ጽሑፍ ታዘጋጃላችሁ::
- ሰዋስዋዊ ግድፈት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ ትጽፋላችሁ::



## ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

አንድ ጽሑፍ በመምህርና በተማሪ ሲነበብ፣ በሬድዮና በካሴት ሲተረክ፣ ንግግር፣ ውይይት፣ ጭውውት፣ ክርክር፣ ቃለ ምልልስ ሲደረግ፣ መልዕክቱን በትክክል፣ በጥሞና በማዳመጥ፣ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ መፃፍና ጥያቄዎችን መመለስ ይገባል:: ስለዚህ የሚከተሉትን የማዳመጥ መመሪያዎች በማንበብ ተግባራዊ አድርጉ::

1. ማዳመጥ፣ከመስማት ይለያል፤ ማዳመጥ መልዕክቱን ሳያዛቡ በአዕምሮ መቅረፅና መመዝገብ መሆኑን መለየት፣
2. ለማዳመጥ ጆሮን ብቻ ሰጥቶ ቁጭ አለማለት፣ጠቅላላ ስሜትን በመሰብሰብ በንቃት ማዳመጥ፣ መከታታል፣
3. ሰዎችን ሲናገሩ አለማቋረጥ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣በሥርዓት ይቅርታ ጠይቆ ምክንያቱን መጠቆም፣
4. ከተናጋሪ ሰው ስህተት የሆነ ሀሳብ ስናዳምጥ፣ ወዲያው ሀሰት ከማለት፣መዝግበን እድል ሲሰጥ በምክንያት ማስረዳት፣
5. ሰዎች ንግግር ሲያደርጉ፣ በንቀት መንፈስ አለማንኳሰስና አለማጥላላት፣
6. ከምናዳምጠው ውስጥ ዋና ዋና ሀሳቦችን በቃላትና በሐረጋት መልክ በማስታወሻ መፃፍ ፣ ወዘተ ያስፈልጋል::

## ሰመመን

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ሰመመን የሚለውን ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ አንብባችሁታል?
2. መጽሐፉን ካነበባችሁት ከታሪኮቹ ውስጥ የመሰጣችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ንገሯቸው::

### የተግባር መመሪያ

መምህራችሁ "ሰመመን" ከሚል ረጅም ልቦለድ የተቀነጨበ ጽሑፍ ያነቡላችኊል:: ማስታወሻ በመያዝ አዳምጡ:: ከዚያም በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን መልሱ::

### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. የአዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ::

1. የአዳመጣችሁትን ቅንጫቢ ጽሑፍ ዋና ጭብጥ በአንድ አንቀጽ ጻፉ::
2. ጥቅምት 14 ለአቤል ፈጽሞ የማትረሳ ቀን የሆነችው ለምንድን ነው? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ::
3. "ከአንዲት ኮረዳ ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጠሙ" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ::
4. የአቤል የዓይን ወዳጅ ማን ትባላለች? ባዳመጣችሁት መሰረት ግለጿት::
5. አቤል የአይን ወዳጁን ያያት የት ቦታ ነው?

፪. ካዳመጣችሁት ቅንጫቢ ተነስታችሁ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ባዳመጣችሁት ቅንጫቢ ጽሑፍ ውስጥ አቤልን የሚያበራታታው ሰው ማን ይባላል?

   ሀ. በድሉ    ለ. እስክንድር    ሐ. መሀመድ    መ. ዋቆ

2. አቤል የስራ ፍላጎቱ ላልቶ፣ የወጣትነት ስሜቱ በርዶ የታየው ለምንድን ነው?

   ሀ. ከመምህሩ ጋር ስለተጣላ    ለ. በትምህርቱ ስለወደቀ
   
   ሐ. ትዕግስትን ስለአፈቀረ    መ. ጓደኛ የሚሆነው ስላጣ

3. አቤል ተወልዶ ያደገው የት ነው?

   ሀ. ጎንደር    ለ. ጅማ    ሐ. ሀረር    መ. ጋምቤላ

## ክፍለ ትምህርት ሁለት: ንግግር

**ከታች በቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ::**

1. አንድ የአጭር ልቦለድ ጽሑፍ በማንበብ ስለጭብጡ በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻችሁ ጋር ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩ::
2. መምህሩ የሚጠቁሟችሁን መጽሐፍ በማንበብ የገጸ ባህርያትን ተግባር በንግግር ግለጹ::
3. የአቤል የልጅነት ትዝታው ከአሁኑ ህይወቱ ጋር በምን ይገናኛል? ካዳመጣችሁት ተነስታችሁ በቡድን በመሆን ተወያዩና ውጤቱን ለክፍል ጉደኞቻችሁ በተራ በተራ ንግግር አድርጉ::

## ክፍለ ትምህርት ሦስት: ንባብ

### ሸክም

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሸክም ምንን ይገልጻል? በጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩ::
2. "ሸክም" የሚለው ምንባብ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል? ገምቱ:: ማን በትክክል እንደገመተ ምንባቡን እያነባባችሁ አረጋግጡ::

### ሸክም



ሥዕል 7 : ከባድ ሸክም የተሸከመ ሰው

### አጭር ልቦለድ

መዝገቡ እንቅልፍ በዐይኑ አልዞር ብሎት ጣሪያ ይቆጥራል::አሁንም አሁንም ይገላበጣል::ከራስጌው ያለውን መብራት አበራና ከጠረጴዛ ላይ ከደረደራቸው መጻሕፍት መካከል፣አንዱን <u>አፈፍ</u> አደረገ:: መጽሐፍ የሚገልጠው <u>በተካልቦ</u> አይደለም:: በእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅጠል ላይ፣እንደኒሻን የተደረደሩትን የቃላት <u>መንጋ</u>፣ በጥሞና ይመረምራል:: <u>አርበ ጠባቧ</u> ክፍል ጅምር ንባብ በዳበሳቸው መጻሕፍት ተሞልታለች:: እንዲያም ሆና ብዙም የከፋ ገጽታ የላትም::

ከእጁ የገባው ድርሳን፣ የሌሊቱን ሸክም የሚያስረሳ መስሎ ስለታየው፤ ለማንበብ ተበራታ።ድርሳኗን የከተበው ጥበበኛ በጨዋታ እያዋዛ፣ ቋጥኝ ቁም ነገርን ማቀበል ያውቅበታል።ጥቃቅን ገጠመኞችን እያስታከከ፣ ንቃትን የሚያበራ ስንቅ እንካችሁ ይላል።ሲጠበብ ድንቅፍቅፍ አያደርገውም። መስመር በመስመር የደረደራቸው ውብ ሽንጣም የምናብ ፍሬዎች፣ እየተስለመለሙ ይጠራሉ። አንዴ ማንበብ ከጀመሩ፣ ለማቆም ሐሞት ይጠይቃል።

የመጽሐፉን ገጽ እንደገለጠ፣ እጅነስቶ የተቀበለው፣ የአንድ ሸክም አልባ ትሁት ሰው ገጠመኝ ነው። ያ ሰው አብርሃም ሊንከን ይባላል።

አብርሀም ሊንከን የአገሪቱ ቁንጮ በሆነ ማግሥት፣ የመክፈቻ ንግግር ለማድረግ ወደሰገነቱ ወጣ፤በዚህ ጊዜ አንድ ግርማ ሞገስ የራቀው አድሃሪ፣ ጉባኤውን በቃጭል ድምጹ ያውከው ጀመረ።

“ስማ፣ በለስ ቀንቶህ መሪ ሆንክ ማለት፣ ድህነትህ ይፋቃል ማለት አይደለም።አባትህ ጫማ ጠጋኝ እንደነበረ፣ ሀገር ያውቃል። እንደውም፤በዚህ ጉባኤ የታደምነው የምክርቤት አባላት የተጫማናቸው ጫማዎች፣ በአንተ አባት እጅ የተበጃጁ ናቸው። እናም፤ ትላንትህን አትርሳ” አለ እያፌዘ።

አብርሀም ሊንከንም ይህንን ጎርባጭ ፌዝ፣ በሚገርም ሁኔታ ወደቁም ነገር እንዲህ ለወጠው፤“ወዳጄ፤ የአባቴን ስራ ስላስታወስከኝ በእጅጉ አመሰግንሃለሁ። እርግጥ ነው፣ አባቴ ጫማ ሰፊ ነበር። ሲበዛ ፈጠራን የታደለ፣ ቢፈጥር ቢፈጥር የማያልቅበት፤ እኔ እንኳን እዚህ ደረጃ ላይ ደርሼ፣የእርሱን አንድ እጅ ችሎታ ልተካከል አልችልም። በእውነት ዛሬ የምክርቤቱ አባላት በሙሉ የተጫሙት ጫማ፣ በአባቴ ታታሪ እጆች የተበጃጁ እንደሆኑ በመበሰሬ፣ ልዩ ስሜት ነው የተሰማኝ፤ ደስታዬን እጥፍ ድርብ ላደረገልኝ ለዚህ ቀናኢ ወዳጄ፣ ደግሜ እጅ እነሳለሁ፤” አለ።

ጠቢቡ ታሪኳን ተንተርሶ ያኖረውን ምልከታ ለመቃረም፤መዝገቡ በመጣደፍ ስሜት ቀጣዩን ገጽ ገለጠና በምናብ ማነብነብ ጀመረ፤

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እናንተ አብርሃም ሊንከንን ብትሆኑ ኖሮ ለሰውዬው ምን ትመልሱለት ነበር?
2. ቀጣዮቹ አንቀጾች ስለምን የሚገልጹ ይመስሏችኋል? ሀሳባችሁን በተራ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ሸክምህን እንደአብርሃም ሊንከን ማቅለልም ሆነ ማክበድ የምትችለው አንተ ብቻ ነህ።” በትላንት ማንነትህ የምትታሰር፣ በነገ ሕልምህ የምትታበይ ከሆነ፣ ሸክምህን ለመቋቋም ጫንቃህን ከወዲሁ ማወፈር ይጠበቅብሃል። ሰዎች ሸክምህን በጎነተሉት ቁጥር፣ ስሜትህ ይጎፈንናል። እላይህ ላይ በየአፍታው የሚቀያየር የአየር ጠባይ፣ እንደመርግ ይጫንሃል። በሰዎች ተግሳጽ ቆፈን ውስጥ ትገባለህ። በሰዎች ጭብጨባ ወበቅ ትቸገራለህ። ምርጫው የአንተ ነው። “ወደ እሳት ወይም ወደ ውሃ።”

መዝገቡ በውድቅት ቀስቅሶ ንቃት የሚያበራ ቁም ነገርን ላቀበለው ጠቢብ እጅ ነሳ:: ምልከታው በውስጡ ያደፈጠውን ጨለማ ሰብእናን፣ እንደ ባትሪ ወለል አድርጎ ሲያሳየው ይሰማዋል:: ጣቱን ከመጽሐፉ መሀል እንደ ወሸቀ፣ የወየበው ግድግዳ ላይ ዓይኑን ማንከራተት ጀመረ:: ጥቂት ጥሞና ውስጥ እንደገባ በሞት ታናሽ ወንድም ተቸነፈ::

በማግሥቱ

በሩ በኃይል ሲደቃ ይሰማዋል::መዝገቡ ድብልቅልቅ ባለስሜት እየተጨናበሰ መዝጊያውን እንደከፈተ፣ የሰማይ ስባሪ የሚያህል መለዮ ለባሽ ሰደፉን እላዩ ላይ አሳረፈበት::

“አንተ ብሎ ተራማጅ፣ ቀጥል!” አለ ጉርድ በርሜል የመሰለው ሌላኛው ባለመለዮ:: የሥጋ ጨርቅ አድርገው ከጭነት መኪናው ላይ አሰጡት::

መለዮ ለበሾቹ እያዳፉ ከአስፈሪው ወህኒ ቤት ለምን እንደጣሉት ቢያወጣ ቢያወርድ፣ ወደአእምሮው ሊመጣለት አልቻለም:: ጊዜው "የአይንህ ቀለም አላማረኝም" ተብሎ የጥይት ራት የሚሆንበት ዘመን ስለሆነ፤ በእርሱ ላይ የደረሰው አልደነቀውም::

በወህኒ ቤቷ የታሸገው እስረኛ ለዐይን ያስፈራል:: የሚያቃስት ድምጽ እዚህም እዚያም ይሰማል::የወህኒ ቤቷ ብቸኛ መጽናኛዎች  በየግድግዳው ላይ የተኳሉ ጥቅሶች ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ “አለም ሰፊ እስር ቤት ናት፤” “እንኳን ከእስር ወደ እስር በደህና መጣችሁ:: “ሽክምህ እንዲቀልህ ከፈለግህ፤ ሞትን እንደ ሶቅራጠስ ቅደመው” የሚሉት ናቸው:: ከጥቅሶቹ መሀል መዝገቡን የሳበው፣ “ሽክምህ እንዲቀልህ ከፈለግህ፤ ሞትን እንደ ሶቅራጠስ ቅደመው” የሚለው ነው:: በእርግጥ ጥቅሶቹ በቁጥር አይገፉም::

ከውድቅት ጀምሮ እንደጥላ እየተከተለው ያለው ሽክም፣ ለራሱ ገርሞታል::እግር የጣለው አውጠንጣኝ ወህኒ ቤቷን እንደተወዳጃት ገመተ:: አስፈሪዋን ወህኒ ቤት በዐይኑ ከእግር እስከ ራሷ ዳበሳት:: አንድ ሪዛም አዛውንት ከጥቅሱ ጋር በአይን ይነጋገራሉ:: የጥቅሱ ቅኔ በብቸኝነት የገባቸው ይመስላሉ:: እንደ መቃብር በሚደብት ፅልመት ውስጥ ፊታቸው እንደፀሐይ ያበራል:: የፊታቸው ጸዳል ሲጋባበት ይሰማዋል፤ በአዛውንቱ ሰበብ እርሱም በተራው ሽክሙን ለመመርመር ተነሳሳ::

“ገላዬን እንደ አውሬ ትቦጫጭቁት ይሆናል:: ነፍሴ ግን ከእናንተ አይን የራቀ ነው:: እኔም እንደ ፈላስፋው ከዚህ ግኡዝ በድኔ ጋር ሰማኒያዬን ቀድጃለሁ::” እንዳለ እንደ መርግ የተጫነው ሽክም ከላዩ ላይ ሲራገፍ ተሰማው::

(ደረጀ ይመር:: 2021:: ሽክም:: ተሻሽሎ የተወሰደ::)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ።**

1. እንቅልፍ በዓይኑ አልዞር ያለው ሰው ዓለሙ ነው።
2. ሽክም አልባ የተባለው ሰው ተግባሩ በትህትና የተሞላ ስለነበር ነው ።
3. ቁምነገር አቀባዩ ጠቢብ ሰው የመጸሐፉ ደራሲ ነው ።
4. አብርሃም ሊንከን ፕሬዚዳንት ከመሆኑ በፊት ድሃ ነበር።
5. የአብርሃም ሊንከን አባት የሞላለት ሃብታም ነጋዴ ነበር።

**፪. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ስጡ።**

1. ቋጥኝ ቁምነገር ማቀበል ያውቅበታል የተባለው ማን ነው?

    ሀ ደራሲው    ለ አንባቢው    ሐ መጽሐፉ    መ መኝታ ክፍሉ

2. ጸሐፊው ሽክምህን እንደ አብርሃም ሊንከን ማቅለልም ሆነ ማክበድ የምትችል አንተ ነህ ሲል ምን ማለቱ ነው?

    ሀ. የገጠመህን ነገር ሁሉ በቀናነት ማየት    ለ. በአለቅነት መንፈስ መኮፈስ

    ሐ. ንግግር አዋቂ መሆን    መ. ለመሪነት መመረጥ

3. መዝገቡ እየተጨናበሰ በሩን ሲከፍት ያጋጠመው ነገር ምንድን ነው?

    ሀ. የሰማይ ስባሪ    ለ. መለዮ ለባሽ    ሐ. ሰደፍ    መ. ጠመንጃ

4. ወዳጄ የአባቴን ስራ ስላስታወስከኝ በእጅጉ አመሰግናለሁ ሲል፣ ንግግሩ የሚያመለክተው

    ሀ. ቁጭትን    ለ. ትህትናን    ሐ. ቂምን    መ. አዋቂነትን

5. ብዙም የከፋ ገጽታ የላትም የተባለችው ማናት?

    ሀ. የመኖሪያ ክፍሉ    ለ. መጽሐፍ መደርደሪያው    ሐ. የትዳር ጓደኛው    መ. የሚያነበው መጽሐፍ

**፫. መምህራችሁ የልቦለድ ንባብ መከታተያ ቋሑፍ አዘጋጅተው ይሰጧችኋል። እናንተም በተሰጣችሁ የንባብ መከታተያ መሰረት መጽሐፉን አንብባችሁ ስትጨርሱ የንባብ መከታተያውን ጥያቄ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ ትመልሳላችሁ ።**

## ክፍለ ትምህርት ሶስት: ጽሕፈት

### መጻፍን ለመማር ጠቃሚ መመሪያ

መጻፍን ለመማር በድግግሞሽ መተግበር ያለባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡- ሀሳብን ማመንጨት፤ ሀሳብን መምረጥ፤ ቢጋር ማዘጋጀት፤ ማርቀቅና መጻፍ ናቸው። የመጻፍ ክሂልን ለማለማመድ ግራፎችን፣ ችግሮችንና መፍትሄዎችን፣ በጅምር የቀሩ ሀሳቦችን፣ ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተ ነገሮችን፣ ያልተስተካከሉ አንቀጾችን፣ ድርሰቶችን፣ መጠቀም ይገባል።

፩. ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ድምር ሀሳብ ለሚሰጡታቸሁ ለንቀጽ ጻፉ፡፡

ትምህርት ቤት እውቀት የሚገበይባት ገበያ ናት ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ፈረስ፣ ጥጥና ጤፍ ለመግዛት ቢፈልግ ፈረስ ለመግዛት ወደ ደጋ፣ ጥጥ ለመግዛት ወደ ቆላ፣ ጤፍ ለመግዛት ወደ ወይና ደጋ በመንከራተት ፈንታ በቀጥታ ወደ ገበያ ሄዶ ሳይንገላታና ብዙ ጊዜ ሳያጠፋ የፈለገውን ሁሉ ከአንድ ቦታ በአንድ ጊዜ ገዝቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ እንዲሁም.....

፪. ከታች የቀረበውን ግጥም እንደገና በማስተካከል ጻፉ፡፡

ህይወቴ

ምሳሌ ፡- ህይወቴ ነሽ ብዬ ነፍሴን ብሰጥሽ

እስትንፋሴ ብዬ ባነጣጥስሽ

ቻው ብለሽኝ ሄድሽ ምን አደረኩሽ

ህይወቴ (እንደገና የተጻፈ)

ህይወቴ ነሽ ብዬ ነፍሴን ብሰጥሽ

እስትንፋሴ ብዬ ብተነፍስሽ

ቻው ብለሽኝ ሄድሽ ምን አደረኩሽ

ህይወቴ (እንደገና ደግሞ የተጻፈ)

ህይወቴ ነሽ ብዬ ነፍሴን ብሰጥሽ

እስትንፋሴ ብዬ ብተነፍስሽ

ደና ሰንብት አልሽኝ መላ አጣሁልሽ፡፡

ህይወቴ (እንደገና ደግማቸሁ ጻፉ)

፫. ከላይ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ዋና ዋና ነጥብ በማስታወሻ መልክ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ለንብቡላቸው፡፡

፬. ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች ለሳጥራችሁ በሁለት ለንቀጽ ጻፉ፡፡

፭. ከላይ በማስታወሻ መልክ በተገለጠላችሁ መሰረት በመረጣችሁት ርዕስ ለጭር ልቦለድ ጻፉና ለመምህራችሁ ለስረክቡ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

፩ ከታች የተዘረዘሩት ቃላት ‘ ሽክም’ በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የወጡ ናቸው:: በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ::

| ተ.ቁ ከምንባቡ የወጡ ቃላት | ተ.ቁ ከምንባቡ የወጡ ቃላት |
|---|---|
| 1. አፈፍ | 6. ቋጥኝ |
| 2. በተካልቦ | 7. ድንቅፍቅፍ |
| 3. መንጋ | 8. መበሰሬ |
| 4. ድርሳን | 9. ቀናኢ |
| 5. የከተበው | 10. በምናብ |

፪. ከታች የተዘረዘሩ ቃላትን በመጠቀም ቃላት በልቦለድ ውስጥ ያላቸውን አጠቃቀም ለማሳየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ::

| ተ.ቁ ከምንባቡ የወጡ ቃላት | ተ.ቁ ከምንባቡ የወጡ ቃላት |
|---|---|
| 1. ይጎፈንናል | 6. ጽልመት |
| 2. ቆፈን | 7. ጸዳል |
| 3. ወበቅ | 8. ጉርድ በርሚል |
| 4. የወየበው | 9. የሰማይ ስባሪ |
| 5. ጥሞና | 10. የተኳላት |

## ክፍለ ትምህርት ስድስት: ሰዋስው

### የአረፍተ ነገር አወቃቀር

አረፍተ ነገር የሚዋቀረው ከሁለት ነገሮች ነው:: እነዚህም ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ናቸው::

ምሳሌ፦ <u>ያ ትልቅ ልጅ አንድ የሰዋስው ደብተር ገዝቷል::</u>

ከላይ በምሳሌነት የተሰጠው አረፍተ ነገር የተዋቀረው፣

ሀ. ያ ትልቅ ልጅ

ለ. አንድ የሰዋስው ደብተር ገዝቷል:: ከሚሉት ሁለት ሀረጎች ነው:: የመጀመሪያው ሀረግ ስማዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግሳዊ ነው::

ይህ ስለ ሰዋስው ደብተር መግዛት ተግባር የተነገረ አረፍተ ነገር ነው:: ገዥው ሰው ማን እንደሆነ፣ የተገዛው ነገር ምን እንደሆነ ተገልጿል:: በሌላ አነጋገር አረፍተ ነገሩ ሙሉ ሀሳብን ይገልጻል:: ስለዚህም ተናጋሪው ሌላ ሀሳብ እስኪመጣለት ድረስ ሊያርፍ ይችላል:: እንደዚህ ያለ የተሟላ ሀሳብ የሚገልጽ መዋቅር አረፍተ ነገር ይባላል::

(ባየ፣ 2002፣ 200)::

፩. ከዚህ በታች የሚገኙት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ አስተካክላችሁ ጻፏቸው፡፡

1. ዓለማየሁና በላይ ከትምህርት ቤት መጣ፡፡
2. አበበ ጎበዝ ተማሪ ናቸው፡፡
3. እኔ ደግሞ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የምፈልገው ከነደበላ ጋር ነኝ፡፡
4. እኔ አንተን እወድሻለሁ፡፡ ከበደም አንተን ትወዳለች፡፡

፪. ከላይ በተራ ቁጥር አንድ የተሰጡትን አረፍተ ነገሮች ካስተካከላችሁ በኋላ ስማዊና ግሳዊ ሀረጋቸውን ከስር በማስመር ለዩ፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ልቦለድ ተምራችኋል፡፡ ከዚህ በኋላ ልቦለድ ስለመጻፍና መለማመድ ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ ልቦለድ መፃፍን፣ በመፃፍ ነው የምትለማመዱት፡፡ ልቦለድ ለመፃፍ ልምምድ ከማድረጋችሁ በፊት ግን ስለ ልቦለድ ምንነት የተወሰኑ ነጥቦች ማንሳት ያስፈልጋል፡፡

ልቦለድ በመባል የሚታወቀው የሥነጽሑፍ ዘርፍ አያሌ ገፅታዎች አሉት፡፡ አይነቶቹም ብዙ ናቸው፡፡ ይህ የሥነጽሑፍ ዘርፍ በእርግጥ ዘመናዊና በዝርው የሚቀርብ የፈጠራ ድርሰት ነው፡፡

ልቦለድ ድርሰት የሚባለው አንድ ደራሲ ከአዕምሮው አንቅቶ፣ ከልቡ አመንጭቶ የሚያቀርበው ድርሰት ነው፡፡ እንዲህ ሲባል የልቦለድ ድርሰት ከሀቅ የራቀ ነው ማለት ግን አይደለም፤ የእውኑ ዓለም ነጸብራቅ ስለሆነ፡፡

ከላይ እንደተጠቀመው የልቦለድ ዓይነቶቹ ብዙ ቢሆኑም ከሚያስተናግዳቸው ይዘትና ቅርፅ አንጻር ለሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም፦ አጭርና ረጅም ልቦለድ ናቸው፡፡ አጭር ልቦለድ በነጠላ ታሪክ፣ በጥቂት ገፀባህሪያት፣ በጠባብ መቼትና በአንድ የትረካ አንጻር መሰረትነት ስለአንድ የህይወት ገፅታ የሚቀርብበት የፈጠራ ጽሑፍ ነው፡፡

በአንጻሩ በረዥም ልቦለድ ውስጥ ልዩ ልዩ የህይወት መልኮች የሚታዩበት፣ ብዙ ገጸባህሪያት፣ ሰፊ መቼት፣ አብይና ንኡስ ታሪክ የሚቀርብበት፣ ከሁለት በላይ ግጭቶች ሊከሰቱ የሚችሉበትና ሌሎች አላባውያንም በስፋት የሚታዩበት የልቦለድ ክፍል ነው፡፡ ልቦለድ ለመፃፍ ስንነሳ ልናተኩርባቸው የሚገቡ ፊሬ ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም፡-1. ታሪክ፣ 2. ገፀባህሪያት፣ 3. መቼት፣ 4. የትረካ አንፃር ፣ 5. ግጭት፣ 6. ትልም ፣7. ጭብጥ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የልቦለድ ገፀባህሪያት የእውኑ አለም ሰዎችን ባህሪ ተላብሰው የመኖሪያ ስፍራና ጊዜ ተበጅቶላቸው ሲንቀሳቀሱና ድርጊት ሲፈጽሙ የሚታዩ፣ ደራሲው በራሱ ምናብ በፈጠረላቸው ታሪክ ውስጥ የሚኖሩ ባለታሪኮች ናቸው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ልቦለድ ከቅርጽ አንጻር በስንት ይከፈላል? ምንና ምን በመባል?
2. የልቦለድ ጭብጥና ታሪክ የሚባሉትን ጽንሰ ሀሳቦች ዘርዝሩ።
3. አጭር ልቦለድ ጻፉና ለጓደኛችሁ አንብቡ።
4. አጭር ልቦለድ ከረዥም ልቦለድ የሚለይባቸውን ባህርያት ዘርዝሩ።
5. ሽክም ከሚለው አጭር ልቦለድ ምን ቁም ነገር ተማራችሁ? ለጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።

### የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል። በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የV)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከላይ በአነበባችሁት ልብወለድ ውስጥ ያሉ ገጸባህሪያትን ተግባራት መዘርዘር እችላለሁ። | | | |
| 2 | በአነበብሁት ልብወለድ ውስጥ የዋናው ገጸባህሪ ተግባር ምን ምን እንደሆነ ማብራራት እችላለሁ። | | | |
| 3 | በአጭር ልብወለድ ውስጥ የሚኖሩ ገጸባህሪያትን በመጠቀም አጭር ልብወለድ መጻፍ እችላለሁ። | | | |
| 4 | ቃላትን በልብወለድ ውስጥ በማስገባት አጠቃቀማቸውን ማሳየት እችላለሁ። | | | |
| 5 | በሚሰጠኝ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ድርሰት እጽፋለሁ። | | | |
| 6 | ለቃላት አውዳዊፍች እሰጣለሁ። | | | |
| 7 | ሰዋስዋዊ ስርዓትን የጠበቁ ዓረፍተ ነገሮችን መጻፍ እችላለሁ። | | | |
| 8 | ጽሑፍን በራስ አባባል ደግሞ መጻፍ እችላለሁ። | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ስምንት: እንግዳ ተቀባይነት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የማድመጥ ስልቶችን ተከትላችሁ ታዳምጣላችሁ::
- ጭብጥ ተኮር ንግግሮችንና የሰላምታ ልውውጦችን በማዳመጥ ትተነትናላችሁ::
- የግል ልምዳችሁን በማወዳደር ትጽፋላችሁ::
- የንግግርን ጠቀሜታ በንግግር ትገመግማላችሁ::
- የታሪኮችን ማጠቃለያ ትጽፋላችሁ::
- የተሰጣችሁን ጽሑፍ ካነበባችሁ በኋላ ጭምቅ ሀሳቡን ትናገራላችሁ::
- ቃላዊ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- ስለእንግዳ ተቀባይነት የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን ታነባላችሁ::
- ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚያሳዩትን የቃል ክፍል ለውጥ ትጽፋላችሁ::



## ክፍለ ትምህርት አንድ: ማዳመጥ

### ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. እቤታችሁ እንግዳ መጥቶ ያውቃል? ምን ምን ተደረገለት?
2. እናንተ ሌላ ሀገር በእንግድነት ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? በሄዳችሁበት ሀገር ምን አጋጠማችሁ?

**የተግባር መመሪያ**

መምህራችሁ 'ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት' በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጽሑፍ ያነቡላችኋል:: ማስታወሻ በመያዝ አዳምጡ:: ከዚያም በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን መልሱ::

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. የአዳመጣችሁትን ቅንጫቢ መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን እውነት፣ ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡**

1. ኢትዮጵያዊነት እንግዳን ማፍቀር፣ ማክበር፣ ስለእውነት መኖር ማለት ነው፡፡
2. ጨለማን የሚያሻግረው አገራዊ ስማችን ኢትዮጵያዊነትና እንግዳ ተቀባይነት ነው፡፡
3. በኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት የታወቁት ሰው ቦጋለ በየነ ይባላሉ፡፡
4. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት እንግዳ ተቀባይ አባት መኖሪያ ቦታ ዳንግላ ነው፡፡
5. የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የሚገኝበት ክልል ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ነው፡፡

**ለ. ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡**

1. ካዳመጣችሁት ጽሑፍ የተረዳችሁትን ዋና ሀሳብ ባጭሩ ተናገሩ፡፡
2. በአዊኛ ቋንቋ አዲናስ ማለት ምን ማለት ነው?
3. በታሪኩ ውስጥ በእንጅባራ ከተማ የሚገኙት ኢትዮጵያዊ አባት ማን ይባላሉ? ምን ምን ተግባራትንስ አከናወኑ ?
4. እንግዳ ተቀባይነትና ኢትዮጵያዊነት እንዴት እንደሚገናኙ በቃል ዘርዝራችሁ አስረዱ፡፡
5. "ከኢትዮጵያዊነት እሴት አንዱ እንግዳ ተቀባይነት ነው" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተወያዩበት፡፡



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

ከታች በቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡

1. በየአካባቢያችሁ እንግዳ ተቀባይነት ምን ምን መገለጫዎች እንዳሉት መረጃ በማሰባሰብና ዝግጅት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡
2. በተነበበላችሁ ጽሑፍ ውስጥ "ኢትዮጵያዊነት ማፍቀር፣ ማክበር፣ ስለእውነት መኖር፣ ለአሸናፊነት መፈጠር፣ በፀጋ መክበር፣ ለሰውና ለነገ መኖር ነው፤" ይላል፡፡ በዚህ ሀሳብ ውስጥ የተሰመረባቸው አገላለጾች ምን ማለት እንደሆኑ ቃላዊ ማብራሪያ ስጡ፡፡

## ክፍል ትምህርት ሦስት: ንባብ

# እንግዳ ተቀባይነት

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ስለእንግዳ ተቀባይነት የሚያወሳ ምንባብ ቀርቦላችኋል:: ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::

1. በቅርቡ እንግዳ በቤታችሁ ተስተናግዶ ያውቃል ?
2. እቤታችሁ እንግዳ ሲመጣ እንዴት ይስተናገዳል?
3. እናንተ እንግዳ ሆናችሁ ሰው ቤት ብትሄዱ እንዴት መስተናገድ ትፈልጋላችሁ?

የኢትዮጵያ ህዝብ እንግዳ ተቀባይ ነው ይባላል:: በእርግጥም እንግዳ ተቀባይ ነው:: እንግዳ ተቀባይነቱ ጥቅም በሚያስገኙለት ቱሪስቶች የተገደበ አይደለም:: ቱሪስትንማ ማን ይጠላል፤ገንዘብ አለውና:: የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነት ግን በችግር ምክንያት ምንም ሳይኖራቸው ከሃገራቸው ወጥተው መጠጊያ የሚፈልጉ ስደተኞችን የሚያካትት ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ በላይ የኤርትራ፣ የደቡብ ሱዳንና፣ የሶማሊያ ስደተኞች በኢትዮጵያ ይገኛሉ::

ይህ እንግዳ ተቀባይነት የቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያ መለያ አይደለም:: ድሮም የነበረ የህዝቡ ባህል ነው:: የጥንቱን እንተወውና ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ያሉትን እናስታውስ:: በአውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1915 ዓ.ም አርመኖች በደረሰባቸዉ ችግር ምክንያት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ሃገራቸውን ለቀው ተሰደው ነበር:: አርመኖች ተሰደው ከሄዱባቸው ሃገራት አንዷም ኢትዮጵያ ነበረች::

ከዚህ በተጨማሪ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ አልጋወራሽ በነበሩበት ወቅት እየሩሳሌምን ለመጎብኘት ሄደው በእዚያ ያገኙዋቸውን አርባ ወጣት አርመናዊያንን ወደኢትዮጵያ አምጥተዋቸዋል:: እነዚህ አርመናዊያን በኢትዮጵያ እንደሃገራቸው መኖር የሚችሉበት እድል አግኝተዋል:: በተለይ አርባ ልጆች በመባል ከሚታወቁ ወጣቶች መካከል የኢትዮጵያ ሙዚቃ እመርታዊ መሻሻል እንዲያመጣ ያደረጉት የነረሲስ ናልባንዲያንን ቤተሰብ ያፈራው የመጀመሪያ ትውልድ ይገኝበታል::

አርባዎቹ ልጆችም ሆኑ ሌሎቹ አርመኖች ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩት እንደስደተኛ ባይተዋር ተደርገው አልነበረም:: እንደኢትዮጵያዊ በፈቀዱት ስራ ላይ ተሰማርተው፣ ሃብት አፍርተው፣ ከኢትዮጵያዊያን ጋር ተዛምደው ነበር:: ትውልደ አርመናዊያኑም እንደሃገራቸው በኖሩባት ኢትዮጵያ በሥነጥበብ፣ በምህንድስና በኢኮኖሚና በሌሎችም የሞያ መስኮች አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ግዙፍ የጫማ ፋብሪካ ዳርማርን፣ ሜክሲኮ አካባቢ የሚገኘውን አረቄ ፋብሪካና አርሾ የህክምና ላብራቶሪን ያቋቋሙትም በትውልድ አርመናዊያን ናቸው:: ትውልደ አርመኖቹ በኢሉአባቦር፣ ወለጋና ሌሎችም የሃገሪቱ አካባቢዎች መሬት ተሰጥቷቸው ኢትዮጵያዊውን መስለው፣ ተጋብተው፣ ወልደው ኖረዋል:: ከአርመናዊያን በተጨማሪ በተለያየ አጋጣሚ ወደኢትዮጵያ የመጡ ግሪኮችና ጣሊያኖችም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚኖሩ ይታወቃል::

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረቡት አንቀጾች የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ቀጥሎ የሚመጣው የምንባቡ ክፍል ስለምን የሚያነሳ ይመስላችኋል? ገምቱ፡፡

ሌላው የኢትዮጵያን እንግዳ ተቀባይነት አጉልቶ የሚያሳየው፣ ከ1930ዎቹ በኋላ በኢኮኖሚያዊ ችግር ምክንያት በብዛት ወደኢትዮጵያ ለፈለሱ የመናዊያን የተደረገው አቀባበል ነው፡፡ የመናዊያን ማንም ከየት መጣህ፣ አባትህ ማነው? ሳይላቸው በመላሃገሪቱ በተመቻቸው ቦታ በንግድስራ ተሰማርተው ኖረዋል፡፡ የችርቻሮ መደብርንና ሻይቤትን ለኢትዮጵያዊያን ያስተዋወቁት እነዚህ የመናዊያን ናቸው፡፡ የችርቻሮ መደብር አረብ ቤት ይባል የነበረው በእነዚህ የመናዊያን ምክንያት ነው፡፡

የኢትዮጵያዊያንን እንግዳ ተቀባይነት ለማሳየት አሁን ያለው ትውልድ የሚያውቀውን ሌላ እውነታ እንመልከት፡፡ ከ1982 ዓ/ም ጀምሮ ሶማሊያ በእርስ በርስ ግጭት መንግስት አልባ ስትሆን፣ በርካታ ሶማሌያዊያን ወደኢትዮጵያ ሸሽተዋል፡፡ ጠረፍ አካባቢ ወዳሉ ከተሞችና የስደተኛ ጣቢያዎች ከገቡት በተጨማሪ፣ በርካቶቹ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው አዲስ አበባ ገብተዋል፡፡ በአዲስ አበባ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቤት ተከራይተው፣ ከህዝቡ ጋር ተቀላቅለው ኖረዋል፤ ይኖራሉም፡፡ በርካቶቹ በ1980ዎቹ መጀመሪያ አዲስ መንደር በነበረው ቦሌ ሚካኤል በመባል በሚታወቀው አካባቢ ነበር የሰፈሩት፡፡ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሱቆች ከፍተው፣ የሚችሉትን ስራ እየሰሩ ከኢትዮጵያዊያኑ ጋር ተቀላቅለው ይኖራሉ ፡፡ እዚያ ሰፈር ተወልደው ያደጉ ልጆች ከሶማሌያዊያኑ ልጆች ጋር አብረው ስላደጉ ሶማሊኛ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ እነዚህን ሶማሌያዊያን ወዳጅ ከማድረግ ውጭ ማንም እንደባይተወር ገፍቷቸው አያውቅም፡፡

ኢትዮጵያ አሁንም ስደተኞችን በመቀበል በዓለም አቀፍ ደረጃ ስማቸው ከሚጠራ አስር ሃገራት አንዷ ነች፡፡ ከላይ ላይ እንደተጠቀሰው በደቡብ ሱዳን በተቀሰቀሰው የእርስ በርስ ግጭት፣ በሶማሊያ ባለው ሰላም እጦትና ድርቅ ባስከተለው የምግብ እጥረት ሳቢያ ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ ያህል ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተዋል፡፡ ኢትዮጵያ እነዚህን ስደተኞች በሃገራቸው እንደሚኖሩ ያህል እንዲሰማቸው በሚያደርግ ሁኔታ ተቀብላ እያስተናገደቻቸው ትገኛለች፡፡



ሥዕል 8፡ የስደተኛ መጠለያ

በደቡብ ሱዳን የእርስ በርስ ግጭት ከተቀሰቀሰ በኋላ ባሉት ዓመታት አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊየን ዜጎቿ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል፡፡አንድ ነጥብ አራት ሚሊየን የሚሆኑት ደግሞ ሃገራቸውን ለቀው ሄደዋል፡፡

እነዚህን ዓለምን ያጥለቀለቁ ስደተኞችን ተቀበሎ በማስተናገድ ከፍተኛውን ድርሻ ከተሸከሙት አስር ሀገራት መካከል አብዛኞቹ መካከለኛና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ከበለጸጉት ሀገራት በአስሩ ተርታ የገባችው ጀርመን ብቻ ነች፡፡ ስደተኞችን ተቀብሎ በማስተናገድ ቀዳሚዋ ሀገር ቱርክ ስትሆን ኢትዮጵያ በአምስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

(ምንጭ፦ ዋልታ ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ኮረፖሬሽን ኢ.ማ 2017) ለመጻሐፉ ዝግጅት እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡**

1. በዓለም ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛ በማስተናገድ አንደኛ ሀገር ቱርክ ናት፡፡
2. አርባ ወጣት አርመናዊያንን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት መሪ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸዉ ፡፡
3. ስደተኛ ከሚያስተናግዱ አስር ሀገራት መካከል አብዛኞቹ መካከለኛና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላችው ሀገራት ናችው፡፡
4. በምንባቡ መሰረት ኢትዮጵያ ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ ስደተኞችን ተቀብላ ታስተናግዳለች፡፡
5. የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነት የተገደበው ጥቅም በሚያስገኘው የቱሪዝም መስክ ላይ ነው፡፡
6. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞች የኤርትራ፣ የደቡብ ሱዳንና የሶማሊያ ብቻ ናቸው፡፡

**፪. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. በአለማችን ብዙ ስደተኞችን ከሚያስተናግዱ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ስንተኛ ናት?
   ሀ .አንደኛ ለ. ሁለተኛ ሐ. አራተኛ መ. አምስተኛ
2. የኢትዮጵያ ሙዚቃ እምርታ እንዲያመጣ ያደረጉ የየት ሀገር ስደተኞች ናቸው?
   ሀ. የሶማሌ ለ. የኤርትራ ሐ. የአርመን መ. የሱዳን
3. በትውልደ አርመናዊያን ያልተቋቋመ ድርጅት የቱ ነው?
   ሀ. የጫማ ፋብሪካ ለ. የአረቄ ፋብሪካ
   ሐ. አርሾ ህክምና ማዕከል መ. ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል
4. ትውልደ አርመኖች ይኖሩበት የነበረው የኢትዮጵያ ክፍል የትኛው ነው?
   ሀ. ኢሉባቦር ለ. ወለጋ ሐ. ጎጃም መ. አዲስ አበባ

5. የመኖች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት መቼ ነው?

   ሀ. ከ1930ዎቹ በፊት ለ. ከ1940ዎቹ በፊት ሐ. ከ1980ዎቹ በፊት መ. ከ1990ዎቹ በፊት

6. ለስደት ምክንያት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱና ዋናው ምንድን ነው?

   ሀ. ጦርነት ለ. ትምህርት ሐ. ጉብኝት መ. ሁሉም

7. በእርስ በእርስ ግጭት የተፈናቀሉ ሶሪያዊያን ቁጥር ወደ____________ይጠጋል።

   ሀ. አስራ ሁለት ሚሊዮን ለ. አስራ አራት ሚሊዮን ሐ. አስር ሚሊዮን መ. አንድ ሚሊዮን

8. የሻይ ቤት ንግድ ለኢትዮጵያዊያን ያስተማሩት ስደተኞች እነ ማን ናቸው?

   ሀ. አርመኖች ለ. የመኖች ሐ. ጣሊያኖች መ. አረቦች

## ፫ የንባብ ስልቶች

**የፍጥነት (የገረፍ ገረፍ) ንባብ:-** ከጽሑፉ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥ በፍጥነት የሚከናወን የንባብ ስልት ነው።

**የአሰሳ ንባብ:-** ከጽሑፉ ውስጥ አንድ ተፈላጊ መረጃ ነጥሎ ለማውጣትና ለይቶ ለመረዳት በፍጥነት የሚከናወን ንባብ ነው።

**ሰፊ ንባብ:-** ብዙ ጊዜ ለመዝናናት ሲባል አንድን ረጅም ጽሑፍ በስፋት ማንበብን ይመለከታል። ንባቡ ሰፊ ስለሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥ እንዲቻል ጊዜ ወስዶ በንቃት ይከናወናል።

**ጥልቅ ንባብ :-** የተወሰኑ ሀሳቦችን በጥልቀት ለመገንዘብ ሲባል በዝርዝርና በጥልቀት የሚከናወን ንባብ ነው። ይህ ዓይነት ንባብ ከፍጥነት ይልቅ ጥልቀትን መሰረት በማድረግ በተለምዷዊ የንባብ ፍጥነት ይከናወናል።

፫. ከላይ የቀረበውንና ስለእንግዳ ተቀባይነት የቀረበውን ምንባብ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ስለእንግዳ አቀባበል ባህላችን በክፍል ውስጥ ሚና ወስዳችሁ (እንግዳና እንግዳ ተቀባይ በመሆን) ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡት።

## ክፍለ ትምህርት ሰባት፡ ጽሕፈት

፩. ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ሰውና ሀገር ከተፈጠሩበት ዘመን ወይም ጊዜ ጀምሮ የእንግዳ ተቀባይነት ስሜት ነበር ለማለት እንደፍራለን፡፡ ሥለዚህ እናንተም በአካባቢያችሁ ስለሚካሄደው የእንግዳ አቀባበል ነዋሪዎችን በመጠየቅና በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

2. ስለሀገር ስለእንግዳ አቀባበል ባህላችን የሚያወራ ሁለት አንቀጽ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

3. ስለእንግዳ ተቀባይነት የሚሰማችሁን ነገር በአጭሩ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

፪. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቀሙባቸሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

እንደሆነ፣ ስለዚህ፣ ቢሆንም፣ ይሁን እንጂ፣ በመሆኑም፣ ምክንያቱም

፫. ርዕስ መምረጥ፣ ቢጋር መንደፍ፣ ማርቀቅ፣ መጻፍ፣ ማደት፣ እንደገና መጻፍ፣ የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርእስ አንቀጽ ጻፉ፡፡

፬. ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም በጥንቃቄ አንብቡና የግጥሙን ጭብጥና ጸሐፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰል አንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ፡፡

“እዚያ ዘመድ አለ፣
ሁሉም የናት ልጅ ነው፣
ሁሉም ያባት ልጅ ነው፣
ጠላትም አንዳንዴ ይመጣል መቃብር፣
ባላጋራም ቸር ነው “ያገር ልጅ” ሲቸገር፡፡

(መሐመድ ነስሩ፡፡ 2015፡፡ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፩. ከዚህ በታች በቀረበው አንቀጽ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ አሥር ዋና ዋና ቃላት ናቸው የምትሏቸውን ለቅማችሁ አውጡና መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ጻፉ።

የኢትዮጵያን የመከራ ቀንበር የሚሸከም፣ ጨለማን የሚያሻግር አገራዊ ስማችን ኢትዮጵያዊነት ነው። በኢትዮጵያዊነት ውስጥ ከላይ የዘረዘርናቸው ማንነቶች ጎልተው ይታያሉ። ኢትዮጵያዊነት አመፀኛን ያሸንፋል፣ መከራን ያሳልፋል፣ የተደፋን አንገት ያቃናል፣ ህብር ነው። የተሠሩ አኩሪ ታሪኮች ሁሉ መነሻቸው ኢትዮጵያዊነት ነው።

፪. የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

1. ቋንቋ
2. ቧንቧ
3. መጓንጕ
4. ቋት
5. ቋሚ
6. ሟች
7. ጧፍ
8. ቋንጣ
9. ቋንጃ
10. ፏፏቴ
11. ቧጋች
12. እሷ
13. ቀሚሷ
14. ጓደኛ
15. ጧሪ
16. አጓት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### የሀረግ አመሰራረት

ሀረግ ከቃላት የሚመሰረትና ከቃል ሰፋ የሚል የመዋቅር ዓይነት ነው። የሚመሰረተውም የቋንቋው የቃል ክፍሎች መሰረት አድርጎ ነው። የቃል ክፍሎች ደግሞ ስም፣ ቅጽል፣ ግስ፣ ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድና መስተዓምር ናቸው።

ስለዚህ ከነዚህ የቃል ክፍሎች ሀረጋት ጥገኛ ወይም ነጻ ሆነው ሊመሰረቱ ይችላሉ። ምሳሌ፦ "ወደ ውጭ ሀገር ስለሄደ" ግሳዊ ሀረግ (ጥገኛ ዓረፍተ ነገር) ነው።

"ወንድሟ ወደ ውጭ ሀገር ስለሄደ"ጥገኛ ዓረፍተ ነገር ነው። "ወንድሟ ወደ ውጭ ሀገር ስለሄደ አዘነች።" ዓረፍተ ነገር ነው።"አስቴር ወንድሟ ወደ ውጭ ሀገር ስለሄደ አዘነች።"ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ይመሰረታል። በዚህ ሁኔታ ከቃል ክፍሎች ሀረጋት ሲመሰረቱ ከሀረጋት ደግሞ ዓረፍተ ነገሮች ነጻና ጥገኝ ሆነው ሊዋቀሩ ይችላሉ።

በሚከተሉት ጥገኛ ዓረፍተ ነገሮች ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ልጁ እንደሄደ፣ ቁርሱን ስለበላ፣ ጓደኛዬ ድንገት ከመጣ፣ ልብሱ አለመጠን የሰፋ፣

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአዳምጦና የአንብቦ መረዳት ስልቶች ማዳመጥንና ማንበብን ለማስተማር ውለዋል፡፡ በተሰጧችሁ ርእሰ ጉዳዮች ላይም ሰፋ ያለ ውይይትና ንግግር በማድረግ ስለእንግዳ አቀባበል ባህላችን ተምራችኋል፡፡ በተጨማሪም በተሰጧችሁ ርእሰ ጉዳዮች ስለእንግዳ ተቀባይነት የራሳችሁን ሀሳብና እውቀት ለሌሎች በማጋራት ተሳትፋችኋል፡፡ ጽሕፈት በሚለው ክፍል ደግሞ መጻፍን ለመማር ደጋግሞ መጻፍ አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ የተሰጣችሁንና አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አንቀጽ የመጻፍ ተግባር አከናውናችኋል፡፡ በክፍል አምስት ደግሞ ቃላት በሚለው ስር ከቀረበው አንቀጽ ውስጥ ለአንቀጹ ዋና የሚባሉትን ቃላት በመምረጥ መዝገበቃላዊ ፍች መስጠትን ተለማምዳችኋል፡፡ በዚህም የቃላት ፍች ከመዝገበ ቃላት ውጭ በአውድም እንደሚገኝ ተምራችኋል፡፡ አውዳዊ ፍች ማለት ከመዝገበ ቃላዊ ፍች ውጭ ቃላት በመገኛ ቦታቸው የሚኖራቸው አገባባዊ ፍች ማለት እንደሆነ ተምራችኋል፡፡ በመጨረሻም ሰዋስው በሚለው ክፍል ስለሀረግ ዓይነቶችና አመሰራረት የተማራችሁ ሲሆን ሀረግ ማለት ደግሞ ያልተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ የሰዋስው ክፍል ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. እንግዳ ተቀባይነት እንዴትና በምን ይግለጻል?
2. ከላይ ከተዘረዘሩት የንባብ ስልቶች የትኛውን ትጠቀማላችሁ?
3. ረዥም ንባብ ለማከናወን የምንጠቀመው የንብብ ዓይነት የቱ ነው? ለምን? ማብራሪያ ጻፉ፡፡
4. አንድን ጽሑፍ አሳጥሮ በራስ አባባል መጻፍ ያለውን ፋይዳ አስረዱ፡፡
5. ቃላት ሀረጋትን ለመመስረት እንደሚረዱ ሁሉ ሀረጋትም ለአረፍተ ነገር ምስረታ ያገለግላሉ ሲባል ምን ማለት ነው በዝርዝር ጻፉ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከላይ ባነበብሁት ስለእንግዳ ተቀባይነት በቀረበው ጽሑፍ የቀረቡ ተግባራትን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | እንግዳ ተቀባይነት ኢትዮጵያዊ እሴት መሆኑን መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የሀረግ አመሰራረትን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ከአንቀጽ ውስጥ መሰረታዊ የሚባሉ ቃላትን መለየት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የታሪኮችን ማጠቃለያ መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ስለ ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት በቃል ንግግር ማድረግ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚኖራቸውን የቃል ክፍል ለውጥ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት፡ ባህላዊ ክንውኖች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- አጠቃላይ እውነታዎችን አዳምጣችሁ ትወያያላችሁ።
- እያዳመጣችሁ ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን ታወጣላችሁ።
- በመረጃዎቹ ላይ ሀሰባችሁን ትገልጻላችሁ።
- አዳምጣችሁ ለጥያቄዎች ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- በሚሰጧችሁ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ።
- በርስ በርስ ንግግር ትሳተፋላችሁ።
- በመማሪያ መጽሐፋቸው ያሉ ማስታወሻዎችን አንብባችሁ ትመዝናላችሁ።
- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተሟላ አንቀጽ ትጽፋላችሁ።
- በተጨባጭ ርእሰ ጉዳች ላይ ትጽፋላችሁ።
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ትለያላችሁ።
- ተመሳሳይ ቃላትን ታዛምዳላችሁ።
- ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ።



## ክፍል ትምህርት አንድ፡- ማዳመጥ

### የዘመን አቆጣጠር

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ንገሩ።
2. በየአካባቢያችሁ የሚገኙ የዘመን አቆጣጠሮችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።
3. ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለ ዘመን አቆጣጠር ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ግምታችሁን በደብተራችሁ አስፍሩና ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ምን ያህል ትክክል እንደነበረና እንዳልነበረ አረጋግጡ።
4. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት "የዘመን አቆጣጠር" ከሚለው ጽሑፍ የተወሰዱ ናቸው። ስለ ፍችያቸው የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

   ሀ. ዓውድ ለ. መከንዳት ሐ. ባህረ ሐሳብ

የተግባር መመሪያ

መምህራችሁ "የዘመን አቆጣጠር" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ማስታወሻ በመያዝ አዳምጡ፡፡ ከዚያም በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ ክፍል የቀረቡ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በአዳመጣችሁት መሠረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ህዝቦች በተለያየ መንገድ ዘመንን ለመለካት ሞክረዋል፡፡
2. ዘመን መጀመሪያም መጨረሻም የለውም፡፡
3. ዘመንን ለመለካት የተፈጥሮ ክስተቶች ጉልህ ሚና ነበራቸው፡፡
4. ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ዘዴን ያገኘችው በ13ኛው ምእተ አመት ነው፡፡
5. አቡ ሻክር የተባለው ሊቅ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡
6. የዘመን ቆጠራ መፈጠር ራሳችንን ከተፈጥሮ ጋር እንድናስማማ አግዞናል፡፡

ለ. በአዳመጣችሁት መሠረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሶቻችሁን ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

1. የዘመን አቆጣጠር በኢትዮጵያ ምን የሚል ስያሜ አለው?
2. ኢትዮጵያዊያን የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር መጀመሪያ እንደነበራቸው የሚያሳዩ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
3. የዘመን ቆጠራ ባህል (ትውፊት) ነው የሚባለው ለምንድን ነው?
4. በጽሑፉ ውስጥ "ጌቶቻችን" ተብለው የተጠቀሱት ምኖች ናቸው?
5. የዘመን ቆጠራ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?
6. ዘመንን መለካት ለምን አስፈለገ?
7. ካዳመጣችሁት ጽሑፍ ይዘት በመነሳት ጨረቃን የተከተለ የዓመት በዓልና የዘመን አቆጣጠርን አብራሩ፡፡
8. እኛ ኢትዮጵያዊያን የባህረ ሀሳብ አቆጣጠርን ለሁለተኛ (ሦስተኛ ጊዜ) ያገኘነው መቼ ነው?



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

፩. በየአካባቢያችሁ ያሉ የስም አወጣጥ ሥርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አካፍሉ፡፡

፪. በየአካባቢያችሁ የሰርግ ሂደት ምን እንደሚመስል መረጃ ሰብስቡና በቡድን በመሆን ገለጻ አቅርቡ፡፡

፫. በየአካባቢያችሁ ያሉ የባህላዊ መድኃኒት ጥበብ ማስተላለፍና ምሥጢራዊነት በሕዝብ ዘንድ ያለው ይሁንታ እንዴት ነው? ተወያዩበት፡፡

፬. በቡድን በቡድን በመሆን በየአካባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊ መድኃኒቶችን ለማዘጋጀትና ለመስጠት የሚመረጡትን የተለያዩ፤ ወራት፣ ዕለታት (ቀናት)፣ ጊዜያት፣ እንዲሁም ለግብዓትነት የሚውሉ ነገሮችን አስመልክቶ መረጃዎችን ከተለያዩ ሰነዶችና የአካባቢው ነዋሪዎች በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ፡፡



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## ሀገረሰባዊ የሕክምና ጥበብ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. በጥንድ በጥንድ በመሆን የተለያዩ ህመሞችን (ለምሳሌ፡- የሆድ ቁርጠትን፣ ምችን፣ ጉንፋንን፣ ወዘተ) ለማከም በቤታችሁ ወስጥ የምትጠቀሟቸውን ባህላዊ መድኃኒቶች ዘርዝሩ፡፡ በመድኃኒቶቹም ፈዋሽነት ላይ ያላችሁን ሀሳብ በቃል ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡
2. ከርዕሱ ተነስታችሁ ቀጣዩ ምንባብ ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ሀሳባችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ የአጠቃላይ ዕውቀትና ተግባር ድምር ውጤት የሆነ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊ ጠንቆችንና ተውሳኮችን ለመከላከልና ለማስወገድ እንዲሁም ለመመርመር የሚተገበር ሙያ ነው፡፡ በዕውቀትና በእምነት ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ዕፀዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድናትና፣ የመሳሰሉትን በተወሰነ የቅመማ ሒደት አዘጋጅቶ በሽታን ለማከም፣ ለመከላከልና ጤናን ለመጠበቅ የሚደረግ ክንውን ተብሎም ሊገለጽ ይችላል፡፡ መንፈሳዊ በሆነ መንገድ የሚካሄድ ሕክምናም ከባህላዊ ይመደባል፡፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከመስፋፋቱ አስቀድሞ ለዘመናት ሲተገበር የቆየ፣ ከሰው ልጅ ንቃተ ህሊና፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የዘመናት ጥበብ፣ ልምድ፣ ተሞክሮና ዕውቀት ውጤት ነው፡፡

የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና የተለየ ጥበብን እንደሚፈልግ ባለሙያዎች ይናገራሉ::በተፈጥሮና በሳይንስ መካከል ያለውን ሚዛናዊነት የማስጠበቅ ባህሪ እዳለውም የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማማሉ:: አንድ የባህል ሐኪም ለታማሚው ፈውስ ለመስጠት የታማሚውን አካላዊ፣ አዕምሯዊና መንፈሳዊ ሁኔታ በጥልቀት ማጤን ይጠበቅበታል:: ይህም የተለየ ጥበብንና ተሰጥኦን የሚጠይቅና ለተመረጡ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ፀጋ ተደርጎ ይታሰባል::

በባህላዊ ሕክምና መድኃኒቱ ከሚቆረጥበት ዕለትና ጊዜ ጀምሮ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች አሉ:: መድኃኒቱን ለመቁረጥ ከመውጣት አስቀድሞ መደረግ ያለባቸው የተለያዩ ጥንቃቄዎችም አሉ:: ለምሳሌ የባህል ሐኪሙ/ሟ መድኃኒት ለመቁረጥ ከቤቱ መውጣት ያለበት/ባት በቀን በተወሰኑና ሰው በማይበዛባቸው ሰዓታት ሊሆን ይችላል:: መድኃኒት ለመቁረጥ በአካልም ሆነ በአዕምሮ ንፁህ መሆን ግድ የሚሆንበት ጊዜ አለ:: በአዕምሮ ተንኮል እያሰላሰሉ መድኃኒት መቁረጥና ለታማሚው መስጠት ዋጋ የለውም ተብሎ ይታሰባል:: ለዚህም በተቻለው ሁሉ ተንኮል አለማሰብ ተገቢ ይሆናል:: መድኃኒቱ ከመቆረጡና ከተቆረጠ በኋላ ከሐይማኖታዊ መጻሕፍት ውስጥ የተወሰኑ አንቀጾችን መድገም ወይም መቅራት ሊያስፈልግ ይችላል::

አንዳንድ በምሽት ሲቆረጡ ዕርኩስ መንፈስ የማስያዝ ባህሪ ያላቸው ዕፀዋት አሉ ተብሎ ስለሚታሰብ አብዛኞቹ የባህል ሐኪሞች መድኃኒት መቆረጥ ያለበት በቀን እንደሆነ ይስማማሉ:: በጾም በዓላት ዕለት የማይቆረጡ የመድኃኒት ዕፆች አሉ::

በዚህ መልኩ መድኃኒቱ ከተቆረጠ በኋላ ሕክምናውን ለመስጠት ከታማሚው ጋር ቤተሰባዊ ግንኙት መፍጠር ሊያስፈልግ ይችላል:: ሕክምናው ከተደረገለት በኋላ መድኃኒቱ እስኪያሽረው ድረስ ከማድረግ መቆጠብ የሚገባው አንዳንድ ነገሮችም የሚኖሩበት ጊዜ አለ::

**? የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ተማሪዎች ንባባችሁን ቆም በማድረግ ከላይ ባነበባችኋቸው አንቀጾች ውስጥ ያገኛችኋቸውን ነጥቦች ለመምህራችሁ ተናገሩ::
2. በሚቀጥሉት የምንባቡ አንቀጾች ውስጥ ሊነሱ ይችላሉ የምትሏቸውን ሀሳቦችም ለመምህራችሁ ተናገሩ::

የባህል ሕክምና በአፋዊና አንዳንዴ በጽሑፍ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ባህላዊና መንፈሳዊ ይዘት ያለው ክዋኔ ነው። እንደዘመናዊ ሕክምና ማንኛውም ሰው በመማርና በማጥናት ሕክምናውን መስጠት አይችልም። ለበሽታው የሚዘጋጁ ቅመማዎች ምስጢራዊና ዕውቀቱም ለተመረጡ ሰዎች ብቻ የሚተላለፍ ነው። አንድ ባህላዊ ሐኪም ዕውቀቱ እንዲሰጠው የተለየ ነገር ሊኖረው ይገባል። አካላዊ፣ አዕምሯዊ መንፈሳዊ ስሜቶችን የሚመረምሩ ዓይኖች ሊኖረው ይገባል። ለዚህም ነው ባህላዊ ሕክምና ከጥበብ የሚቆጠረው።

የተለያዩ ዕፃች የዕፀዋት ቀንበጥ፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ ሥር፣ ግንድ የእንስሳት ተዋፆዎችና የተለያዩ ማዕድናት ለባህላዊ ሕክምና ግብዓት ናቸው። ጤናአዳም፣ ነጭሽንኩር፣ ዝንጅብል፣ ዳማከሴ፣ ኮሶ፣ ሬት፣ ሎሚ የመሳሰሉት አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በባህላዊ መንገድ ራሱን ለማከም ከሚጠቀምባቸው መካከል በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። እርኩስ መንፈስን እንደሚያርቅ ስለሚታመንበት ብዙዎች ጤናአዳምን በየበረንዳቸው ሲተክሉ ይታያል። ጉንፋን የያዛቸው አንዳንዶችም ወደዘመናዊ ሕክምና መስጫ ከመሄድ ይልቅ በዳማከሴ መታጠብን፣ መጠጣትና መተሻሸት ይመርጣሉ።




ሥዕል 9፡ ባህላዊ መድኃኒት እየቀመመ ያለ ሰው

ዘመናዊ ሕክምና እስኪጀመር ድረስ ፈውስ የሚገኘውም በባህላዊ ሕክምና ነበር።ትልቅ በጀት ተይዞለት በቂ ጥናት በሚደረግበት በዘመናዊ ሕክምና የተሻለ ሕክምና ማግኘት እንደሚቻል ብዙዎች ያምናሉ። ይሁንና በአፍሪካና በእስያ የሚገኙ 80 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች የባህላዊ ሕክምና ተጠቃሚ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ። አንዳንድ ጥናቶች ደግሞ አራት ቢሊዮን የሚሆነው የዓለም ሕዝብ የባህላዊ ሕክምና ተጠቃሚ መሆኑን ሲገልጹ፣ በኢትዮጵያም ዘመናዊ ሕክምና ከተጀመረ 100 ዓመት አልሞላውም።ከዛ በፊት ሰዎች ሲታመሙ የሚታከሙት በባህላዊ ሕክምና ነበር። ይሁንና ተገቢው ትኩረት ስላልተሰጠውና ጥናት ስላልተደረገበት የሚጠበቅበትን ያህል ማደግ አልቻለም። ይህንን በደንብ ጥናት አድርገንበት መድኃኒቶችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ በፋብሪካ ደረጃ ማምረት የሚቻልበት አቅም መፈጠር ነበረበት።

ኢትዮጵያ ብዙ መንፈሳዊ ተአምራት የሚሠራበት አገር ስለሆነች ሰዎች ጤናቸውን ለመመለስ በየሃይማኖታቸው የሚያደርጉት ድርጊት ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በሌላው ዓለም እንዲህ ያሉ ነገሮች በደንብ ጥናት ይደረግባቸዋል፡፡ እኛ ጋ ያሉትን ዝም ብሎ ከመግፋት የራሳቸው የተለየ ቀመር ያላቸው እንደሆነ በማጥናትና በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይገባል፡፡

(ሻሂዳ ሁሴን፡፡ 2009 ዓ.ም፡፡ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. ምንባቡ በሀገራችን የባህላዊ ህክምና ተገቢ ትኩረት ይፈልጋል የሚል አንድምታ አለው፡፡
2. ለባህላዊ መድኃኒት ግብዓት የሚሆኑ እጸች አቆራረጥ ጊዜና ወቅትን መሠረት ያደርጋል፡፡
3. የባህላዊ ህክምና ጥበብ የሚተላለፈው ቃላዊ በሆነ መንገድ ብቻ ነው፡፡
4. እምነትን መሠረት ያደረገ መንፈሳዊ ህክምና ባህላዊ ህክምና ነው፡፡
5. ማንኛውም ሰው የባህላዊ ህክምና መስጠት ይችላል፡፡
6. በሀገራችን ባህላዊ ህክምና በስፋት ጥቅም ላይ አይውልም፡፡

ለ. የሚከተሉትን ተግባራት በትእዛዛቱ መሠረት ፈጽሙ፡፡

1. የጽሑፉ ዋና ጭብጥ ምን እንደሆነ በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡
2. የጸሐፊው ዓላማ ምንድን ነው? በቃል ግለጹ፡፡
3. ባህላዊ ህክምና በኢትዮጵያ የተጀመረው መቼ ነው? ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
4. በምንባቡ ውስጥ የቀረበው የባህል ህክምና የመድኃኒት እጽዋት አቆራረጥ በእናንተ አካባቢ ካለው ለመድኃኒት የሚውሉ እጽዋቶች አቆራረጥ ጋር ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት በጽሑፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
5. በቡድን ቡድን በመሆን በምንባቡ ውስጥ በተገለጹት ለባህላዊ ህክምና በሚውሉ እጽዋት እና በእናንተ አካባቢ ለባህላዊ ህክምና ጥቅም ላይ በሚውሉት እጽዋት መካከል ያሉ ተመሳስሎና ልዮነቶችን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
6. "ሀገረሰባዊ ህክምና ከሰው ልጅ ንቃተ ህሊና፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና ጋር የተቆራኘ ነው " የሚለውን ሀሳብ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስራት፡ ጽሕፈት

ቀጥሎ ከቀረቡት ርእስ ጉዳዮች መካከል አንዱን መርጣችሁ በትእዛዛቱ መሠረት ጻፉ::

፩. በየአካባቢያችሁ ያሉ የተለያዩ የዘመን አቆጣጠር ባህሎችን አስመልክቶ ከሽማግሌዎች በመጠየቅና መጻሕፍትን በማንበብ አንቀጽ ጻፉ::

፪. የየአካባቢያችሁን ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ::

፫. የየአካባቢያችሁን የጋብቻ አይነቶች የሚገልጽ ጽሑፍ አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ::

፬. በቡድን በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ባህላዊ ጋብቻ ሲከናወን የሚደረጉ ነገሮችን መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ ሙሉ ሂደቱን የሚገልጽ ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

## ክፍለ ትምህርት ስምንት፡ ቃላት

፩. ቀጥሎ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ በጉልህ የተጻፉ ቃላት አሉ:: የእነዚህን ቃላት አገባባዊ ፍቺ ከታች በ “ለ” ምድብ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች ትክክለኛውን አዛምዱ::

ምግብን በጋራ መመገብ አንዱና ትልቁ የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት አካል ነው:: በአመጋገባችን ሥርዓት ካሉና ለዓለም ልናስተምር ከምንችላቸው **ድንቅ** ነገሮች አንዱ አብሮ መብላት ነው:: አብሮ መብላት፣ **ማዕድን** ከቤተሰብ ወይም ከሌላ ሰው ጋር ሆኖ **መቋደስ** ማለት ነው:: አብሮ በመብላት ውስጥ ያለው ትልቁ **መርህ** ምግብን መጋራት ነው:: አብሮ መብላት ምግብን ከአንድ መሶብ ላይ በጋራ ከመመገብ የዘለለ ነው:: አብሮ መብላት ብዙ **ትሩፋቶች** አሉት::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ድንቅ | ሀ. ጥቅም |
| 2. ማዕድ | ለ. ምግብ |
| 3. መቋደስ | ሐ. ምሳ |
| 4. መርህ | መ. መመሪያ |
| 5. ትሩፋት | ሠ. መካፈል |
| | ረ. መመገብ |
| | ሸ. ግሩም |
| | ቀ. ጥቂት |

፫. ቀጥሎ በተዘረዘሩት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በምሳሌው መሠረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቾቻቸውን ስጡ፡፡

1. ምሳሌ፡- የሆዱን ተነፈሰ፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡- አየር አስወጣ

   ፍካሬያዊ ፍች፡- ተናገረ

2. እሷ አርፋለች፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡- ---------------

   ፍካሬያዊ ፍች፡-------------------

3. ወንበር ላይ ወጣች፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡- -----------------

   ፍካሬያዊ ፍች፡--------------------

4. እሷ ተፋችው፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡--------------------

   ፍካሬያዊ ፍች፡--------------------

5. ጎጆ መሠረተ፡፡

   እማሬያዊ ፍች፡--------------------

   ፍካሬያዊ ፍች፡--------------------

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች

ነጠላ አረፍተ ነገር አንድ ግስ ብቻ ያለው ሲሆን ውስብስብ አረፍተ ነገር ሲባል ደግሞ በአረፍተ ነገሩ ወስጥ ከአንድ በላይ ግሶችን የያዘ አረፍተ ነገር ማለት ነው፡፡ ምሳሌ፡-

- ማርታ መጽሐፍ ገዛች፡፡
- ማርታ መጽሐፍ ሰጠችኝ፡፡

  ከላይ ያሉትን ተራ አረፍተ ነገሮች በሚከተለው መንገድ በውስብስብ አረፍተ ነገሮች መግለጽ ይቻላል፡፡

- ማርታ የገዛችውን መጽሐፍ ሰጠችኝ፡፡
- ማርታ መጽሐፍ ገዝታ ሰጠችኝ፡፡

፩. ከላይ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡላችሁን ነጠላ አረፍተነገሮች እያጣመራችሁ ወደ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ቀይሯቸው፡፡

1ሀ. አብሮ መብላት የደስታ ምንጭ ነው

1ለ. የእርቅ ምልክት ነው፡፡

1.______________________________________________________________________

2ሀ. ወንድሜ ጎበዝ ጋዜጠኛ ነው፡፡

2ለ. ወንድሜ አንጋፋ ደራሲ ነው፡፡

2. ______________________________________________________________________

3ሀ. በእጅ መመገብ ባህላችን ነው፡፡

3ለ. በእጅ መመገብ እንኮራበታለን፡፡

3. ______________________________________________________________________

፪. ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ተካተው ቀርበዋል፡፡ አንቀጹን ካነበባችሁ በኋላ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ስለኢትዮጵያ አመጋገብ ሲወሳ አብሮ መነሳት ያለበት ነገር ቢኖር ማፈርና መግደርደር ነው፡፡ ኢትዮጵያዊያን ከሰው ፊት ስንመገብ እናፍራለን፡፡ ይህ ደግሞ "ማካፈል ሲገባኝ ብቻዬን በመብላቴ ማፈር ይገባኛል" ከሚል መንፈስ የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ መግደርደርና ይሉኝታ በአመጋገባችን ውስጥ እንደወግ የወሰድናቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ይሉኝታ ስግብግብነትን ለመከላከል በውስጣችን ያለ የጥበቃ ኃይል ነው፡፡ ይሉኝታ የሰውነት ትርፍ ክብደትን በማስተካከሉ በኩል የራሱን ሚና ሳይጫወት አይቀርም፡፡

፫. አምስት የራሳችሁን ውስብስብ አረፍተነገሮች መስርቱና ክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ ባህላዊ ክንዉኖችን ተመልክታችኋል። በመጀመሪያው ክፍል የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ባህል አስመልክቶ አዳምጣችችሁ ዝርዝርና ጥቅል መረጃዎችን መያዝ ችላችኋል። በክፍል ሁለት እንደስም አወጣጥ፣ የጋብቻ ስርዐትና ባህላዊ መድኃኒቶች ባሉ ባህላዊ ልምምዶች ላይ ቃላዊ ተግባቦት (በግል ንግግር፣ ውይይትና ጭውውት) ማድረግ ችላችኋል። በክፍል ሦሥት ደግሞ የሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብን አስፈላጊነት፣ በግብዓትነት የሚውሉ እጽዋቶች፣ ተላልፎት ትኩረት አስመልክቶ አንብባችሁ ተረድታችኋል። በክፍል አራት የተለያዩ ባህላዊ ክንውኖችን አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብ ድርሰት ጽፋችኋል። በክፍል አምስት ቃል በሚለው ክፍል ደግሞ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችዎች መስጠት ችላችኋል። በመጨረሻው ክፍል  ማለትም ሰዋስው በሚለው ስር የነጠላና የውስብስብ አረፍተ ነገርን ምንነት ተገንዝባችኋል። የተለያዩ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን በማጣመር ወደ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች መቀየር፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ችላችኋል። ነጠላ አረፍተ ነገር አንድ ግስ ብቻ ያለው ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ሲባል ደግሞ በአረፍተ ነገሩ ወስጥ ከአንድ በላይ ግሶችን የያዘ አረፍተ ነገር ማለት ነው።

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጊዜን መለካት ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ ያለው የዘመን አቆጣጠር የሚከናወነው  ምንን መሠረት ባደረገ ልኬታ ነው?
3. በአከባቢያችሁ ያሉ የባህል ህክምና ዓይነቶችን ዘርዝሩ።
4. አስቴር <u>አንበሳ</u> ነች። የተሰመረበትን  ቃል እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ስጡ።
5. ከሚከቱለት ውስጥ ውስብስብ አረፍተ ነገር የቱ ነው?
   - ሀ. ልጁ ከትምህርት ቤት መጣና ምሳውን በላ።
   - ለ. ዳንኤልና ኢክራም ከትምህርት ቤት መጡ።
   - ሐ. እናታችን ለእኔና ለወንድሜ ልብስ ገዛችልን።
   - መ. ወንድሚ መልእክት ላከላት።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን ሙሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በዘመን አቆጣጠር ላይ የሚያተኩረውን ጽሑፍ አዳምጬ መረጃዎችን ይዣለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ሀገረሰባዊ የሕክምና ጥበብን በተመለከተ የቀረበውን ምንባብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በሚሰጡኝ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ንግግር አደርጋለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በሚና ተኮር ንግግር እሳተፋለሁ፡፡ | | | |
| 5 | በተጨባጭ ርእስ ጉዳች ላይ ድርሰት እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችዎች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን እመሰርታለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት፡ ለካቶ ትምህርት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኂላ፦

- አዳምጣችሁ ያልተሟላ አንቀጽ ታሟላላችሁ፡፡
- አዳምጣችሁ የራሳችሁን ሀሳብ ትሰጣላችሁ፡፡
- በተለያዩ ይዘቶች ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ፡፡
- ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ታሳያላችሁ፡፡
- የቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- በተወሰነ ርእሰ ጉዳይ ላይ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- ቅድመ፣ውስጠና  ድህረ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ መዋቅሮችን ትመሠርታላችሁ፡፡



## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ፈተናን ወደ መልካም ዕድል መለወጥ

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ እናንተ የምታደንቋቸውንና ውጤታማ ናቸው የምትሏቸውን አካል ጉዳተኞች ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡ የሠሯቸውንም ሥራዎች በቃል ተናገሩ፡፡
2. ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ስለሚባሉት ኢትዮጵያዊት ከአሁን ቀደም ሰምታችሁ የምታውቁት ነገር አለ? ሰምታችሁ የምታውቁ ከሆነ ለመምህራችሁ በቃል ንገሩ፡፡

**የተግባር መመሪያ**

መምህራችሁ “ፈተናን ወደ መልካም ዕድል መለወጥ” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጽሑፍ ያነቡላችኂል፡፡ ማስታወሻ በመያዝ አዳምጡ፡፡ ከዚያም የቀረቡ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. መምህራችሁ በመምህሩ መመሪያ የቀረበውን የአንድ ሰመጥር የህይወት ታሪክ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አድምጡና ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ያሉ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ፡፡

የትነበርሽ ንጉሴ እ.ኤ.አ ጥር 24፣ 1982 (1) _________ ተወለደች፡፡ በአጋጣሚት የማጅራት ገትር ህመም ምክንያት የአይን ብርሃንዋን ያጣችው በ(2) _________ ነበር፡፡ ፈጣሪዋን ከማማረርና ከመውቀስ ግን ይህን አጋጣሚ በተወለደችበት በአማራ ክልል በስፋት ይፈጸም ከነበረው (3) _________ የማምለጫ ዘዴ አድርጋ ቆጠረችው፡፡ 4) _________ እስኪሞላት ድረስ የነበረባት የአካል ጉዳት በሌሎች ዘንድ (5) _________ ሊቀንሰው እንደሚችል አስባው አታውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን እየዋለ እያደረ(6) _________ የነበሩ ልጆች (7)_________ ከመሆን ሲቆጠቡ ታስተውል ጀመር፡፡

፪. በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. የባለታሪኳ ሥራዎች በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው?
2. ወ/ሮ የትነበርሽ የዓይናቸውን ብርሐን ያጡት በምን ምክንያት ነበር?
3. ባለታሪኳ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ያገኙት በምን የትምህርት መስክ ነው?
4. ወ/ሮ የትነበርሽ ብርቱ ሴት እንዲሆኑ ያደረጋቸው ዋናው ምክንያት ምን ነበር?
5. የወ/ሮ የትነበርሽ የዘወትር ተግባር ምንድን ነው?
6. አጠቃላይ የጽሑፉ መልክት ምንድን ነው? ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
7. በአካበቢያችሁ ጎበዝ የሚባሉ አካል ጉዳተኛ ካሉ ከወ/ሮ የትነበርሽ ጋር በማነጻጸር ተናገሩ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

፩. በቡድን በቡድን በመሆን በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚሰጠውን ትኩረት ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

፪. በቤታችሁ፣ በትምህርት ቤታችሁና በአካባቢያችሁ ከምታዩትና ከምትሰሙት በመነሳት በአካል ጉዳተኛ ሰዎች ትምህርት ላይ እንቅፋት የሚሆኗቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አጋሯቸው፡፡

፫. በቡድን በቡድን በመሆን ዝግጅት ካደረጋችሁ በኋላ በምትወክሉት ተወካይ አማካኝነት ከታች ከቀረቡት ርዕሶች በአንዱ ላይ ተመካከራችሁ የክርክር ሃሳባችሁን አቅርባችሁ ተወያዩ፡፡

| ቡድን “ሀ” | ቡድን “ለ” |
|---|---|
| ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል | ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ አያስፈልግም |



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

# የአይበገሬነት ተምሳሌት

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. በየአካባቢያችሁ አካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች ካሉ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው መስተጋብር ምን እንደሚመስል ለመምህራችሁ በቃል ግለጹ።

፪. ከምንባቡ ርዕስ ተነስታችሁ ቀጥሎ የቀረበው ምንባብ ምን ምን ጉዳዮችን ይዳስሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ሁለቱ እጆቻችሁና ሁለቱ እግሮቻችሁ ባይኖሩ ኖሮ የቀን ከቀን ውሏችሁ ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡት። መራመድ ሳትችሉ፣ መሠረታዊ ፍላጎቶቻችሁን መከወን ሳትችሉ፣ እንደ ነፍሳችሁ የምትሳሱላቸውን ሰዎች እንኳ ማቀፍ ሳትችህሉ ስትቀሩ ህይወት ምን ሊመስል እንደሚችል ሳሉት።

በዚች አጭር ጽሑፍ ደግሞ ኒኮላስ (ኒክ) ቩይቺችን ተዋወቁት። ያለምንም ህክምናዊ ማብራሪያ፣ ኒክ እጆችና እግሮች ሳይኖሩት እ.ኤ.አ. ታህሳስ 4፣ 1984 ሜልቦረን፣ አውስትራሊያ ውስጥ ተወለደ። በዚህም ምክንያት በህይወቱ በበርካታ ችግሮች ውስጥ ለማለፍ ተገዷል፤ ብዙ መሰናክሎችንም ማለፍ ችሏል። ለምሳሌ እጆችና እግሮች ባለመኖሩ ምክንያት ዓለማቀፋዊ ትምህርት ቤቶች ሊቀበሉት አልቻሉም ነበር።

ኒክ መጀመሪያ ላይ እንደ ሌሎች ጓደኞቹ መሆን ባለመቻሉ በጣም ይበሳጭና ከፍተኛ ድብርት ውስጥ ይገባ ነበር። አስር ዓመት ላይ በመታጠቢያ ገንዳው ውስጥ ራሱን በማስጠም ራሱን ለማጥፋት ሞክሮ ነበር። እንደ ዕድል ሆኖ አባቱ ከሞት አዳነው። በኋላ ላይ ግን በራስ መተማመኑን አግኝቶ በህይወቱ ላይ ሙሉ ለውጥ አድርጓል። ወላጆቹም የትምህርት ህይወቱን እስኪጨርስ ድረስ በመደበኛ (ዋና) ትምህርት ቤት እንዲቆይ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በተጨማሪም ትምህርት ቤት ውስጥ እንደ ሌሎች ተማሪዎች መያዙንና ተገቢ ድጋፍ እየተሰጠው መሆኑን ለማረጋገጥ ሞክረዋል።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ከአነበባችሁት ታሪክ ምን ተገነዘባችሁ?

2. ከቀረው የምንባብ ክፍልስ ምን ትጠብቃላችሁ?

አስራ ሰባት አመት ሲሆነው በወቅቱ ይማር የነበረበት ትምህርት ቤት በነበሩ የጽዳት ሠራተኛ አማካኝነት ጥሩ ተናጋሪ እንዲሆን ይበረታታና ይጎተጎት ነበር። በዚህም ምክንያት በልጅነቱ ስላሳለፋቸው ችግሮችና መሰናክሎች ለሌሎች ተማሪዎች ንግግር ማድረግ ጀመረ። በእርሱ ህይወት ዙሪያ ንግግር ያደርግበት የነበረበት ዋና ምክንያት ሰዎች እሱን በማየት እንዲነሳሱ፣ እንዲበረቱና እነሱ በተለየ መንገድ አካሎቻቸውን የመጠቀም ችሎታ እንዳላቸው በማሳየት በህይወታቸው ትልቅ ነገር እንዲያደርጉ ለማስቻል ነበር።

የአጠቃላይ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ በ21 ዓመቱ ከግሪፍዝ ዩኒቨርሲቲ ሁለት ዲግሪዎችን (ቢ.ኤ ዲግሪ በሂሳብ አያያዝና ፋይናንስ ዕቅድ እና ቢ. ኤ ዲግሪ በንግድ) አግኝቷል። በዩኒቨርሲቲ ቆይታውም የንግግር ክህሎቶቹን አሳድጓል። የንግግር አሰልጣኙ ኒክ የንግግር ክሂሎቶቹን እንዲያሳድግ፣ እንዲሁም የአካል ቋንቋውንም እንዲያሻሽል ረድቶታል።

ኒክ አነቃቂ ንግግሮችን መስጠት እየጀመረ ባለበት ጊዜ አንዲት ወጣት ልጅ ለጥሩ አበረታች ንግግሮቹ አመስግናው ነበር። ይህ ደግሞ ኒክ ወደተለያዩ ሀገሮች እንዲጓዝና ብዙ ንግግሮችን እንዲያቀርብ መነሳሳትን ፈጥሮለታል። እየቆየም ጥሩ ተናጋሪ እየሆነ በመምጣቱ በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ታዳሚያን በሚገኙባቸው መድረኮች አነቃቂ በሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ንግግር ማድረግ ጀመረ።

ኒክ የእምነትና የተስፋ መልዕክቱን በዓለም ለማስፋፋት "ሕይወት ያለእጆችና እግሮች" የተሰኘ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ፈጥሯል። በተጨማሪም "አመለካከት ከፍታ ነው" የተሰኘ ድርጅት መስርቷል።

ኒክ ሥራዎቹን በቴሌቪዥን መርሐ ግበሮችና በጽሑፍ አስተዋውቋል። የመጀመሪያ መጽሐፉ እ.ኤ.አ. በ2010 ዓ.ም "ህይወት ያለእጅና እግር፤ ለአስቂኝ ጥሩ ህይወት" የተሰኘው ታትሟል። እ.ኤ.አ. በ2005 ዓ. ም. በእርሱ የእለት ከዕለት ተግባራትና የቤት ውስጥ ሕይወት ላይ ያጠነጠነ  አነቃቂ የሆነ አጭር ዘጋቢ ፊልም በዲቪዲ መልክ አዘጋጅቶ ሸጧል።

እ.ኤ.አ በ2008 ዓ.ም. ከካኔ ሚያሃራ ጋር ተዋወቀ።  ምንም እንኳ ኒክ እጆችና እግሮች ባይኖሩትም፣ ባለው ጥሩ ባህሪ፣ በሰብዕናውና በመልኩ ካኔ በጣም ተሳበችበት። በኋላ ኒክና ካኔ ተጋብተው በደቡብ ካሊፎርኒያ መኖር ጀመሩ። አሁን ትዳራቸው በልጆች ተባርኳል።

ኒክ እጅና እግር ያለው ሰው ሊያሳካቸው የሚችለውን ነገሮች ሁሉ ስላሳካ ለሁሉም ሰዎች መነሳሳት ምክንያት ነው። በዋና፣ በእግር ኳስና በሌሎች ብዙ ማህበራዊ ጉዳዮችና ክለቦች ይሳተፋል። ማድረግ የሚችለውንም ሁሉ አድርጓል።

ኒክ በአንዱ ንግግሩ ውስጥ ከተናገራቸው ጥቂት ቃላት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ። "ጓደኛዬ ትልቅ ህልም ይኑርህ፤ ተስፋ አትቁረጥ። በአንድ ጊዜ አንድ ጉዳይ ላይ አተኩር። ቀና አመለካከት፣ እይታ፣ መርህንና እውነታን ያዝ፤ አንተም ታሸንፋለህ።"

(http://www.attitudeisaltitude.com/about-nick-his-story)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ::**

1. የጽሑፉ አጠቃላይ መልእክት ምንድን ነው?
2. የዚህ ጽሑፍ ባለታሪክ የስኬት ምስጢር ምንድን ነው?
3. በኒክ ሕይወት የወላጆቹ አስተዋጽኦ ምን ይመስል ነበር?
4. ይህ የአይበገሬነት ተምሳሌት የሆነ ሰው በራሱ ህይወት ዙሪያ ያጠነጠነ ንግግር ያደርግ የነበረው ለምንድን ነው?
5. ኒክ በልጅነት ዕድሜው በራሱ ላይ ተስፋ ቆርጦ የነበረው ለምንድን ነው ?
6. በአካባቢያችሁ ልክ እንደ ኒክ ሹይቺች የአካል ጉዳተኝነታቸው ሳይበግራቸው ህይወታቸውን የሚመሩ ሰዎችን ፈልጋችሁ ታሪካቸውን በመጻፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ::

**ለ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ከአነበባችሁ በኋላ በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነውን "እውነት"፣ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ:: መልሳችሁ ሐሰት ከሆነ ምክንያታችሁንም በአጭሩ ግለጹ::**

1. ኒክ እምነቱንና ተስፋውን ለማስፋፋት ሲል ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ፈጥሯል::
2. ይህ ጠንካራ ባለታሪክ በሕይወት ዘመኑ በራሱ ላይ ተስፋ ቆርጦ አያውቅም::
3. የትምህርት ቤቱ የጽዳት ሠራተኛ ኒክ የአካል ቋንቋውን እንዲያሻሽል ረድቶታል::
4. አውስትሪያላዊው ኒክ ሁለት ዲግሪዎችን በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል::
5. ኒክ አካል ጉዳተኛ መሆኑ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች እንዳይቀበሉት አድርጎታል::
6. የዚህ ጽሑፍ ባለ ታሪክ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዳይሳተፍ የተገለለ ነው::

## ክፍለ ትምህርት ሶስት፡ ጽሕፈት

### የድርሰት ዓይነቶች

የድርሰት አይነቶች አራት ሲሆኑ እነሱም ተራኪ፣ ስእላዊ ፣ አስረጂና አመዛዛኝ ናቸው::

### ተራኪ ድርሰት

ስሙ እንደሚያመለክተው ተራኪ ድርሰት ሰንሰለታዊ ሁኔታዎችን ወይም ድርጊቶችን እንዲህ ሆነ ወይም እንዲህ ተደረገ በማለት የሚተርክ ነው:: ታሪኩ፣ ተራኪው የደረሰበት፣ በልምድ ያገኘው፣ በሀሳቡ ያውጠነጠነው ወይም ከሌላ ሰምቶ የሚያስታውሰውን ያህል አሳጥሮ ወይ አስፍቶ ለሌሎች የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል::

### ስእላዊ ድርሰት

ስእላዊ ጽሑፍ ለስሜት ህዋሶቻችን ቅርብ እንዲሆን ተደርጎ ምስል ከሳች በሆነ መንገድ የሚቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው።

### አስረጂ ድርሰት

ይህ የድርሰት ዓይነት ስለአንድ ጉዳይ መረጃን መሠረት በማድረግ እውቀትን ለአንባቢ ለመስጠት የሚጻፍ ነው። ዓላማው እውቀትን መስጠት ስለሆነ ዋና ትኩረቱ በመረጃ ሊረጋገጡ የሚችሉ ፍሬ ነገሮችን መዘርዘር ላይ ነው።

### አመዛዛኝ ድርሰት

አመዛዛኝ ድርሰት ጸሐፊው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት በተወሰኑ ነጥቦች ዙሪያ እየተሟገተ አንዱን ሀሳብ በአሸናፊነት እንዲወጣ የሚያደርግበት የጽሑፍ ዓይነት ነው።

**በምዕራፍ ሦስት ሥር የቀረቡትን የድርሰት አጻጻፍ መርሆችን በመጠቀም ከታች የቀረቡትን ተግባራት በትእዛዛቱ መሠረት ከውኑ።**

፩. ከተዘረዘሩት ርዕሶች መካከል አንዱን መርጣችሁ ከ150 ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ ስዕላዊ፣ አስረጂ፣ ወይም አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ።

1. ከሀገር ፍቅርና ከእናት ፍቅር
2. የኢትዮጵያዊያን ሴቶች ታሪክ
3. ሰፈሬ
4. ልጅነት

፪. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ወይም በተለያየ መንገድ ስለተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው ሲነገርላቸው የምትሰሟቸውን ጠንካራ አካል ጉዳተኛ ሰዎች አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብ ታሪካቸውን የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ።

፫. "ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው፤" የሚለውን ሀሳብ በሚመለከት አንድ ጽሑፍ አዘጋጁ።

፬. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑት ሰዎች እኩል በትምህርት ውጤታማ መሆን ይችላሉ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ድርሰት ጻፉ።

## ክፍለ ትምህርት ስምስት፡ ቃላት

### ቅጥያ

ቅጥያ ምንድን ነው? ቅጥያ ከሌሎች ምዕላዶች ለምሳሌ ከቃል ጋር ሲያያዙ ብቻ የሚገኝ ነው:: በብያኔው ቅጥያ ጥገኛ ምዕድ ነው:: በራሱ ሊቆም የሚችል ቅጥያ ያለው አንድም ቃል የለም:: ቅጥያዎች ከሚገቡበት ቦታ አኳያ ሦስት አይነት ናቸው:: እነዚህም ቅድመ፣ ድህረና ውስጠ ቅጥያዎች ብለን እንጠራቸዋለን::

1. **ቅድመ ቅጥያ፡-** ከቃሉ በፊት የሚገኝ ቅጥያ ነው::

   ምሳሌ፡- አስ- እና ኢ- ወዘተ.

   አስረጂ፡- አስ-ሠራ፣ ኢ-ፍጹም

2. **ድህረ ቅጥያ፡-** ከቃሉ በኋላ የሚያያዝ ቅጥያ ነው::

   ምሳሌ፡- -ነት፣-ኦ

   አስረጂ፡- የዋህነት፣ ሆዳምነት፣ ጅብ-ኦ › ጅቦ

3. **ውስጠ ቅጥያዎች፡-** በስሩ በራሱ ውስጥ የሚገቡ ቅጥያዎች ናቸው:: ውስጠገብ ቅጥያዎች እንደ አማርኛ ባሉ ሴሜቲክ ቋንቋዎች የተለመዱ ናቸው::

   ምሳሌ፡- ክ-ብ-ድ በሚለው ስር ውስጥ የተለያዩ ቅጥያዎች (አምድ መስራች አናባቢዎች) ሲገቡ  ከባድ (ክኧብብኣድ) የሚል ቃል (የቅፅል አምድ) ተመስርቷል::

**፩. ቀጥሎ በቀረቡት ቅጥያዎች በመጠቀም በምሳሌው መሠረት ቃሎችን መሥርቱ::**

| ዋና ቃል | ቅድመ ቅጣይ | ምሳሌ |
|---|---|---|
| 1. ሸለመ | ተ- | ተሸለመ |
| 2. ሠራ | መ- | መስራት |

| ዋና ቃል | ድህረ ቅጥያዎች | ምሳሌ |
|---|---|---|
| 1. ተራራ | -ኣማ | ተራራማ |
| 2. ኃይል | -ኧኛ | ኃይለኛ |
| 3. ሹም | -ኧት | ሹመት |
| 4. ወገን | -ኣዊ | ወገናዊ |

፪. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ቅድመና ድህረ ቅጥያዎችን ዕውጡ፡፡

ምሳሌ፡- በከንፈራምነቱ

በ-ከንፈር-ኣም-ነት-ኡ

1. ኢትዮጵያዊ
2. ጓደኝነት
3. አስተማሪነት
4. ኢሞራላዊ
5. መጥረግ
6. ድብብቆሽ

## ክፍስ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

፩. በምዕራፍ ሁስት ክፍል ስድስት ስስ ዕማርኛ የቃል ክፍሎች የተማራችሁትን በማስታወስ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በጉልህ ተጽፈው የተሰመረባቸውን ቃላት የቃል ክፍላቸውን ስዩ፡፡

1. እንግዲህ ሞታም ከሆነ ደብዳቤያችን ተመልሶ ይመጣልናል፡፡
2. እንግዲህ ህዳር ከገባ፣ ነገ ወደ ላይ ወደ ኮረብታዎቹ ወጥቼ እንጉዳይ እለቃቅማለሁ፡፡
3. እግራችን ወደ ጉድጓድ እየሄደ ነው፡፡ ሞት ደግሞ ሌባ ይመስል፣ ሹክክ ብሎ ነው የሚመጣ፡፡
4. ያይበገሬነትና ሌሎችም ብሄራዊ ባህሪያት እጅግ ስለሚመስጡኝና ጉዳዩ በጥሞና ለማጥናት ስመኘው የነበረ በመሆኑ ብዙ ሳላንገራግር ተነሳሁ…
5. ጭንቀታም! ያላቅሙ ይንጠራራል!
6. አስተማሪው እየተንጎራደደ “በላ ተናገር! ምን መሆን ትመኛለህ?” አለኝ፡፡
7. እኔ ደግሞ አልፌው ሊሄዱ ነው ብያለሁ፡፡ ከፊት-ለፊት ካለው ዲብ ላይ፣ ከቤቱ መቼም አንድ ሃያ እርምጃ ይሆናል፤ ቆሞ፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረቡት ዕረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ዕሉባቸው፡፡ ስህተቶቹን በማረም ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ ዕረፍተ ነገሮች ጻፉ፡፡

1. ልክ ከዚህ ጋ ነው ምንጪቱ ያለች፡፡
2. ከዛፉ ስር፣ ጉድጓድ ስፋቷ አንድ ሰው የሚያስገባ፣ ወደታች ደግሞ የኔን ቁመት የሚያጠልቅ ነበረች፡፡
3. ጉድጓዱን ግን ሞልታው ኣታውቅ ምንጪቱ፡፡

4. ከምንጪቱ ማሳዎቹ  ወረድ ብለው አይደል ያለ?

5. ጊዜ የምታስተካክልልኝ እያስመሰለች ለመግዛት ኩታውን እየነካካችና ሙግት ገባች፡፡

6. ጎረቤቱ ሲስቅ ሁሉ አመሹ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የቀረበላችሁን ጽሑፍ አዳምጣችሁ ተረድታችኋል፡፡ ያያችሁትንና የሰማችሁትን መሠረት በማድረግ  በተሰጧችሁ ርእሰ ጉዳዮች ላይ  ንግግር አድርጋችኋል፡፡ በውይይቶችም ተሳትፋችኋል፡፡ ጽሕፈት በሚለው ክፍል ደግሞ በቀረቡላችሁ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ  ድርሰቶችን መጻፍ ችላችኋል፡፡ በክፍል አምስት ቃላት በሚለው ስር የቅድመና ድህረ  ቅጥያዎችን  ምንነት ተገንዝባችኋል፡፡ ቅድመ ቅጥያ ማለት በግራ በኩል ከፊት ለፊት የሚጨመር ሲሆን ድህረ ቅጥያ ደግሞ በቀኝ በኩል ከኋላ ላይ የሚጨመር ቅጥያ ነው፡፡ የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጠቀምም የተለያዩ ቃላትን መሥርታችኋል፡፡ በመጨረሻም ሰዋስው በሚለው ክፍል የቃላትን የቃል ክፍል በአውዳቸው መሠረት ለይታችኋል፡፡ የቃል ክፍሎች የሚባሉት ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድና መስተዓምር ናቸው፡፡ ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችንም ጽፋችኋል፡፡ አንድ የአማርኛ አረፍተ ነገር ሰዋስዋዊ  ህግን የጠበቀ ነው የሚባለው የቃል አደራደሩ ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ግስ ከሆነና በግሱ ላይ የሚታዩት የባለቤትና የተሳቢ አፀፋ ምዕላዶች ከአረፍተ ነገሩ ባለቤትና ተሳቢ ጋር ተስማሚ ሲሆኑ ነው፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. አካል ጉዳተኝነት ማለት ነገሮችን ማድረግ አለመቻል አይደለም፤ የሚለውን ሀሳብ ደግፋችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

2. <u>አንደኛ</u> የሚለው ቃል የተመሠረተበትን መንገድ በቃል አብራሩ፡፡

3. <u>አስተማሪነት</u> በሚለው ቃል ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በመለየት ለመምህሩ ተናገሩ፡፡

4. "<u>ጳኛቸው</u> መጽሐፍ ማንበብ ይወዳል፤" በሚለው አረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

5. "የተጣሉትን ሰዎች ማን <u>ዳኛቸው?</u>" በሚለው አረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ምንድን ነው?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በስኬታማ አካል ጉዳተኛ ሴት ዙሪያ የሚያተኩረውን ጽሑፍ አዳምጬ መረጃዎችን ይዣለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የአካል ጉዳተኛ ጠንካራ ሰውን በተመለከተ የቀረበውን ምንባብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር አደርጋለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በሚቀርቡ የተለያዩ ሀሳቦች ላይ የማጠቃለያ ሀሳብ እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ቅድመና ድህረ ቅጥያዎችን ለይቻለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ ዓረፍተ ነገሮችን እመሰርታለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት፡ ሥነግጥም

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የቀረበውን ግጥም በማዳመጥ ማብራሪያ ትሰጣላችሁ::
- የተሰጣችሁን ግጥም ተጠቅማችሁ በግጥሙ ላይ ውይይት ታደርጋላችሁ::
- ግጥሞችን በመሰብሰብ ታነባላችሁ::
- ስለመማሪያ ክፍላችሁ አጭር ግጥም ትጽፋላችሁ::
- የሥነግጥም ቃላት አጠቃቀምን ታብራራላችሁ::
- ሥነግጥም የሚያካትታቸውን ይዘቶች ትዘረዝራላችሁ::
- የቃላትን የፍች ልዩነት ታሳያላችሁ::
- እማሬያዊና ፍካሪያዊ ፍች አብራርታችሁ ትጽፋላችሁ::



## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ሀገሬ ዋርካ ናት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ

ስለ ሀገር ፍቅር የተገጠመ የምታውቁት ግጥም ካለ ወይም ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሟቸው::

### የተግባር መመሪያ

መምህራችሁ ''ሀገሬ ዋርካ ናት'' በሚል ርዕስ አንድ አጭር ግጥም ያነቡላችኋል:: እናንተም በጥሞና አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል ማስታወሻ ያዙ::

### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. "ሀገሬ ዋርካ ናት''የሚለውን ግጥም ካዳመጣችሁ በኋላ በይዘቱ ላይ ውይይት አድርጉና በጽሑፍ ውጤቱን አቅርቡ::
2. ጸሐፊው አገሩን በዋርካ የመሰላት ለምንድን ነው? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና መልሱን በጽሑፍ ለመምህራችሁ ስጡ::
3. የአዳመጣችሁትን ግጥም  ጭብጥ ምን እንደሆን በጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ::



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

፩. የሚከተለውን ግጥም አንብቡና ስለ ጭብጡ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

**ሞት ቀስሙ ይሰበር**

እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ስሞት ሞትም አብሮኝ ይሙት
በሳቅ በደስታ ግደሉት
በሃሴት በዕልልታ ውገሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ለሞት የልብ ልብ አትስጡት
ናቁት አጥላሉት አውግዙት
በሙሾ ግነን አትበሉት
በሞቴ፣ እንዳታስደስቱት፡፡
እንደ ዶርዜ ወንድሞቼ
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ
ሞቴን በዘፈን ሞልቼ
በዳንኪራ ሰበቃና፣ በዘፈን ሆይታ አካትቼ
በሠርጌ ብቀበር ሞቼ
እፀድቅ ነበር ባትረሱ
በእንባ ውሌን ባታፈርሱ፡፡

ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን ፲፱፻፷፫

፪. ግጥም ከሌሳው ድሑፍ ዘርፍ በተለየ መልኩ እምቅ ሀሳብ ይይዛል የሚባለው ለምንድን ነው? በጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩና ማስታዎሻ ያዙ፡፡ ሀሳባችሁንም በቡድን ተወካያችሁ አማካይነት ለክፍሉ ተማሪዎች ተናገሩ፡፡

፫. እባካችሁ ዘመዶቼ፣ በሳቅ ጉዞ ፍታት ፍቱኝ
በሙሾ ዋይታ አታጅሉኝ፤
እናቴም ፊትሽ አይክሰል
በእልልታ ብርሃን ይንበልበል፤
በእረፍቴ እንዳታፌዥብኝ
በሠርጌ እንዳታለቅሽብኝ፡፡
ገጽሽ በጭንቅ አይወረስ

ልብሽ በኀዘን አይላበስ

በሆድሽ ሞት አይፀነስ

ዕንባ በአይንሽ አይቋጠር

የሞት ቅስሙ እንዲሰበር።

የተግባር መመሪያ

በዚህ ግጥም በሞት ማንጠሪያነት የተላለፈው መልዕክት ምን እንደሆነ በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ ማብራሪያውን በቃል ተናገሩ።



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

## ኢትዮጵያዊ ነን!!

### ቅድመ ንባብ ጥያቄ

ግጥምን ሁሉም ሰው መጻፍ ይችላል? ይችላል ካላችሁ ሁለት ስንኝ ያለው ግጥም በደብተራችሁ ላይ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ። አይችልም ካላችሁ ደግሞ ምክንያታችሁን አስረዱ።

ፈቅደን ሲመሩን፣ ችቦ ተቀባይ፣

ለሚነዱን ግን፣ አሻፈረን ባይ፣

ካልነኩን በቀር፣ ቀድመን 'ማንዘምት፣

ከጋሻ በፊት፣ ጦር የማንሸምት፣

ኢትዮጵያዊ ነን!

ህብር ያስጌጠው፣ ህይወት ለማብቀል

ዘር ሳናጣራ፣ የምንዳቀል

ለነዱን ሰይጣን፣ ለመሩን ሰናይ

ጌታን ከገባር፣ ለይተን ምናይ፤

ኢትዮጵያዊ ነን! ( በዕውቀቱ ስዩም ። 2012 ።)

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ያነበባችሁት ግጥም ስለምን ይናገራል?
2. ከተቋረጠበት ቀጥሎ ያለውን ስንኝ አማልታችሁ ግጥሙን በእናንተ ሀሳብ ጨርሱት።

ብዙ ህልሞችን፣ ወዳንድ ዐላማ፣የሰበሰበ ገርቶ፣ ያስማማ፣

በደምና ላብ፤ያቆምነው ካስማ፣

አገዳ አይደለም፣ የሚቀነጠስ፣

የዝምድናችን መተሳሰርያ፣

ሺጊዜ ቢክር፣ የማይበጠስ

ኢትዮጵያዊ ነን!

ምን ሆድ ቢብሰን፣ ምን ብንቸገር፣

እድር አይፈርስም፣ እንኩዋንስ አገር፣

ብለን በትግስት፣ የምንሻገር፣

ሲገፈትረን፣ ግፈኛና አጥቂ፣

ቁልቁል ሲሰደን፣ ሽቅብ መጣቂ፣

ለውርደት ሲያጩን፣ የምንጀነን

ኢትዮጵያዊ ነን!

(በዕውቀቱ ሥዩም፣ 2012)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**ሀ. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ስጡ፡፡**

1. “ኢትዮጵያዊ ነን” የሚለው ቃል ለግጥሙ ምን በመሆን ያገለግላል?

ሀ. አዝማች    ለ. መሪ    ሐ. ፈካሪ    መ. ሁሉም

2. ግጥሙ ምን ዓይነት ግጥም ነው?

ሀ. የሙሾ    ለ. የዘፈን    ሐ. የፉከራ    መ. የቀረርቶ

3. የግጥሙ መልዕክት ለማን የተላለፈ ይመስላችኋል?

ሀ. ለአዝማሪው    ለ. ለፎካሪው    ሐ. ለጠላት    መ. ለመምህሩ

4. ህብር ያስጌጠው፣ ህይወት ለማብቀል

ዘር ሳናጣራ፣ የምንዳቀል

ለነዱን ሰይጣን፣ ለመሩን ሰናይ

ጌታን ከገባር፣ ለይተን ምናይ፤

ከላይ በቀረቡት አራት ስንኞች ውስጥ የሚገኙ ሀረጋት ስንት ናቸው?

ሀ. አንድ    ለ. ሁለት    ሐ. አራት    መ. ስምንት

5. በተራ ቁጥር አራት ከቀረበው ግጥም ሦስተኛው ስንኝ ሁለተኛው ሀረግ _____________ ነው፡፡

ሀ. ለነዱን ሰይጣን    ለ. ለይተን ምናይ    ሐ. ለመሩን ሰናይ    መ. ጌታን ከገባር

## ግጥም

ግጥም የፈጠራ ጽሁፍ ነው:: በግጥም ውሰጥ ቃላትን መምረጥና በተገቢው መንገድ በቦታቸው ማስቀመጥ ያስፈልጋል:: አለያ ግጥሙ ተራ ይሆንና ሳቢነቱ ያነሰ፣አንባቢን ወይም አድማጭን የማይጋብዝ ይሆናል። እስቲ ስለግጥም ምንነት የተሰጠ አንድ ብያኔ እንመልከት::

> ሥነግጥም በቋነቋ አማካኝነት የሚከሰት፣ ጣዕመ ዜማ ያለው፣ ምርጥና በሳል ቃላት የተሰደሩበት፣ደማቅ ዘይቤው የጠበቀ፣ አባጣ ጎባጣ ኮረኮንች የሌለው፣ ጀሮ የማይኮረኩር፣ ስንኙ ከአንድ ግስ በወጡ ዘሮች ቤት የሚመታ፣ ቀጥያሉና ሚዛናዊ የሆኑ መስመሮች በአንጓ ተከፍለው የሚቀርቡበት፣ የሥነጽሑፍ ዘርፍ ነው::

(አያልነህ ሙላቱ:: 2004::)

ከዚህ ሌላ የግጥም ባህሪያት ከሚባሉት ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

ቤት መምታት፣ የቃላት ምርጫ፣ ማፈንገጥ፣ ድግግሞሽ፣ ምስል ከሳችነት፣ ምት፣ ዜማዊ ፣ዘይቤዊ

አገላለጾች፤ይጠቀሳሉ::

፩ ከላይ የተገለጸውን የግጥም ባህሪይ ካነበባችሁ በኋላ ከላይ ያነበባችሁት ግጥም በየትኛው የግጥም ባህሪ የተጻፈ ነው? አጭር መልስ ጻፉ::

፫ የሚከተለውን ግጥም በቃላችሁ ያዙና ክፍል ውስጥ በተራ አንብቡት::

የኔ ውብ ከተማ

ከጎራው ዘልቄ እስኪ ልነጋገር
ካለሰው ቢወዱት ምን ያደርጋል አገር?
የኔ ውብ ከተማ
ሕንፃ መች ሆነና የድንጋይ ክምር
የኔ ውብ ከተማ
መንገድ መች ሆነና የድንጋይ አጥር
የኔ ውብ ከተማ የኔ ውብ አገር
የሰው ልጅ ልብ ነው
የሌለው ዳርቻ የሌለው ድንበር::
ሕንፃው ምን ቢረዝም ምን ቢፀዳ ቤቱ
መንገዱ ቢሰፋ ቢንጣለል አስፋልቱ
ሰው ሰው ካልሸተተ ምንድነው ውበቱ?

(በዓሉ ግርማ፣ 1984)



## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

፩ ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም አሟልታችሁ ጻፉ::

ህመምሽን ታመው፣ ስቃይሽን ተጋርተው

ትንሳኤሽን ሊያዩ፣ ____________________::

ለሚጠባበቁት፣ ዛሬ ብርሃን ነው::

________________________፣ ከጉባ ተራራ

ጨለማውን ገፎ፣________________

ማታ ፈልቋልና፣ የአባይ ግድብ::

፪ ስለመማሪያ ክፍላችሁ አጭር ግጥም ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::




## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉና የተሰመረባቸውን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አብራርታችሁ ጻፉ::

1. ሆዱን <u>በላው::</u>
2. <u>ጎጆው</u> ፈረሰ::
3. <u>በዱላ</u> አበራየው::
4. እርካሽ እንጀራ አግኝቼ ነበረ፤

   እሱም ውድ ሆነና <u>ሳልሽምተው</u> ቀረ::
5. በንዴት ሆዱ <u>ነፈረ::</u>

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በትእዛዛቱ መሰረት የርባታ ሥርዐታቸውን አሳዩ::

፩. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ የርባታ ሥርዐት ያላቸው ስሞችና ቅጽሎች ናቸው:: ቃላቱን ለብዙ ቁጥርና ለጾታ ሲረቡ አሳዩ::

ምሳሌ፡- ልጅ

ለቁጥር፡- ልጆች

ለጾታ፡- ልጂቱ

1. ቤት
2. እናት
3. ወላጅ
4. ጎበዝ
5. ጀግና

፪.ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ግሶች ናቸው:: ቃላቱን ለሁለተኛና ሦስተኛ መደብ፣ ለነጠላና ብዙቁጥርና ለአነስታይና ተባዕታይ ጾታ ሲረቡ አሳዩ::

ምሳሌ፡- ሰበር-ኧ ለ3ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ

ሰበር-ኧች ለ3ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አነስታይ ፆታ

ሰበር-ኡ ለ3ኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር፣

1. ገደለ
2. ነገደ
3. አከመ

፫. ከላይ በቃላችሁ እንድታነቡት የታዘዛችሁትን ‘’ዮኔ ውብ ከተማ’’ የሚለው ግጥም የተጻፈባቸውን ቃላት ተጠቅማችሁ ግጥሙን ወደ ስድ/ዝርው ጽሁፍ ለውጡና የቃላትን የአጠቃቀም ልዩነት ለመምህራችሁ አሳዩ ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአዳምጦና የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በመጠቀም የሥነግጥምን ንበት ተከታትላችሁ አውቃችኋል:: ግጥም በባህሪው ማራኪና ሳቢ ነው:: የሚጻፈውም በተመረጡና በተቆጠቡ ቃላት ነው:: የግጥም ቃላት ይፈጠራሉ፤ የልቦለድ ቃላት ይመረጣሉ:: በተጨማሪም የተሰጣችሁን ግጥም በማንበብና ፍሬ ሀሳቡን ለማውጣት ግጥሙን ከተጠቀሱት የንባብ ስልቶች በአንዱ አንብባችኋል:: ጽሕፈት በሚለው ክፍልም ተጀምረው ያላለቁ የግጥም ስንኞችን በመጨረስ ግጥም መጻፍን ተለማምዳችኋል:: የግጥም ስንኝ ማለት የግጥሙ አንድ መስመር ማለት ነው:: ቃላትን በተመለከተ የግጥም ቃላት ከሌላው የጽሑፍ ቃላት እንዴት እንደሚለዩ በቀረበው ግጥም ምሳሌነት በተግባር ግጥም በመጻፍ ተለማምዳችኋል:: በመጨረሻም ሰዋስው በሚለው ክፍል ቃላት ለቁጥር፣ ለጾታና ለመደብ እንዴት እንደሚረቡ ተረድታችኋል:: በቋንቋ ውስጥ ቁጥር ማለት ብዙና ነጠላ ማለት ነው:: ጾታም ሴትና ወንድን ያመለክታል:: መድብ ሲባልም አረፍተ ነገሩ ያተነገረበትን ባለቤት ያመለክታል:: አንደኛ መደብ እኔ፣ ሁለተኛ መደብ አንተ፣ አንቺ፣ ሶስተኛ መደብ እሱ፣ እሷ እነሱ ማለትነው:: በዝርው ጽሑፍና በግጥም ወቅት የሚኖራቸውን የአጠቃቀም ልዩነት በተግባር በመስራት ተለማምዳችኋል:: ዝርው ጽሁፍ ማለት ግጥም ያልሆነ ጽሑፍን ያመለክታል:: ምሳሌ፦ ልቦለድ፣ ደብዳቤ፣ የምርምር ጽሑፍ ወዘተ.

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ግጥም ቁጥብና እምቅ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ?
2. የግጥም ቃላት ይፈጠራል ሲባል ምን ትረዳላችሁ?
3. ግጥም ለመጻፍ የሚያስፈልገው እውቀት የምን እውቀት ነው?
4. ግጥም ከሌላው የጽሑፍ ዘርፍ በምን በምን ባህሪው ይለያል?
5. የማንን ግጥም ታደንቃላችሁ? ከምታደንቁት ገጣሚ አንድ አንድ ግጥም በማምጣት ለጓደኖቻችሁ አንብቡላቸው::
6. ያነበባችሁትን ግጥም ጭብጥ ወደ ዝርው ጽሑፍ ቀይራችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::
7. በግጥም ውስጥ የምታገኟቸውን የተለዩ ቃላት ሰብስቡና

   ሀ. ለመደብ፣ ለጾታና ለቁጥር አርቡአቸው

   ለ. አንድ አንቀጽ ዝርው ጽሑፍ ጻፉባቸው::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (V) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥነግጥም ባህርያትን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ግጥም መጻፍ ተለማምጃለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የቃላትን እማሬና ፍካሬ ፍች መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ግጥም በባህሪው ብዙ ሀሳቦችን ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ግጥም አጭርና ቁጥብ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ቃላት ለቁጥር፣ ለጾታና ለመደብ ቅርጻቸውን እንደሚለውጡ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 7 | የግጥም ቃላት አጠቃቀም ከዝርው ጽሑፍ ቃላት አጠቃቀም እንደሚለይ ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡ አንድነትና ብዝሃነት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- አዳምጣችሁ የአካባቢያችሁን ማህበራዊ አውድ ትገልጻላችሁ::
- የዳመጣችሁትን ጽሑፍ ወደ ንግግርና ውይይት ለውጣችሁ ታቀርባላችሁ::
- የክፍል ውስጥ ንግግራችሁን ከጓደኞቻችሁ ንግግር ጋር በማነጻጸር ልምድ ትለዋወጣላችሁ::
- በመምህሩ/በተጋባዥ እንግዶች የሚቀርቡ ንግግሮችን ትተነትናላችሁ::
- የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ተጠቅማችሁ መረጃዎችን ትናገራላችሁ::
- በተለያዩ ይዘቶች ላይ ጽሑፎችን ከአዘጋጃችሁ በኋላ ከጓደኞቻችሁ ሥራ ጋር ታወዳድራላችሁ::
- የጽሕፈት ደረጃዎችን ትዘረዝራላችሁ::
- ከአነበባችሁትና ከአዳመጣችሁት ያገኛችኋቸውን አዳዲስ ቃላት ተጠቅማችሁ ድርሰት ትጽፋላችሁ::



## ክፍል ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### አንዱ ለሌላው ምንድን ነው?

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. በእናንተ እይታ አንድነት ማለት ምን ማለት ነው? መልሳችሁን ለጓደኛችሁ ንገሩ::
2. ስለብዝሃነት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

**የተግባር መመሪያ**

መምህራችሁ "አንዱ ለሌላው ምንድን ነው?" በሚል ርዕስ አንድ አጭር ጽሑፍ ያነቡላችኋል:: እናንተም በጥሞና አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል ማስታወሻ ያዙ::

**ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

ጽሑፉን አዳምጣችሁ ስትጨርሱ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ቡድን በመመስረት ተወያዩና የውይይታችሁን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

1. ኢትዮጵያዊያን ስለብዝሃነትና አንድነት ሲመክሩ ከሁለቱ ስለአንዱ እንጂ ስለሁለቱም አፋቸውን ሞልተው መናገር የሚፈሩት ለምንድነው? አብራሩ::
2. በግልጽ የሚታየውን ልዩነት መደበቅ ወይም የሌለ ማስመሰል ፋይዳው ምንድን ነው?
3. ሰዎች በአንድነት ውስጥ ልዩነቶች መኖሩን፤ በልዩነቶች ውስጥ አንድነት መኖሩን መረዳት ለምን ይሳናቸዋል?



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

1. የአንድነትና ብዝሃነትን አስተሳሰብ ለውጥ መገመት የሚቻል ይመስላችኋል? መጀመሪያ በጥንድ፤ ቀጥሎ በቡድን በመሆን ውይይት አካሂዱና የውይይታችሁን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

2. የተፈጥሮ ሥርዓት፤ በሕዝቦች ሕይወትና ግንኙነት ውስጥ ይታያል። ብዝሃነት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሥራ ውጤት ነው። እያንዳንዱ ሰው የት፤ መቼና ከማን እንደሚወለድ መወሰን ወይም መምረጥ አይችልም። ጥቁር ወይም ነጭ፤ አማራ፣ ትግራዋይ፣ ወላይታ፣ አኝዋ፣ ሶማሊ፣ አፋር፣ ኦሮሞ ወይም ሽናሻ ወዘተ. ሆኖ መወለድ የራስ ምርጫ ሳይሆን የተፈጥሮ ውሳኔ ነው። ሰው ሰራሽ የሚሆነው ደግሞ ሰው የሚፈልገውን የትምህርት ዓይነት፤ ሙያ፤ የመኖሪያ ሥፍራ፤እምነት፤ ርዕዮተ ዓለምንና የመሳሰሉትን መርጦ መሆን ወይም መከተል መቻሉ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ መርጦ በያዛቸውና ባወቃቸው ነገሮች ሳይሆን ባልመረጣቸውና በማያውቃቸው ነገሮች መነሻነት መናቆር ለምን ይመስላችኋል? በውይይት መፍትሄውን ፈልጉና ጻፉ።



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

### ሰፊ ንባብ፦

በስፋትና በመጠን ለረዥም ጊዜ ማንበብ ነው።

ለምሳሌ፡- ሁሉንም መፃህፍት፣ ለአጠቃላይ እውቀት ትኩረት በመስጠት ማንበብ ሲሆን፣ ይህ የንባብ መርሃ ግብር ተጨማሪ የክፍል ውስጥ የማንበብ መርሃግብር አካል ነው። በተለይም ከቋንቋ ትምህርት ጋር የተገናኘና ተማሪዎች በራሳቸው አቅምና መጠን፣ ለፈተና ወይም ለማርክ ተብሎ ሳይሆን ለአጠቃላይ እውቀት ዘና ብለው በራሳቸው እንዲያነቡ የሚበረታቱበት ነው፤ እዚህ ላይ የመምህሩ ሚና የሚሆነው ተማሪዎችን ማበረታታት፣ ክትትል ማድረግና መፃህፍትን በሚፈለጉት መጠን እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

በንባብ ወቅት የሚገኙት ቃላት በጥራት፣ በአይነትና በብዛት በቂ የሆኑ፣ ለተማሪዎች ጠቃሚና ሳቢ እንዲሆኑ የሚመረጡት መጻሕፍት በተማሪዎች እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና እውቀት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

የሰፊ ንባብ መርሃግብር  የተለያዩ ስሞች አሉት፡- እነሱም፣ ማቋረጥ የሌለበት የንባብ፣ ሁሉን ነገር ትቶ የማንበብ መርሃግብር፣ ፀጥታ ያለበትና ያልተቋረጠ ንባብና የፍጥነት ንባብ በመባል ይጠራል።

## የተፈጥሮ መንታ ገፅታዎች

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስለብዝሃነትና አንድነት የምትረዱትን ነገር ለጓደኞቻችሁ ግለጹ::
2. አንድነትና ብዝሃነት ለእናንተ ምን ማለት ነው?
3. ምስሉን በመመልከት የተረዳችሁትን በጋራ በመሆን ተወያዩና የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እደሚችል ገምቱ::



ሥዕል 10፡ የተወሰኑ የብሔር ብሔረሰብ ምሥሎች

ሌጣ ትርጉሙ ብዝሃነት፣ ዝንቅነት፣ ጉራማይሌነት ወይም ዥንጉርጉርነት ማለት ነው:: አንድነት ማለት ደግሞ ኅብራዊነት፣ ተመሳስሎ ወይም ወጥነት ነው:: ብዝሃነትና አንድነት የተፈጥሮ ቀለማት ናቸው:: ተፈጥሮ ህልቆ መሳፍርቷን የምታቻችልበት፣ ጎደሎዋን የምትሞላበት፣ ህልውናዋን የምታረጋግጥባቸው መንገዶች ናቸው:: ልዩነት እንጂ ተቃርኖ የላቸውም:: አይነጣጠሉም፣ አንዱ ያለሌላው አይኖርም:: በዥንጉርጉርነት ውስጥ ኅብር፣ በኅብር ውስጥ ዥንጉርጉርነት አለ:: ማኅበረ-ሰብ የተፈጥሮ አካልና አምሳል እንደመሆኑ፣ በአመለካከቱና አኗኗሩ የተፈጥሮውን ቅኝትና መንፈስ መከተል ጤናማ ባሕርይው ነው:: የሰውልጅ ቁሳዊ፣ ማኅበራዊና ሥነልቡናዊ ዓለሙን በሥርዓትና በመልክ የሚያሰናዳው፣ የሚገነዘበውና የሚተረጉመው አንድነትና ልዩነታቸውን እያነጠረ ነው:: ከሁሉም በላይ ብዝሃነትና አንድነት ተደጋጋፊ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ አብሮ የመኖር ፍልስፍናዎች ናቸው::

በመጀመሪያ የሰው ልጆች ሰብአዊነታችን በራሱ የሚያጋራን ውስጣዊ ባሕርያት አሉን:: በዙሪያችን ከሚዳበሉ የተፈጥሮ አካላት ጋር የምናደርገው መስተጋብርም ልዩነትና ተመሳስሎ ያላብሰናል:: የምንጋራው መልክ ዓምድርና የአየር ንብረት በራሱ የባሕርይ፣ የአኗኗርና የአስተሳሰብ ወጥነት ይሰጠናል:: በታሪክ ያለፍንበት ውጣውረድ፣ ፈተና፣ ዕድልና ተስፋም የራሱን ዝንቅ አሻራ ይተዋል::

የአንድነት ኅብሩ፣ ተመሳስሎው ወይም ወጥነቱ በመርሆችና በሕግጋት፣ በሥርዓቶችና ተቋማት፣በእሴቶችና እምነቶች ወዘተ. ሊሆን ይችላል። ኢትዮጵያዊያን ዛሬም ወደድንም ጠላንም የምንኖረው በአንዲት ሀገር ነው። ያለንም አንድ ብሔራዊ መንግሥት ነው። ዜግነታችንም ቢያንስ ከሕግ አኳያ አንድ ኢትዮጵያዊነት ነው። ከዚህ ወረድ ስንል ሃይማኖታችን ክርስቲያን ወይም እስላም ወይም ባህላዊ ወይም ሌላ ሆኖ ያቆራኘናል። በአካባቢ፣ በወንዜ ልጅነት አብሮነት እናገኛለን። መደባችንና ሞያችን ገበሬ፣ አርብቶአደር፣ ነጋዴ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ መሆን ያገናኘናል። በአጠቃላይ በአገር፣ በብሔረሰብና ማኅበረሰብ ደረጃ ያስተሳሰሩን ውስብስብና ተደራራቢ ድሮች አሉን። ማንነታችን የነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነው። እንደ አግባቡ አንዱን ወይም ሌላውን እያጎላና እያደበዘዘ የሚገልፅ፣ ሰፊ የመንሸራሸሪያ ዕድል ያለውና ለሰብዕናችን ነጻነት የሚሰጥ ነው። በአጠቃላይ የሰውልጅ ድርብርብ ማንነቶችን አቻችሎና አካትቶ ለመኖር የተሰራ ነው፤ አንድነትና ብዝሃነት።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረቡት አንቀጾች ስለብዝሃነትና አንድነት ምን ተረዳችሁ?
2. የብዝሃነትና የአንድነት ጉዳይ ግለሰባዊ እይታ የሚንጸባረቅበት ነው። ስለዚህ እናንተ እንደግለሰብ ምን አስተያየት አላችሁ?

የአንድነትም ሆነ የብዝሃነት አቋሞች በማኅበራዊነት የሚበለጽጉ እንጂ፣ በዘር ወይም በደም የሚተላለፉ አይደሉም። አንድ ሰው የአንድነት ወይም የብዝሃነት አቀንቃኝ ሆኖ አይወለድም። ማኅበራዊ መሠረት ቢኖራቸውም ቅሉ፣ በተለያዩ አግባቦች የሚፈጠሩና የሚከስሙ ግለሰባዊ አመለካከቶች ናቸው። ዛሬ ብዝሃነትን የሚያቀነቅኑ ነገ አንድነትን ሊያራምዱ ይችላሉ። በንድፈ ሐሳብም ሆነ በተግባር ብዝሃነት ዴሞክራሲን፣ አንድነት ደግሞ ጭቆናን አያመለክቱም። ሌላውን ትተን ከገዛ ታሪካችን እንደተመለከትነው ዴሞክራሲ፣ ፍትሕና ነጻነት ሊያብቡ ወይም ሊቀጭጩ የሚችሉት የመንግሥቱ ቅርጽ ብዝሃዊ ወይም አሃዳዊ ስለሆነ አይደለም።

እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባው ጉዳዩ ሆነ ተብሎ በአንድ ቃል ታስሮ በመድበስበሱ እንጂ፣ ብዝሃዊነት "በኅብረ ባሕላዊነት" ይገለጻል። የኅብረ ባሕላዊነት ፍልስፍና ሰፊና ፈርጀ ብዙ ነው።ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነልቡናዊ፣ ወዘተ. ጎኖችን ያካትታል። ለኅብረባህላዊነት፣ ባህሎች ያፈጁ፣ ዝጎችና ሙቶች ሳይሆኑ፤ ታዳሽ፣ ክፍቶችና ህያዋን ናቸው። የኅብረ ባሕላዊነት ቁልፍ እሳቤ መነጠልና በራስ መዋጥ ሳይሆን፣ ብዝሃዊነትን ተገንዝቦ በማኅበረሰቦች መካከል መስተጋብርን መፍጠር መቻል ነው። በሌላ አነጋገር ኅብረ ባሕላዊነት ማለት ብዝሃነት በአንድነት ውስጥ የሚስተናገድበት ሚዛናዊ ቀመር ነው።

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

፩. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. አንድነት ማለት ዝንቅነት፣ ጉራማይሌነት ወይም ዥንጉርጉርነት ማለት ነው፡፡
2. ብዝሃነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ኅብራዊነት፣ ተመሳስሎ ወይም ወጥነት ነው፡፡
3. ኢትዮጵያዊያን ያለን አንድ ብሔራዊ መንግሥት ነው፡፡
4. በአካባቢ፣ በወንዜ ልጅነት አብሮነት ሊገኝ አይችልም፡፡
5. ብዝሃነትና አንድነት አይገናኙም፤ አንዱ ያለሌላው ይኖራል፡፡
6. በዥንጉርጉርነት ውስጥ ኅብር፣ በኅብር ውስጥ ዥንጉርጉርነት አለ፡፡
7. ብዝሃነትና አንድነት ተደጋጋፊ የአኗኗር ዘይቤዎችና ፍልስፍናዎች አይደሉም፡፡
8. ብዝሃነትና አንድነት ሰው ሰራሽ ቀለማት እንጂ ተፈጥሮአዊ ጉዳዮች አይደሉም፡፡

፪. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡

1. የአንድነት ኅብሩ፣ ተመሳስሎው ወይም ወጥነቱ የማይመሰረተው በምን ላይ ነው?

   ሀ. በመርሆችና በሕግጋት፣ ለ.በሥርዓቶችና ተቋማት፣ ሐ. በእሴቶችና እምነቶች መ. በግጭት

2. ማንነታችን የሚገለጸው በምንድን ነው?

   ሀ. በገቢያችን ለ. በቋንቋችን ሐ. በሀሳባችን መ. በደብተራችን

3. የሰው ልጅ ቁሳዊ፣ ማኅበራዊና ሥነልቡናዊ ዓለሙን የሚገነዘበውና የሚተረጉመው በ--ነው፡፡

   ሀ. በጽሑፍ ነው ለ. በመልክ በመልክ በማፍረስ ነው ሐ. በሥርዓት ነው መ. ልዩነታቸውን በማስፋት ነው

4. የአንድነትም ሆነ የብዝሃነት አቋሞች የሚበለጽጉት በ-------------ነው፡፡

   ሀ. በነዳጅ ለ. በህንጻ ግንባታ ሐ. በሩጫ መ. በትምህርት ሠ. አብሮ በመኖር

5. ዴሞክራሲ፣ ፍትሕና ነጻነት ሊያብቡ ወይም ሊቀጭጩ የሚችሉት በምንድን ነው?

   ሀ. መንግሥተ ቅርጽ ብዝሃዊ ስለሆነ ለ. የመንግሥቱ ቅርጽ አሃዳዊ ስለሆነ ሐ. የህዝብ ንቃተ ህሊና ስላደገ መ. ብሄርተኝነት ስለተቀነቀነ

6. ኢትዮጵያዊነት ከማይሞትባቸው ምክንያቶች ዋነኛው የቱ ነው?

   ሀ. ኅብረ መደባዊ መሠረቶች ያለው በመሆኑ ለ. መሠረቱ አንድ ነገድ በመሆኑ ሐ. የልዩነቶች መብዛት መ. ሰፊና ጥልቅ መሠረት ስለሌለው

## ክፍለ ትምህርት አራት: ጽሕፈት

**መርጣችሁ አንዱን እንደ ትዕዛዙ ተግብሩ፡፡**

፩. እያንዳንዳችሁ በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በሚመለከት አንቀጽ ጻፉ፡፡

፪. "በኢትዮጵያ የአስተዳደር ሥርዓቶች ታሪክ ውስጥ ከሚገኙ ቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል አንድነትና ብዝሃነት ዋነኞች ናቸው፤" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለክፍል የሚቀርብ ማብራሪያ ጻፉ፡፡

፫. የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት: ቃላት

ከታች ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተወሰኑትን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቀንቃኞች | ዘረኝነት | ርዕዮተዓለም | ያስርፃሉ | ቋንቋን |
| ታጋዮች | ጠባይ | ጨፍልቀው | ሕልውና | ሥነ-ልቡና |
| ፖለቲከኞች | እንከን | ተቀናቃኝ | እሴትን | አመለካከት |
| የአንድነት | ያቆለጳጵሳሉ | አመፅ | እምነት | ቀስቃሽ |
| የብዝሃነት | ትርክት | ገዢዎች | ዘርን | አነሳሽ |
| ቁልፍ | ማሳጣት | ሃይማኖት | እኩልነት | ዘረኝነት |

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### የድምፀች ቅንጅት

ቃላት ከድምጽ፣ ከምዕላድና ከቃላት ሊፈጠሩ ይችላሉ:: ከድምጽ ከሚፈጠሩት ጀምረን እንመልከት:: የአማርኛ ድምጾች ተናባቢና አናባቢ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ ይታወቃል::

**ከድምጽ የሚመሰረቱ ቃላት ምሳሌ አንድ፦**

| ተናባቢ | አናባቢ | ተናባቢ | አናባቢ | ተናባቢ | ቃል |
|---|---|---|---|---|---|
| ስ | ኧ | ው | | | ሰው |
| ስ | ኣ | ም | ኧ | | ሳመ |
| ው | ኧ | ድ | ኣ | ጅ | ወዳጅ |

ምሳሌ ሁለት፦ በመስራች ምዕላድ የሚመሰረቱ

ኢትዮጵያ   -ኣዊ  =  ኢትዮጵያዊ

ልጅ   -ነት   = ልጅነት

፩ ቀጥዩ ያልተጨመረባቸውን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ::

በግ   ወፍ   ፍየል   ቅርበት   ድፍረት   ተማሪ   ጎበዝ   ቂልነት

ሆዳም   ድርቀት   ግብርና   ደካማ   ሞኝነት   ፍጥረት   በሽታ   እህት

፪ የሚከተሉትን ጥገኛ ምዕላዶች ከነጻ ምዕላዶች ጋር በማቀናጀት ቃላትን መስርቱ::

-ኧኛ   -ኧት   -ነት

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአዳምጦና የአንብቦ መረዳት ስልቶችን በመጠቀም እንድታውቋቸው የታሰቡት የቋንቋው ይዘቶች ማለትም ስለንባብ ስልቶች፣ ስለገላጭና አመዛዛኝ ድርሰት አጻጻፍ፣ ስለ አንቀጽ አጻጻፍ፣ ስለ ድምጾች ቅንጀት፣ ስለቃላት ምስረታ፣ ነው:: የንባብ ስልቶች ሲባል አንድን ጽሑፍ ለምን ዓላማ ነው የማነበው? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል:: መረጃ ለመፈለግ፣ ለመረዳት፣ ወይስ ለፈተና ወዘተ. ለዚህ ሁሉ ግን የንባብ ስልታችን የተለያየ ነው:: በተጨማሪም የተሰጣችሁን ምንባብ በማንበብና ፍሬ ሀሳቡን በማውጣት ስለአንድነትና ብዝሃነት ያላችሁን ግንዛቤ አሳድጋችኋል:: ምንባቡንም ከተጠቀሱት የንባብ ስልቶች በአንዱ አንብባችኋል:: ጽሕፈት በሚለው ክፍልም ስለአንድነትና ብዝሃነት የምታውቁትን በመጻፍ ማብራራት ችላችኋል:: የጽሕፈት ልምዳችሁንም አንቀጽ በመጻፍ አሳይታችኋል:: አንቀጽ ደግሞ አንድ ሀሳብን የሚያስተላልፍ የጽሑፍ ክፍል ነው:: ቃላትን በተመለከተ ከምንባቡ በወጡ ቃላት አንቀጽ በመጻፍ የቃላት አጠቃቀም ችሎታችሁን በተግባር አሳይታችኋል:: ቃላት ለየትኛውም የጽሑፍ ስራ በመሰረታዊነት የሚያገለግሉ የቃል ክፍሎች ናቸው:: በመጨረሻም ሰዋስው በሚለው ክፍል የቃላት አፈጣጠርን በተመተለከተ ቃላትን በመመስረትና በተግባር በመስራት ተለማምዳችኋል:: የቃላት ምስረታ ማለት ድምጾች ተሰባስበው ትርጉም ያለው የቋንቋውን አንድ አካል የሚፈጥሩበት ሂደት ነው::

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድነትና ብዝሃነት ይለያያሉ ትላላችሁ ማብራሪያ ስጡ?
2. ስለድምጾች ምስረታ የተረዳችሁትን መነሻ በማድረግ አስር ቃላትን መስርቱ::
3. የድምጾች ቅንጅት በምን በምን ሊከናወን ይችላል?
4. አመዛዛኝ ድርሰት ከገላጭ ድርሰት የሚለይባቸውን ባህርያት ለይታችሁ ጻፉ::
5. ስለአካባቢያችሁ ማህበራዊ መስተጋብር ወይም ማህበራዊ አኗኗር ገላጭ ድርሰት ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1 ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ጨሩስ በጨሩስ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአንድነትንና ብዝሃነትን ዝምድና ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ቃላት ከድምጽና ከምዕላድ እንደሚመሰረቱ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በማዳመጥና በማንበብ ወቅት ያወቅኋቸውን ቃላት በጽሑፍ መጠቀም እችላላሁ፡፡ | | | |
| 4 | አመዛዛኝና ገላጭ ድርሰት መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ማህበራዊ መስተጋብራችንን በንግግር መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የአካባቢየን ማህበራዊ አውድ  በጽሑፍ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አስር: ስደት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- ከምታዳምጡት ጽሑፍ ተነስታችሁ የአካባቢያችሁን ማህበራዊ አውድ ትገልጻላችሁ::
- ቀለል ባሉ ንግግሮችና ውይይቶች ላይ ትሳተፋላችሁ::
- ለተለያዩ  ሀሳቦች የማጠቃለያ አሳብ ታመነጫላችሁ::
- በተለያየ ማህበራዊ አውድ ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- የቀረበላችሁን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ይዘቱን ትተነትናላችሁ::
- መምህሩ የሚጠቁሟችሁን አጋዥ መጻሕፍት ታነባላችሁ::
- አጭር ጽሑፍ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ታነባላችሁ::
- በተመረጡ ርዕሶች ላይ አንቀጽ ትጽፋላችሁ::
- አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ ወቅት ትክክለኛ ቃላትን ትጠቀማላችሁ::
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ::
- ሰዋስዋዊ ትክክለኝነቱን የጠበቀ አንቀጽ በመጻፍ ታሳያላችሁ::



## ክፍለ ትምህርት አንድ:- ማዳመጥ

## ስደትና መከራው

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስደት ስለሚያስከትለው መከራና እንግልት የምታውቁትንና  የሰማችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ::
2. ሰው ለምን ሀገሩን ጥሎ ይሰደዳል? ምክንያቶችን ዘርዝሩ::

**የተግባር መመሪያ**

መምህራችሁ "ስደትና መከራው" በሚል ርዕስ አንድ አጭር ጽሑፍ ያነቡላችኋል:: እናንተም በጥሞና አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል ማስታወሻ ያዙ::

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአዳመጣችሁት ንባብ ውስጥ መንግስት አልባ ሆነው ለህዝባቸው ምቹ ያልሆኑ አገራት እነማን ናቸው? ለምን ምቹ ያልሆኑ ይመስላችኋል? ማብራሪያ ስጡ።
2. ኢትዮጵያዊያን ለምን ሀገራቸውን ትተው ይሰደዳሉ? መጀመሪያ በጥንድ፣ ቀጥሎ በቡድን ሆናችሁ ለዚህ ጥያቄ መልስ ጻፉ።
3. ስደትን ለማስቀረት ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ? መፍትሄ ነው የምትሉትን ነገር ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።



## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ንግግር

**በአነስተኛ ቡድን ተደራጁና የሚከተሉትን ተግባራት ሥሩ።**

1. ዝግጅት አድርጋችሁ የስደትን አስከፊነት ወይም የስደትን ጥቅም በተመለከተ በማስረጃ አስደግፋችሁ ንግግር አድርጉ።
2. ተማሪዎች ስደት ጥቅሙ ነው ወይስ ጉዳቱ የሚያመዝነው? የየግላችሁን መልስ ጻፉና ለመምህራችሁ አቅርቡ።



## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ ንባብ

### ስደት

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ወደበለጸጉ አገራት የሚደረገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍልሰት እንዴት ትገልጹታላችሁ?
2. ኢትዮጵያዊያን ወደበለጸጉ አገራት የሚሰደዱት ለምንድን ነው? የምታውቁትን ግለጹ።
3. ስደት በተማረውና ባልተማረው ማህበረሰብ የሚካሄድ ነው። ልዩነቱ ምንድን ነው? አብራሩ።

ወደ ሰለጠኑ ሃብታም አገሮች የሚደረገው የሰለጠነ የሰው ኃይል ስደት በአሁኑ ወቅት በጣም አሳሳቢና አነጋጋሪ ሆኗል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያወጣው አንድ ዘገባ ከ1972 እስከ 1996 የፈረንጆች አቆጣጠር በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ወደ ምዕራብ የተሰደደው የሰለጠነ የሰው ጉልበት በገንዘብ ሲተመን ከአርባ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ይገመታል። እነዚህ ምሁሮች እንዲሰደዱ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ደግሞ በከፊል የሚከተሉት ናቸው።

የተሻለ የደሞዝ ክፍያ፣ የተሻለ የኑሮ ደረጃ፣ የበለጠና ሰፊ የስራም ሆነ የንግድ እድል፣ ቻይና ተቀባይ የሆነ ህብረተሰብና አካባቢ፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ነፃነት ናቸው።ይህ የምሁራኑ ስደት ለአገር መሪዎችና ለአገር ጉዳይ ተሟጋቾች በጣም አሳሳቢና የተወሳሰበ ፈተና ሆኗል። ሁለቱም ወገኖች ጉዳዩን

ከራሳቸው ጠባብ ትርጓሜ አንጻር ስለሚያዩት ችግሩን በጋራ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ አንዱ ሌላውን በመውቀስ ችግሩን አባብሰውታል፡፡

አብዛኞቹ መሪዎች ለትምህርት ሄደው የሚማሩ ግለሰቦችን፣ አገር ውስጥ ከተማሩ በኋላ የሚሰደዱ ምሁሮችን በጅምላ ራስ ወዳድ፤ ምቾትና ገንዘብ አሳዳጅ፣ አድርገው በመቁጠር ራሳቸውን ንጹህና የአገር ቤዛ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ምሁራኑ በአገራቸው ውስጥ ያሉትን የፖለቲካም ሆነ ህብረተሰባዊ አለመስተካከልንና ኋላቀርነትን ምክንያት በማድረግ ወደ አገር ላለመመለስ ያስወሰናቸውን እርግጠኛ ምክንያት ይደብቃሉ፡፡

ዓለም እያነሰች በሄደችበት በአሁኑ ወቅት እውቀትና ገንዘብ ያለው ግለሰብ መኖሪያውና ቤቱ የትም አገር ነው፡፡ የተሻለ የኑሮ ሁኔታ ማቅረብ የቻለ አገር የአለምን ምሁሮች እንደ ማግኔት ይስባል፡፡ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ለማደግ የሚያስፈልጋቸውን የሰለጠነ የሰው ጉልበት ስለሚያጡ እንደደኸዩና እንደደነቆሩ ይቀራሉ፡፡ የሚሰደዱትን ለማሰልጠን የወጣው ሀብትም ባክኖ ይቀራል፡፡ ይህ የምሁሮች መሰደድ ጉዳይ በቀላሉ የሚታይ አንድ ወጥ የሆነ ክስተት አይደለም፡፡ ከአገር ወደ አገር ከባህል ወደ ባህል የተለያየ መልክና አቀራረብ አለው፡፡ ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን አገሮች እንመልከት፤ ካናዳ፣ህንድ፣ ኬንያና ሜክሲኮ የሚሰደዱበት ምክንያት የተለያየ ነው፡፡ ከካናዳ ወደ አሜሪካ የሚኮበልሉ ምሁሮች አብዛኞቹ በአሜሪካ ኩባንያዎች ስራ አግኝተው በሙያቸው ይሰራሉ፡፡ የትምህርትና የሥልጠናው ደረጃ የተቀራረበ በመሆኑ በሙያቸው ስራ የማግኘት ችግር አይኖርባቸውም፡፡ የሚሰደዱበትም ምክንያት ነጻነት ፍለጋ ወይም ያለው የፖለቲካና የባህል ጭቆና አስመርሮአቸው አይደለም፡፡ አብዛኞቹ ከከፍተኛ የመንግስት ቀረጥ ለማምለጥ ይመስላል፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ምሁሮችን ከሀገር እንዲሰድዱ የሚያደርጓችው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. በቀጣዩ የምንባብ ክፍል ምን ሀሳብ ይነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ከህንድ ወደ ምዕራብ አገሮች የሚደረገው ስደት ታሪካዊ ወደ ሆነ ሁለተኛ ምዕራፍ ተሸጋግሮአል፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት በርካታ የህንድ ምሁሮች በጣም ከፍተኛ ሥልጣኔ ከነበራቸው ሀገሮች ይልቅ ተፈላጊነታቸው በሶስተኛው አለም አገሮች ነበር፡፡ ወደ ምዕራብ የሚሰደዱት ደግሞ የሚሰሩት በሙያቸው ሳይሆን በተገኘው ሥራ ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የህንድ ባለሙያዎች ተለምነውና አገር አማርጠው የሚሄዱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ህንዳዊያን ወደ አሜሪካ አውሮፓ በሙያቸው ተቀጥረው ይሰደዳሉ፡፡ ከካናዳና ህንድ ወደ አሜሪካ የሚሰደዱ ምሁሮች አገራቸው ውስጥ የሰለጠኑ ናቸው፡፡ በምሳሌነት ከቀረቡት አገሮች ተሰዳጅ ኬንያዊያን፣ ለትምህርት መጥተው የቀሩ በሙያቸው ስራ ያገኛሉ፡፡ ለስብሰባ መጥተው ወይም በተለያየ መንገድ አሜሪካና አውሮፓ የሚሰደዱት ግን አብዛኞቹ በሙያቸው ስራ አያገኙም፡፡ ከሜክሲኮ እንደዚሁ ኮብልለው የሚመጡ በሙያቸው ሥራ አያገኙም፡፡ ከእነዚህ አራት አገሮች፣ ለምሳሌ ካናዳዊያን ወደ አሜሪካ ቢሰደዱም ከነሱ የበለጠ በብዛትም ሆነ በትምህርት ከሶስተኛ አገሮች ወደ ካናዳ ይሰደዳሉ፡፡ ስለሆነም የሚደርሰው ጉዳት በጣም ትንሽ ነው፡፡ ህንዶች በተለይም በአሁኑ ወቅት በየሄዱበት አገር በቴክኖሎጂና ሳይንስ ግንባር ቀደም በመሆናቸው ወደ አገራቸው ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ገንዘብ በመላክ ላይ ናቸው፡፡ ከዚያም አልፎ በስደት ያገኙትን የንግድ ተሞክሮ ወደ አገራቸው በማሸጋገር ይህንን የሰለጠነ የሰው ጉልበት ወደ አገራቸው ጥቅም በመቀየር ላይ ናቸው የሚሉ ምሁሮች አሉ፡፡

ከዚህ በተጻራሪ መልኩ፣ በርካታ የሶስተኛ አገር መሪዎች ውጭ ካለው ህዝባቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት አሉታዊ ነው:: በዚህ ረገድ ተሻልን የሚሉትም ህዝባቸውን የሚጠይቁት ባሉበት ሆነው ገንዘብ መላኩን እንዲቀጥሉ ነው:: በስደት ያሉትም አገር ውስጥ ያለውን አለመስተካከል ባሉበት የበለጸገ አገር መነፅር በማየት ወደየአገሮቻቸው ሲመለሱ የማይችሉትን ጥያቄዎች ያቀርባሉ:: በመሀሉ አገርም፣ የተሰደደው ዜጋም ይጎዳል:: አገሮችን ለማሳደግ፣ ድህነትን ለማጥፋት፣ የሚያስፈልጋቸውን የሰለጠነ የሰው ጉልበት ያጣሉ:: በስደት ያሉት ባለሙያዎችም ተምረው እንዳልተማሩ፣ አገር ከመምራት፣ ከማሳደግና ትውልዳዊ ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ርቀው አዲስ ኑሮ ይኖራሉ:: ይህን ችግር በወቅቱ ለመፍታት ካልተቻለ ለዘለቄታው የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ ነው:: ወደ ውጭ የሚኮበልለውን ምሁር ማቆምና ጠፍቶ የቀረውን ማስመለስ የሚቻልበት ዘዴ በጋራ መሻት ያስፈልጋል::

በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያምኑ ግለሰቦች አገር ውስጥ የሚቀበላቸው ከሌለ ሙከራቸው ፍሬ አልባ ነው:: ውጭ ያሉትም ለመመለስ ወይም ግንኙነታቸውን ለማደስና ለማጠናከር ካልሞከሩ አገር ቤት ያሉት ወደ ውጭ ማማተራቸውን አያቆሙም:: እርግጥ ለዚህ ሁሉ መንግስታት የሚገባቸውን ሚና መጫወት አለባቸው:: ከድህነትና ኋላ ቀርነት ለመላቀቅ ደግሞ መንግስት አመራርንና አስተዳደርን ማስተካከል አለበት:: ይህ ደግሞ እውቀትንና ተሞክሮን ይጠይቃል:: እውቀትና ተሞክሮ ያለው ዜጋ የሚሰደድ ከሆነ አገር አደጋ ላይ ይወድቃል:: መንግስት፣ አገር ቤት ያሉና የተሰደዱ ባለሙያዎች ጥቅሞቻቸው የተሳሰሩ መሆናቸውን በመረዳት በጋራ የሚቀራረቡበትን ዘዴ መሻት ይገባዋል::

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ::**

1. በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ወደ ምዕራብ የተሰደደው የሰለጠነ የሰው ጉልበት በገንዘብ ሲተመን አርባ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይደርሳል::
2. ምሁሮች እንዲሰደዱ ምክንያታቸው ሀገር መጥላት፣ በሌላው ዓለም የመኖር ፍላጎትና ከዘመድ መለየት ነው::
3. የምሁራኑ ስደት ለአገር መሪዎችና ለአገር ጉዳይ ተሚጋቾች በጣም አሳሳቢና የተወሳሰበ ፈተና ነው::
4. ምሁሮች ወደ አገር ላለመመለስ ያስወሰናቸውን ትክክለኛ ምክንያትና ፍላጎት በጥብቅ ይደብቃሉ::
5. የተሻለ የኑሮ ሁኔታ ማቅረብ የቻለ አገር የአለምን ምሁሮች እንደ ማግኔት በመሳብ አገሩን ያራቂታል::
6. በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ለማደግ የሚያስፈልጋቸውን የሰለጠነ የሰው ጉልበት ስለሚያጡ እንደደኸዩ ይቀራሉ::
7. የምሁሮች ስደት ከአገር አገር፣ ከባህል ባህል የተለያየ መልክና አቀራረብ እንደሌለው ይገለጻል::
8. ከካናዳ ወደ አሜሪካ የሚኮበልሉ ስደተኞች ምክንያታቸው ገንዘብ ፍለጋ ነው::

፪. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ምረጡ።

1. የምሁሮች ስደት መነሻ ያልሆነው ምንድን ነው?

    ሀ. የተሻለ የደሞዝ ክፍያ    ለ. የበለጠ የስራና የንግድ እድል ፍለጋ

    ሐ. የተሻለ ህብረተሰብና አካባቢ ፍለጋ    መ. የህብረተሰብ ለውጥ

2. አብዛኞቹ መሪዎች ለትምህርት ሄደው የቀሩ ግለሰቦችን የሚሏቸው ምንድን ነው?

    ሀ. ሀገር ወዳድ    ለ. ድህነት ወዳድ    ሐ. ገንዘብ ጠል    መ. ምቾት ወዳጅ።

3. አብዛኛው የአደጉ ሀገራት ምሁሮች የሚሰደዱት ለምንድን ነው?

    ሀ. ለሀገር ፍቅር    ለ. ለፖለቲካ መሪነት.    ሐ. ለድርድር    መ. ለነጻነት

4. አገሮች ለማደግና ድህነትን ለማጥፋት የሚያስፈልጋቸው ምንድን ነው?

    ሀ. ያልሰለጠነ የሰው ሀይል    ለ. ልመና    ሐ. የጦር መሣሪያ    መ. ሀገር ወዳድ ዜጋ

5. ወደ ውጭ የሚኮበልለውን ምሁር ማቆምና ጠፍቶ የቀረውን ማስመለስ የሚቻልበት ዘዴ ምንድን ነው?

    ሀ. ምሁሮች ለሀገር ግንባታ ያላቸውን ሚና ማሳነስ    ለ. የሥራ ግብር መጨመር

    ሐ. የተመቻቸ የስራ ቦታና ክፍያ እንዲኖር ማድረግ    መ. ቁጥጥር መጨመር



## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ጽሕፈት

፩. በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ።

<u>ርዕሶች</u>

መምህርና ተማሪ

ገጠርና ከተማ

ትምህርት ቤትና ገበያ

፪. እናንተ በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።
(ስደት በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ የመጨረሻው አንቀጽ የተጻፈው በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት መሆኑንም ልብ በሉ)።

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ቃላት

፩. ከዚህ በታች የቀረቡ ድርብ ቃላትን ምሳሌ በማድረግ የራሳችሁን አስር ድርብ ቃላት መስርቱ፡፡

ምሳሌ፦ ዓመት በዓል

አየር ወለድ

፪. ከታች ለቀረቡ ድርብ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ልቦለድ
2. ሰው ሰራሽ
3. አሳበ ሩቅ
4. የሩቅ ዘመድ
5. አርሶ አደር
6. ቅጥየለሽ
7. እጅ ስራ
8. ግብረ ገብ
9. ክብረ በዓል
10. ወርቅ አንጣሪ
11. አውራ ዶሮ
12. መሥሪያ ቤት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

፩. አስር አረፍተ ነገሮችን ከመሰረታችሁ በኋላ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎቹን ለዩታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1.----------------------------------------------------------------

2.----------------------------------------------------------------

3.----------------------------------------------------------------

4.----------------------------------------------------------------

5.----------------------------------------------------------------

6. ----------------------------------------------------------------

7.-----------------------------------------------------------------

8.-----------------------------------------------------------------

9.-----------------------------------------------------------------

10.-----------------------------------------------------------------

--------------------------------------

፫. ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጻቸው የተስማሙ አስር አረፍተ ነገሮች ጻፉ፡፡

1.------------------------------------------------------------------

2.------------------------------------------------------------------

3.------------------------------------------------------------------

4.------------------------------------------------------------------

5.------------------------------------------------------------------

6. -----------------------------------------------------------------

7.------------------------------------------------------------------

8.------------------------------------------------------------------

9.------------------------------------------------------------------

10.------------------------------------------------------------------

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአዳምጦና የአንብቦ መረዳት ስልቶችን በመጠቀም የስደትን ምንነትና አስከፊነት ተገንዝባችኋል፡፡ ጽሒፈት በሚለው ክፍልም በተሰጣችሁ ርዕስ ድርሰት በመጻፍ ማብራራት ችላችኋል፡፡ ድርሰት ማለት ደግሞ በጭብጦች የተከፋፈሉና በአንቀጽ የተደራጁ ሀሳቦችን የያዘ ሰፊው የጽሑፍ ክፍል ነው፡፡ ቃላትን በተመለከተ ከምንባቡ በወጡ ድርብ ቃላት አንቀጽ በመጻፍ የቃላት አጠቃቀም ችሎታችሁን በተግባር አሳይታችኋል፡፡ ድርብ ቃላት በውስጣቸው ከአንድ በላይ አናባቢዎችን የያዙ የቋንቋው የቃል ክፍሎች ናቸው፡፡ በመጨረሻም ሰዋስው በሚለው ክፍል አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን በሀረግ ለይታችሁ ማሳየትን ተለማምዳችኋል፡፡ አረፍተ ነገሮች በስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ተከፍለው ይጻፋሉ፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. በእናንተ አስተሳሰብ ስደት ጠቃሚ ነው ወይስ ጎጂ?
2. የአረፍተ ነገር ዋና ዋና ክፍሎች ምን ምን ናቸው?
3. የክፍላችን አንድ ጎበዝ ተማሪ ወደቤቱ ሲሄድ ወደቀ፡፡ ከሚለው አረፍተ ነገር ስማዊና ግሳዊ ሀረጉን ለይታችሁ ጻፉ፡፡
4. የባለቤትና የስም ስምምነት ማለት ምን ማለት ነው?
5. የድርብ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች ከሌሎች ቃላት ፍች ይለያል? አብራሩ፡፡
6. ስለአዳመጣችሁት ቅንጫቢ ጽሑፍ በቃል ማብራሪያ ስጡ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

1. ከዚህ በታች በምዕራፉ አስር የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(V)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁት ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የስደትን አስከፊነት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የድርብ ቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | አረፍተ ነገሮች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከፈሉ ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ሰለ አመዛዛኝ ድርሰት ምንነት መናገር እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ድርብ ቃላትን መመስረት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | የስደትን አስከፊነት በገላጭ ድርሰት ጽፌ ማስነበብ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ያዳመጥሁትን ቅንጫቢ በጽሁፍ ማስፈር እችላለሁ፡፡ | | | |

2. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ማጣቀሻዎች

ሻሂዳ ሁሴን፡፡ (2009ዓ.ም)፡፡ ግንቦት 6፣ ሪፖርተር ጋዜጣ፡፡

ሽብሩ ተድላ፡፡ (2011)፡፡ ከየት ወደየት፡፡ አዲስ አበባ፡ ኢክሊክስ፡፡

በአሉ ግርማ፡፡ (1984)፡፡ ኦሮማይ፡፡ አዲስ አበባ፡ ኩራዝ አሳታሚድርጅት፡፡

በዕውቀቱ ሥዩም፡፡ (2012)፡፡ ስደምኤል፡፡ አዲስ አበባ፡ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት፡፡

ባዬ ይማም፡፡ (2009)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው፡፡ ሦስተኛ የተሻሻለ ዕትም፡፡ አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፡፡

ዋልታ ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ኮረፖሬሽን አ.ማ፡፡ (2017)፡፡ ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡ (1996)፡፡ ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ደረጀ ይመር፡፡ (2021)፡፡ ሽክም፡፡ አዲስ አድማስ፡፡ ሰኔ 2921፤ አዲስ አበባ፡፡

ፀጋየ ገብረ መድህን፡፡ (1966)፡፡ እሳት ወይ አበባ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

Appleyard, David . 1995. Colloquial Amharic. New York: Routledge.

Hawassa Online //www.hawassaonline.com/subpage_articles.php?id=259&catagory=Psychology፣ ነሐሴ 13፣ 2013 ዓ.ም)

www.lifewithoutlimbs.org

www.attitudeisaltitude.com/about-nick-his-story)

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ Ha | ሁ Hu | ሂ Hi | ሃ Ha | ሄ Hie | ህ H | ሆ Ho | ዐ A | ዑ U | ዒ I | ዓ A | ዔ Ie | ዕ E | ዖ O |
| ለ Le | ሉ Lu | ሊ Li | ላ La | ሌ Lie | ል L | ሎ Lo | ዘ Ze | ዙ Zu | ዚ Zi | ዛ Za | ዜ Zie | ዝ Z | ዞ Zo |
| ሐ Ha | ሑ Hu | ሒ Hi | ሓ Ha | ሔ Hie | ሕ H | ሖ Ho | ዠ Zhe | ዡ Zhu | ዢ Zhi | ዣ Zha | ዤ Zhie | ዥ Zh | ዦ Zho |
| መ Me | ሙ Mu | ሚ Mi | ማ Ma | ሜ Mie | ም M | ሞ Mo | የ Ye | ዩ Yu | ዪ Yi | ያ Ya | ዬ Yie | ይ Y | ዮ Yo |
| ሠ Se | ሡ Su | ሢ Si | ሣ Sa | ሤ Sie | ሥ S | ሦ So | ደ De | ዱ Du | ዲ Di | ዳ Da | ዴ Die | ድ D | ዶ Do |
| ረ Re | ሩ Ru | ሪ Ri | ራ Ra | ሬ Rie | ር R | ሮ Ro | ጀ Je | ጁ Ju | ጂ Ji | ጃ Ja | ጄ Jie | ጅ J | ጆ Jo |
| ሰ Se | ሱ Su | ሲ Si | ሳ Sa | ሴ Sie | ስ S | ሶ So | ገ Ge | ጉ Gu | ጊ Gi | ጋ Ga | ጌ Gie | ግ G | ጎ Go |
| ሸ She | ሹ Shu | ሺ Shi | ሻ Sha | ሼ Shie | ሽ Sh | ሾ Sho | ጠ Te | ጡ Tu | ጢ Ti | ጣ Ta | ጤ Tie | ጥ T | ጦ To |
| ቀ Qe | ቁ Qu | ቂ Qi | ቃ Qa | ቄ Qie | ቅ Q | ቆ Qo | ጨ Che | ጩ Chu | ጪ Chi | ጫ Cha | ጬ Chie | ጭ Ch | ጮ Cho |
| በ Be | ቡ Bu | ቢ Bi | ባ Ba | ቤ Bie | ብ B | ቦ Bo | ጰ Pe | ጱ Pu | ጲ Pi | ጳ Pa | ጴ Pie | ጵ P | ጶ Po |
| ተ Te | ቱ Tu | ቲ Ti | ታ Ta | ቴ Tie | ት T | ቶ To | ጸ Tse | ጹ Tsu | ጺ Tsi | ጻ Tsa | ጼ Tsie | ጽ Ts | ጾ Tso |
| ቸ Che | ቹ Chu | ቺ Chi | ቻ Cha | ቼ Chie | ች Ch | ቾ Cho | ፀ Tse | ፁ Tsu | ፂ Tsi | ፃ Tsa | ፄ Tsie | ፅ Ts | ፆ Tso |
| ኀ Ha | ኁ Hu | ኂ Hi | ኃ Ha | ኄ Hie | ኅ H | ኆ Ho | ፈ Fe | ፉ Fu | ፊ Fi | ፋ Fa | ፌ Fie | ፍ F | ፎ Fo |
| ነ Ne | ኑ Nu | ኒ Ni | ና Na | ኔ Nie | ን N | ኖ No | ፐ Pe | ፑ Pu | ፒ Pi | ፓ Pa | ፔ Pie | ፕ P | ፖ Po |
| ኘ Gne | ኙ Gnu | ኚ Gni | ኛ Gna | ኜ Gnie | ኝ G | ኞ Gn | ቨ ve | ቩ vu | ቪ vi | ቫ va | ቬ vie | ቭ v | ቮ vo |
| አ A | ኡ U | ኢ I | ኣ A | ኤ Ie | እ n | ኦ o | ኰ Kue | | ኲ Kui | ኳ Kua | ኴ Kuie | | ኵ Kwo |
| ከ Ke | ኩ Ku | ኪ Ki | ካ Ka | ኬ Kie | ክ E | ኮ O | ዀ Kue | | ዂ Kui | ዃ Kua | ዄ Kuie | | ዅ Kwo |
| ኸ Ke | ኹ Ku | ኺ Ki | ኻ Ka | ኼ Kie | ኽ K | ኾ Ko | ቈ Que | | ቊ Qui | ቋ Qua | ቌ Quie | | ቍ Qwo |
| ወ We | ዉ Wu | ዊ Wi | ዋ Wa | ዌ Wie | ው K | ዎ Ko | ጐ Gue | | ጒ Gui | ጓ Gua | ጔ Guie | | ጕ Gwo |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ 10 | ፳ 20 | ፴ 30 | ፵ 40 | ፶ 50 | ፷ 60 | ፸ 70 | ፹ 80 | ፺ 90 | ፻ 100 |

## የግዕዝ ቁጥሮችና የአረብኛ አቻቸው

| የግዕዝ ቁጥሮች | የአረብ ቁጥሮች | የግዕዝ ቁጥሮች | የአረብ ቁጥሮች |
|---|---|---|---|
| ፩ | 1 | ፳፬ | 24 |
| ፪ | 2 | ፳፭ | 25 |
| ፫ | 3 | ፳፮ | 26 |
| ፬ | 4 | ፳፯ | 27 |
| ፭ | 5 | ፳፰ | 28 |
| ፮ | 6 | ፳፱ | 29 |
| ፯ | 7 | ፴ | 30 |
| ፰ | 8 | ፴፩ | 31 |
| ፱ | 9 | ፴፪ | 32 |
| ፲ | 10 | ፴፫ | 33 |
| ፲፩ | 11 | ፴፬ | 34 |
| ፲፪ | 12 | ፴፭ | 35 |
| ፲፫ | 13 | ፴፮ | 36 |
| ፲፬ | 14 | ፴፯ | 37 |
| ፲፭ | 15 | ፴፰ | 38 |
| ፲፮ | 16 | ፴፱ | 39 |
| ፲፯ | 17 | ፵ | 40 |
| ፲፰ | 18 | ፵፩ | 41 |
| ፲፱ | 19 | ፵፪ | 42 |
| ፳ | 20 | ፵፫ | 43 |
| ፳፩ | 21 | ፵፬ | 44 |
| ፳፪ | 22 | ፵፭ | 45 |
| ፳፫ | 23 | ፵፮ | 46 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፵፯ | 47 | ፸፩ | 71 |
| ፵፰ | 48 | ፸፪ | 72 |
| ፵፱ | 49 | ፸፫ | 73 |
| ፶ | 50 | ፸፬ | 74 |
| ፶፩ | 51 | ፸፭ | 75 |
| ፶፪ | 52 | ፸፮ | 76 |
| ፶፫ | 53 | ፸፯ | 77 |
| ፶፬ | 54 | ፸፰ | 78 |
| ፶፭ | 55 | ፸፱ | 79 |
| ፶፮ | 56 | ፹ | 80 |
| ፶፯ | 57 | ፹፩ | 81 |
| ፶፰ | 58 | ፹፪ | 82 |
| ፶፱ | 59 | ፹፫ | 83 |
| ፷ | 60 | ፹፬ | 84 |
| ፷፩ | 61 | ፹፭ | 85 |
| ፷፪ | 62 | ፹፮ | 86 |
| ፷፫ | 63 | ፹፯ | 87 |
| ፷፬ | 64 | ፹፰ | 88 |
| ፷፭ | 65 | ፹፱ | 89 |
| ፷፮ | 66 | ፺ | 90 |
| ፷፯ | 67 | ፺፩ | 91 |
| ፷፰ | 68 | ፺፪ | 92 |
| ፷፱ | 69 | ፺፫ | 93 |
| ፸ | 70 | ፺፬ | 94 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፺፭ | 95 | ፬፻ | 400 |
| ፺፮ | 96 | ፭፻ | 500 |
| ፺፯ | 97 | ፮፻ | 600 |
| ፺፰ | 98 | ፯፻ | 700 |
| ፺፱ | 99 | ፰፻ | 800 |
| ፻ | 100 | ፱፻ | 900 |
| ፪፻ | 200 | ፲፻ | 1000 |
| ፫፻ | 300 | ፼ | 10000 |